**DSpace Institution**

**DSpace Repository** **http://dspace.org**

Folklore/Cultural Studies Thesis and Dissertations

2021-02-22

# þÿ•Í- ¥•ð `+Ê ð•e 5 `Bë 5 u•u `

þÿ ó•} ð•`

http://ir.bdu.edu.et/handle/123456789/11911

*Downloaded from DSpace Repository, DSpace Institution's institutional repository*

ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ

ሂዩማኒቲስ ፋኩሊቲ

ፎክሎር (ባህል ጥናት) ትምህርት ክፍል ድኅረ-ምረቃ መርሃ ግብር

# ነውር እንደማህበራዊ ደንብ ማስጠበቂያ ስልትነት በዶርዜ ማህበረሰብ

ለፎክሎር የሁለተኛ ዲግሪ ከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት

በ

አዳነች ደንበሌ

አማካሪ፡- ዋልተንጉሥ መኮንን (ዶ/ር)

ጥር 2013 ዓ.ም

ባህርዳር

# ነውር እንደማህበራዊ ደንብ ማስጠበቂያ ስልትነት

# በዶርዜ ማህበረሰብ

ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ሂዩማኒቲስ ፋኩሊቲ

ፎክሎር (ባህል ጥናት) ትምህርት ክፍል ድኅረ-ምረቃ መርሃ ግብር

ለፎክሎር የሁለተኛ ዲግሪ ከፊል ማሟያነት  የቀረበ ጥናት

በ

አዳነች ደንበሌ

ጥር 2013 ዓ.ም

ባህር ዳር

**ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ሂዩማኒቲስ ፋኩሊቲ**

**ፎክሎር (የባህል ጥናት) ትምህርት ክፍል**

**ድኅረ-ምረቃ መርሃ ግብር**

# ነውር እንደማህበራዊ ደንብ ማስጠበቂያ ስልትነት

# በዶርዜ ማህበረሰብ

**በ**

**አዳነች ደንበሌ**

**2013 ዓ.ም**

የፈታኝ ቦርድ አባላት

አማካሪ.......................................... ፊርማ................

የውስጥ ፈታኝ................................. ፊርማ ..............

የውጭ ፈታኝ.................................. ፊርማ..............

# በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ በጋሞ ዞን የጨንቻ ወረዳ ካርታ



# የቀበሌዎች ማሳያ



Zute_Kebele
Zolo_Kebele
Yoyira_Kebele
Wobera_Kebele
Woro_Kebele
Tutusha_Kebele
Tada_Kebele
Shasha_Kebele
Shaye_Kebele
Shama_Kebele
Shale_Kebele
Holoo_Kebele
Masho_Kebele
Malda_Kebele
MaponaZolo_Kebele
Losha_Kebele
Kogo_Kebele
Kale_Kebele
Hirpo_Kebele
Hayzo_Kebele
Gultaguye_Kebele
Gule_Kebele
Gordye_Kebele
Gendo_Kebele
Gadino_Kebele
Tula_Kebele
Otha_Kebele
Elo_Kebele
Eleza_Kebele
ElenaChare_Kebele
Doshke_Kebele
DorzeTown_Kebele
Degagema_Kebele
Danbo_Kebele
Dolonzara_Kebele
BoyenaTupa_Kebele
Bele_Kebele
Ayira_Kebele
AmaranaBodo_Kebele
EzoTown_Kebele
chencha kebele

# ማረጋገጫ

ይህ ጥናት ነውር እንደ ማህበራዊ ደንብ ማስጠበቂያ ስልትነት በዶርዜ ማህበረሰብ በሚል ርዕስ በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ሂዩማኒቲስ ፋኩሊቲ በፎክሎር (ባህል ጥናት) ትምህርት ክፍል የድኅረ ምረቃ መርሃ ግብር፣ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት ያቀረብኩት ከዚህ በፊት በሌሎች አጥኝዎች ያልተሰራ መሆኑን እንደሚከተለው በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

**ስም፡** አዳነች ደንበሌ

**ፊርማ**……………………

**ቀን**…………………..

## አበርክቶ

ለእናቴ ለወ/ሮ አበራሽ መሸሻ

ለአባቴ አቶ ደንበሌ ዳሮታ

ለወንድሜ ዳኛቸው ደንበሌ

ይሁንልኝ

# ምስጋና

ይህን ጥናት በሚጠናበት ወቅት ከጅምሩ አንስቶ እስከመጨረሻ ከፈጣሪ ቀጥሎ በርካታ አካላት አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡ በመጀመሪያ ይህን የትምህርት እድል እንዳገኝ የላከኝ አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ልባዊ ምስጋናዬ እነሆ፡፡ የተለያዩ መርጃ መጻሕፍትን በመጠቆምና በመስጠት ጥናቱን በማረም ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ላገዙኝና ላበረታቱኝ የእውቀት አባቴ ዋልተንጉስ መኮንንን (ዶ/ር) መቼም የማልረሳው መምህሬ አባቴ ነህና ምስጋናዬ ከልቤ አቀርባለሁ፡፡

ቀጥሎ የተለያዩ መርጃ መጻሕፍትን በሶፍት ኮፒ በመስጠት የተባበረችኝ የቀድሞ መምህሬ ባሁን ሰአት የስራ ባልደረባዬ ለሆነችው ለመምህርት ህሊና ሰብስበው ምስጋናዬ ይድረስሽ፡፡ ለጥናቱ መሳካት ያላቸውን ዕውቀት ሳይሰስቱ መረጃ ለሰጡኝ ለጥናቱ ባለቤቶች/ተጠኚዎች እና አብረውኝ ከቦታ ቦታ ሲዘዋወሩ ለነበሩ ለአቶ አስፋው ሶሬ እና ለአቶ ጋሞ ጋጎ እድሜና ጤና ይስጥልኝ፡፡ እንዲሁም የክፍል ጓደኞቼ ስታበረታቱኝ ለነበራችሁ በጣም አመሰግናለሁ፡፡

ልዩ ምስጋና ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ከልጅነት አንስቶ ላሳደጉኝ ላስተማሩኝ ለቁም ነገር ላበቁኝ ወላጆቼ፣ ወንድሜ ዳኜ ይኸው ያሰባችሁት ተሳክቷል፡፡ ዕድሜን ከጤና ጋር ጨምሮ ይስጥልኝ፡፡

# ማውጫ

ይዘት ገፅ

ምስጋና ........ i
ማውጫ ........ ii
አጠቃሎ ........ v
ምዕራፍ አንድ ........ 1
መግቢያ ........ 1
1.1 የጥናቱ ዳራ ........ 2
1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 6
1.3 የጥናቱ አላማ ........ 7
1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ ........ 8
1.5 የጥናቱ ወሰን ........ 8
1.6 ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ ሀሳቦች ........ 9
1.7 የጥናቱ አደረጃጀት ........ 9
1.8 የመስክ ተሞክሮ ........ 10
ምዕራፍ ሁለት ........ 12
ክለሳ ድርሳን ........ 12
2.1. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት/Related literature ........ 12
2.1.1 የሀገር ውስጥ ጥናቶች ........ 12
2.1.2 በውጭ ሀገራት ነውሮች ላይ የተሰሩ ጥናቶች ........ 15
2.2. ፅንሰ ሀሳባዊ ዳራ ........ 17
2.2.1. ማህበራዊ ልማዶች/Social norms/ ........ 17
2.2.2. ልማዳዊ ሕጎች/Customary Law/ ........ 18
2.2.3. የነውር ምንነት /The meaning of taboo ........ 19
2.2.4. የነውሮች መፈጠር ምክንያትና ፋይዳ ........ 20
2.2.5. የነውር አይነቶች/Types of taboo ........ 21
2.2.6. የነውሮች ለውጥና ተከታታይነት/Change and continuity ........ 23
2.2.7. ማሕበራዊ ቅጣቶችና ሽልማቶች/Social sanction and rewards ........ 25
2.3. ንድፈ ሀሳባዊ ዳራ ........ 25
2.3.1. ፍካሬ ልቦናዊ ንድፈ ሀሳብ/ Psychoanalytical theory ........ 25

2.3.2.ተግባራዊ/ጠቀሜታዊ ንድፈ ሀሳብ/Functional theory ........ 26
ምዕራፍ ሶስት ........ 28
የጥናቱ ዘዴ ........ 28
3.1. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ........ 28
3.1.1. ምልከታ ........ 28
3.1.2 ቃለመጠይቅ ........ 29
3.1.3. ቡድን ውይይት ........ 30
3.1.4 መዛግብት ፍተሻ ........ 30
3.2. የናሙና ዘዴ ........ 30
3.3. የመረጃ መተንተኛ ዘዴ ........ 31
ምዕራፍ አራት ........ 32
4. የዶርዜ ማህበረሰብ አካባቢያዊ ዳራ ........ 32
4.1. የመልክዓምድር አቀማመጥና የአየር ሁኔታ ........ 32
4.2. የመሪዎች/የአለቆች አመራረጥና ሹመት ስርዓት ........ 33
4.2.1. ዴሙሳ (ንጉስ) ........ 33
4.2.2. የአለቃ አመራረጥ ........ 33
4.2.3. የአለቃ ሹመት ........ 34
4.2.4. የአለቃ ዋና አገልግሎት (ስራ) ........ 35
4.2.5. የአለቃ አቀያየርና የስልጣን ሽረት ........ 35
4.3. የጋብቻ አፈፃፀም ........ 36
ምዕራፍ አምስት ........ 38
የመረጃ ትንተና ........ 38
5.1. የዶርዜ ማህበረሰብ የነውር አይነቶችና ምክንያቶቻቸው ........ 38
5.1.1. ክብርን ከማስጠበቅ አንፃር የሚገለጹ ነውሮች ........ 38
5.1.2. በሌላ ወገን ላይ ከሚደርሱ ነገሮች አንጻር ........ 44
5.1.3. ዝምድናን ከመጠበቅ ጋር ተያያዥ ነውሮች ........ 48
5.1.4. የትዳርን ሕልውና ከማስጠበቅ ጋር ተያያዥ ነውሮች ........ 50
5.1.5. ለሴቶች የሚከለከሉ ነገሮች ........ 51
5.1.6. ከእምነት ጋር ተያያዥ ነውሮች ........ 53
5.2. የዶርዜ ማህበረሰብ ማህበራዊ ቅጣቶችና ሽልማቶች ........ 56
5.2.1. ማህበራዊ ቅጣቶች ........ 56

5.2.2. ማህበራዊ ሽልማቶች ......... 59
5.3. የነውሮች ፋይዳ እና ጉዳት በዶርዜ ማህበረሰብ ......... 59
5.3.1. የነውሮች ፋይዳ ......... 59
5.3.2. የነውሮች ፋይዳ ከነውር አይነቶች አንጻር ......... 60
5.3.3 የነውሮች ጉዳት ......... 62
5.4. የዶርዜ ማህበረሰብ የነውር አይነቶች ላይ የታየ ለውጥና ተከታታይነት ......... 62
ምዕራፍ ስድስት ......... 66
ማጠቃለያና የይሁንታ ሀሳብ ......... 66
6.1. ማጠቃለያና የጥናቱ ውጤቶች ......... 66
6.1.1. ማጠቃለያ ......... 66
6.1.2. የጥናቱ ውጤቶች ......... 68
6.2. የይሁንታ ሀሳብ ......... 69
ዋቢዎች ......... 72
የመረጃ አቀባዮች ስም ዝርዝር ......... 75

# አጠቃሎ

*ይህ ጥናት ነውር እንደማህበራዊ ደንብ ማስጠበቂያ ስልትነት በዶርዜ ማህበረሰብ በሚል ርዕሰ ጉዳይ የተጠና ነው፡፡ የጥናቱ አላማ በማህበረሰቡ አስተሳሰብና አመለካከት ውስጥ ነውር ያለውን ቦታ በመመርመር የማህበረሰቡን አስተሳሰብ አመለካከትና እውቀት መግለጽ ነው፡፡ የጥናቱን አላማ ከግብ ለማድረስ በዋነኝነት ቃለ መጠይቅ፣ ቡድን ተኮር ውይይት፣ ምልከታ እና መዛግብት ፍተሻ በማካሄድ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ የጥናቱ አይነት አይነታዊ ገላጭ ምርምር ነው፡፡ በጥናቱ ተሳታፉ የነበሩ ሰዎች በአላማ ተኮር እና ጠቋሚ ናሙና ስልት የተመረጡ ናቸው፡፡ በመረጃው መሰረትም ክብርን ከማስጠበቅ አንጻር፣ በሌላ ወገን ላይ በሚደርሱ ነገሮች፣ ዝምድናን ከማስጠበቅ፣ የትዳርን ሕልውና ከማስጠበቅ ጋር ፣ለሴቶች የሚከለከሉ እና ከእምነት ጋር ተያያዥ ነገሮችን ጉዳይ ያደረጉ 52 ነውሮች የጥናቱ አካል ተደርገዋል፡፡ በእነዚህ ላይ የተደረገው ምደባና ትንተና ይዘታቸውን መሰረት ያደረገ ነው፡፡ ከክብር ጋር ተያያዥ ነውሮች የመከባበር እሴትን ለማስጠበቅና ለማስቀጠል ማህበራዊ ደረጃን ቅደመ ተከተላዊ ስርአቱን ለማስጠበቅ ነው፡፡ በሌላ ወገን ላይ ከሚደርሱ ነገሮች ጋር የሚገለጹ ነውሮች ደግሞ እርስ በርስ የመረዳዳትና የመተሳሰብ እሴትን ለማስጠበቅ በስነ ምግባር የታነጹ ለወገን ደራሽ ትውልድ ለማፍራት ነው፡፡ ከዝምድና ጋር ተያያዥ ነውሮች በቤተ ዘመድ መሀል ያለውን የደም ትስስር እንዳይፈርስ፣ የሚወደደውን ለማቅረብ  የሚጠላውን ለማራቅ ሲሉ ነውሮችን ይፈጥራሉ፡፡ ትዳርን ከመሰረቱ  በታማኝነት በመቻቻል የተሞላ እንዲሆን፣ ለሴቶች ደግሞ ጾታን መሰረት ያደረጉ ክልከላዎችን ከሀይማኖታዊ ስርአት ጋር በማያያዝ እና ከንጽህና ጋር በተያያዘ ርኩሰትን ስለሚያመጡ፣ ከእምነት ጋር የሚያያዙ ነውሮች ደግሞ ማህበረሰቡ ከሰው ልጆች ውጭ ያሉ መብረቅ፣  እባብና ነብርን እንደመልዕክተኛ ይቆጥሯቸው ነበር፡፡ ከእነዚህ መካከል አንደኛቸው ቢከሰቱ በቤተሰቡ ላይ መቅሰፍትን ሞትን ስለሚያመጡ የሚሉ ምክንያቶችን መነሻ እንደሚያደርጉ በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡ በማህበረሰቡ ዘንድ ያሉ ደንቦችና ሕጎች እንዲጠበቁ የተለያዩ ማህበራዊ ሽልማቶች እና ቅጣቶች አሉ፡፡ እነዚህ የማሕበረሰቡን ደንብ የጠበቀ የሚከበርበት አለቃ እስከመሆን እንደሚያደርስ ከደንቡ ያፈነገጠ ደግሞ እንደየጥፋቱ አይነት እንደሚቀጠና ካልታረመ ከአካባቢው እስከ መገለል እንደሚያደርስ ታውቋል፡፡ ማህበረሰቡ ነውሮችን የሚፈጥረው ለአኗኗሩ መመሪያ እንዲሆነው፣ የልጆችን ስብዕና ለመቅረጽ፣ ላመነባቸውና ለሚገለገልበት  ነገሮች የአጠቃቀም ስርአት ለማበጀት፣ በስነ ምግባር የታነፀ ትውልድ ለመፍጠር በአጠቃላይ ፍላጎቶቹን ለማሟላት፣ የሚወደድ የሚጠላውን ለይቶ ለማሳየት ነው፡፡ በመሆኑም ነውሮች የማህበረሰቡን ባህል እምነት፣ ታሪክ አስተሳሰብና አመለካከት ዕውቀቱን የሚያሳውቁ ናቸው፡፡ ስለሆነም የነውሮች የመተላለፊያ መንገድ ቃላዊ ስለሆነ የመረሳትና የመጥፋት እድላቸው የሰፋ ነው፡፡ እነዚህና ሌሎች በጥናቱ ያልተካተቱ ነውሮችን በመሰብሰብና በመሰነድ ለተተኪው ትውልድ ቢተላለፍ፣ መልካም ጎን ያላቸውን ነውሮች ቢያስቀጥሉና አሁን ካለው የአኗኗር ሁኔታ ጋር የማይጣጣሙ ወይም አሉታዊ ጎን ያላቸውን ነውሮች በሂደት ማሻሻያ ቢደረግባቸው የሚሉ የይሁንታ ሀሳቦችን በመጥቀስ ጥናቱ ተጠናቋል፡፡*

# ምዕራፍ አንድ
# መግቢያ

ባህል ለሰው ልጆች ከተፈጥሮ ጋር ተስማምቶ ለመኖር፣ ተፈጥሮን ለመግዛትና ያለበትን ህብረተሰብ ለመምራት መንገድና መሳሪያ በመሆን ያገለግለዋል፡፡ “የሰው ልጅ በባህሪው ከመሰሎች፣ ከተፈጥሮና ከማያውቀው ዓለም ጋር ተስማምቶ መኖርን የሚሻና ለዚህም ባህልን በመሳሪያነት የሚጠቀም ፍጡር ነው፡፡ በመሆኑም፣ ፍላጎቱን የሚሉልኛል፣ ከመሰሎቹ ጋር በሰላም ለመኖር ዋስትና ይሆኑኛል፣ ሌሎችን ለመቆጣጠር ያስችሉኛል የሚላቸውን የተለያዩ ባህሎችን ይፈጥራል፡፡” ሞላ (2009፣ሰ)

የሰው ልጅ ከፈጠራቸው ባህሎች መካከል ልማዳዊ ህጎች ይገኙበታል፡፡ እነዚህ ህጎች በፅሁፍ ያላሰፈራቸው፣ በልቦናው ይዞ ያቆያቸውና ከጊዜ ወደ ጊዜ ከትውልድ ወደ ትውልድ ያስተላለፋቸው መተዳደሪያው ናቸው፡፡ ከልማዳዊ ህጎች መካከል ነውሮች ይጠቀሳሉ፡፡ ነውር ደግሞ፣ የአንድ ማህረሰብ ፍልስፍናው፣ እምነቱ፣ እውቀቱና ልምዱ አስተሳሰቡ የሚገለፅበት ነው፡፡ አባላቱን ከማህበረሰቡ ህግና ደንብ እንዳይወጡ መንገድ የሚጠቁም፣ እንዳያፈነግጡ የሚቆጣጠሩና ባህርይን የሚቀርፁ ናቸው፡፡ በመሆኑም፣ የአንድን ማህበረሰብ ነውሮች በማጥናት አስተሳሰብና አመለካከቱን ብሎም ህዝቡን ማወቅ እንደሆነም ይገልፃል፡፡ ይህ ጥናት በዶርዜ  ማህበረሰብ ዘንድ ያሉ ነውር ተብለው በሚከለከሉ ነገሮች ላይ ትኩረት ያደረገ ነው፡፡

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

የሰው ልጆች ከተፈጥሮ ጋር ተስማምቶ ለመኖር ተፈጥሮን በአግባቡ ለመጠቀም፣ የሚኖርበትን ህብረተሰብ ለመምራት የራሱንም መንገድ ለመተለም ባህልን ዋነኛ መሳሪያ ያደርጋሉ። ሰዎች ከፈጠሩት ባህል መካከል አንዱ ሃገረሰባዊ ልማድ ነው። (ዶርሰን፣1972፡3) ሀገረሰባዊ ልማድ ማህበረሰቡ በተደጋጋሚ ለሚከውነው ድርጊትና ሥርዓት አስይዞ ቅደም ተከተላዊ በሆነ አኳኋን ለሚያከናውነው ጥበብ ጥቅል መጠሪያ ነው። ማህበረሰቡ ዘወትር የሚተገብረው የእለት ተለት እንቅስቃሴውን የሚመለከት ሆኖም በተደጋጋሚ የሚያደርገው ባህልን መሰረት ያደረገ ልምዱን የሚያጠቃልል ነው። እነዚህንም ከሀገረሰባዊ እምነት፣ ከሀገረሰባዊ ክብረ በዓላት እና ከተለያዩ ማህበራዊና ባህላዊ አጋጣሚዎች ጋር በማያያዝ የሚያከብሩት የሚከውኑት እንደሆነ ያስረዳል።

(cristina፣ 2016;12) ሰዎች የተለያየ ፍላጎት አላቸው በጋራ የሚያስፈልጋቸውን ፍላጎት ለማሟላት አንድነት ይፈጥራሉ። ይህ አንድነታቸው የጋራ ጉዳያቸውን ለማከናወን ማህበራዊ ህይወታቸውን ለማጠናከር ልዩ አጋጣሚ ይሆናቸዋል። በዚህ አጋጣሚ የሚያደርጉት የድርጊቶች ድግግሞሽ ልማድ እየሆነ ይመጣል።

ማህበረሰቡ ለህይወቱ ይጎዱኛል የሚላቸውን የሚያርቅበት፣ ይጠቅሙኛል የሚላቸውን ደግሞ የሚያቀርብበት በኑሮው ውስጥ ዘወትር የሚተገብራቸው ልማዶች አሉት። በእነዚህ ልማዶች ላይ የራሱን ማብራሪያ የሚሰጥበትና ለራሱ ህግና ደንብ፣ ስርዓትና መመሪያ በማበጀት የሚመራባቸው ናቸው። ሆኖም በማህበረሰቡ ባህል፣ ታሪክ፣ መልክአ ምድራዊ አቀማመጥ፣ ፆታ፣ እድሜ፣ ማህበራዊ ደረጃ፣ በአስተዳደራዊ ስርዓት ወዘተ... ላይ የተመሰረቱ በመሆናቸው እነዚህ ደንቦች እንደ ማህበረሰቡ አኗኗር እና አካባቢያዊ ሁኔታ የተለያዩ ናቸው።

የማህበረሰቡ አባላት ከህጉና ከደንቡ እንዳይወጡ እና ያልተገባ ባህሪ እንዳያሳዩ (እንዳያፈነግጡ) የሚቆጣጠርበት የራሱ የሆነ ስርዓት አለው። ማህበራዊ ልማዶች በማህበራዊ ቅጣቶች አማካይነት የሚጸኑ (social norms are enforced through social sanctions) ፣ በማህበረሰቡ ውስጥ ዘልቀው የሚገቡ፣ አፈንጋጭ ባህሪ ሲኖር የሚቀጡ፣ መልካም የሰራውን የሚያበረታቱ፣ በመልካምነቱ ዝነኛ የሚሆንበት፣ ልማዱን (ህጉን) የጣሰ ሲኖር አግባብነት ያላቸው ቅጣቶች አስከፊ ወይም አስደሳች ገደብ የሚጥሉ ናቸው (Cass (2013:15)።

በመሆኑም፣ ማህበራዊ ልማዶች ከፖለቲካ አሰራር የተለዩ/የራቁ የወል ህጎች ሲሆኑ እነሱም ስርዓትን የሚያጠናክሩ፣ በየአባሉ ህሊና ውስጥ በማንኛውም ሁኔታ የሚኖሩ፣ ልማዱን

ለተገበረ/ለጠበቀ ማስከበሪያ የሚሆኑ፣ ሽልማት የሚያስጡ፣ የሚስከብሩና፣ ጎልተው የሚታወቁ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ነገሮች ናቸው። በተቃራኒው ደግሞ ከልማዱና ከህጉ ያፈነገጠን የሚቀጡበት፣ ስነ-ስርዓት የሚያስይዙበት፣ መንገድ የሚመሩበት መቆጣጠሪያቸው መሆኑን የሚገልፅ ነው።

Engert (2016፤341) ልማዶች የጋራ እውቀቶችን የሚፈጥሩ ሚዛናዊ ዘዴዎች (equilibrium stratégies that have been made common knowledge.) ናቸው ይላሉ። ልማዶች ሚዛናዊ የሀብት ክፍፍልና ፍትሃዊ ስርዓት የሚያሰፍኑ፣ በማህበረሰቡ የእለት ተእለት ኑሮ ውስጥ ዘወትር የሚከወኑ ስርዓቶች መሆናቸውን ይጠቅሳሉ። ጠቃሚ እሴቶችን ለማስከበር፤ የሚወደድ የሚጠላውን ጠብቆ ለማቆየት የሚጠቀሙባቸው ስልቶች ናቸው።

ሞላ 2009፣2; Sorcar, 2009፡2-3 "በልማዶች ውስጥ የሚካተቱ ልማዳዊ ህጎች (Customary laws) ፣ በተፃፈ ድንጋጌ መልክ ሳይሆን በነባር ልማድ አማካይነት ተላልፈው የመጡና አንድ የማህበረሰብ ክፍል እንዲከወኑ ወይም እንዳይከናወኑ የተስማማባቸውን ባህሪያት፣ እሴቶች፣ እምነቶች፣ አመለካከቶችና ስሜቶች ወዘተ. የያዙ ናቸው"

ስለሆነም፣ ልማዳዊ ህጎች አንድ ማህበረሰብ ወደፊት እንዲሆኑለት ከሚፈልጋቸው ወይም እንዲያጋጥሙት ከማይፈልጋቸው ውጤቶች በመነሳት የሚፈጥራቸው የመተዳደሪያ መመሪያዎች ናቸው። እነዚህ ህጎች በፅሁፍ ያልሰፈሩ በልቦናቸው ይዘው ያቆዩአቸው፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተገበሩት የሚኖሩት መተዳደሪያ ደንቦች ናቸው።

ማህበራዊ ልማዶችን Erkki (1972፡ 27) ፎክዌይ፣ ሞርስ እና ሕግ በማለት በሶስት ይከፍላቸዋል። ጥናቱ ከልማዳዊ ህጎች (Customary laws) ጋር ተያያዥ በሆነው በሞርስ ላይ ትኩረት ያደረገ እና በዋነኝነት ነውሮችን በስፋት ይዳስሳል። ሞርስ በቡድኖች ውስጥ ያለውን ማንኛውንም ልማድ የሚመለከት ሲሆን እነዚህንም ልማዶች አባላቱ ከማህበረሰቡ የሚማሩት ነው። ይህንንም በተደጋጋሚ እየከወነው የሚቆይና ልማዶቹም በአባላቶቹ እየቀጠሉ የሚሄዱ መሆኑን የሚገልፅ ነው። የግድ መሆን/መደረግ ያለበት ባህሪ ሞርስ እንደሚባል ይገልፃል።

Erkki (1972፡ 27) ሞርስ እጅግ ጥብቅ የሆኑ ደንቦች (more serious norms) ሲሆኑ ነገር ግን ልክ እንደ ሌሎች ፎክሎሮች መደበኛ ያልሆኑ (informal like folkways) እና ያልተፃፉ ልማዶች ሆነው አይነተኛ የህይወት መንገዶች ናቸው። በመሆኑም፣ በሰነድ ያልተሰነዱ ነገር ግን በህገልቦና ያሉ በልማድ እየተገበሩትና እየከወኑት የሚገኙ ደንቦች ናቸው። እነዚህ

ልማዶችና ደንቦች ከሌሎች ልማዶች በተለየ ጥብቅ ሲሆኑ የማህበረሰቡን እሴት የሚያስጠብቁ መመሪያዎች፣ ማህበራዊ ህግ ማስጠበቂያ፣ ስርዓት ማስያዣ ናቸው።

ከላይ ከተጠቀሱት ሀሳቦች በመነሳት ይህ ጥናት በዋነኝነት ከማህበራዊ ደንቦችና ህጎች መካከል አንዱ በሆነው በነውር (tabbo) ላይ ያጠነጠነ ነው። ይህ ቃል ከእንግሊዘኛው መዝገበ ቃላት yohannes ejigu (2015) ላይ "የተከለከለ ነገር" የሚል ፍቺ ይይዛል። Frued (2004፣21) " the meaning of 'taboo', as we see it, diverges in two contrary directions." ነውር (tabbo) የሚለው ቃል በተለያዩ በሁለት ተቃራኒ አቅጣጫ ማየት እንችላለን። አንደኛው የተቀደሰ (sacred)፣ አንደቅዱስ የሚታሰብ/የተሰጠ ('consecrated') ማለት ሲሆን በሌላ በኩል በጣም ረቂቅ ('uncanny')፣ አደገኛ/የሚፈራ ('dangerous')፣ ክልክል (forbidden')፣ ርኩስ ('unclean') ወ.ዘ.ተ... በማለት ይተረጉመዋል።

ነውር የሚከበር እንደቅዱስ የሚታይ በሌላ መንገድ ደግሞ የሚፈራ የተከለከለ ነገር መሆኑን የሚጠቅስ ነው። በዚህ የተገለፀው ሀሳብ ነውር በማህበረሰቡ ውስጥ ያለ ልቦናዊ ህግ (አፅንኦት የኔ) ሲሆን ይህንንም የሚፈሩትና የሚያከብሩት እንደሆነ ነው። በመሆኑም በህይወቱ ላይ ተፅዕኖ ያሳድሩብኛል፤ ይጎዱኛል ብሎ ለሚያስባቸው/ለሚፈራቸው ነገሮች፣ ስጋት ውስጥ ከሚከቱት ነገሮች ለመከላከል ሲል የራሱን ህግ ያወጣል። በዚህም የሚወዳቸውን ነገሮች ለማቅረብ የሚጠላቸውን ነገሮች ደግሞ ለማራቅ ይጠቀምበታል። ይህም አባላቱ እንዳያደርጓቸው ወይም የሚመራበትን ማህበራዊ ሕግና ደንብ እንዳይጥሱ "ነውር ነው" እያለ የሚያስተምርበት ዘዴ ነው። ነውር አንድን ማህበረሰብ አንድነቱን የሚያጠናክርበት፣ ህይወቱን ለመምራት ህግ የሚያወጣበት መንገዱ ነው።

የዶርዜ ማህበረሰብ በተለየ መልኩ ብዙ ጊዜ ወግ ያጠብቃሉ ይባላል። ለዚህም ደግሞ ነውር የሚሏቸው ነገሮች ዋነኛ ተጠቃሽ ሲሆኑ ባሉበት ቦታ ሆነው ባህላቸውን የሚጠብቁ ናቸው። ለምሳሌ ነውር ነው እያሉ የሚጠቅሷቸው ነገሮች በተለያዩ አጋጣሚዎች ሲገለፁ፣ የለቅሶ ስርአታቸውን ማህበራዊ ደንቡን በጠበቀ መልኩ ሙሾ እየገጠሙ ከለቅሶ ጭፈራ ጋር በከተሞች አካባቢ ሲያከናውኑ ይስተዋላል። በመሆኑም ከሌላው ህብረተሰብ እንዲለዩ ያደረጋቸውን፣ ነውር የተባሉ ነገሮችን በማየት በምን መልኩ ደንቦቻቸውንና ህጎቻቸውን እንደሚያስጠብቁ ማጥናት አስፈላጊ ሆኗል። ይህ ጥናት የዶርዜ ማህበረሰብ ማህበራዊ ደንቦቹንና ህጎቹን በምን መልኩ እንደሚያስጠብቁ የቀረበ ጥናት ነው።

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ይህ ጥናት "ነውር እንደ ማህበራዊ ደንብ ማስጠበቂያ ስልትነት በዶርዜ ማህበረሰብ" የሚል ጉዳይ ይዞ የተጠና ነው፡፡ በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ለማጥናት ሰበበ ምክንያቶች ሁለት ናቸው፡፡

አንደኛው ግላዊ ምክንያት ሲሆን ይኸውም ገጠመኝ ነው፡፡ የመስቀል በዓልን ለማክበር ወደ አካባቢው በሄድኩበት ጊዜ የተመለከትኳቸው አንዳንድ ነገሮች ነበሩ፡፡ ይህ በዓል በዚህ ማህበረሰብ ዘንድ ትልቅ ቦታ የሚሰጠውና ከሌሎች በዓላት ይልቅ ደምቆና በሰፊው የሚከበር ነው፡፡ የአከባበር ስርዓቱም በክወናው ላይ ማህበራዊ ደረጃን የሚለይ ሲሆን፣ በተለይ የደመራ (የችቦ ማብራት) ስነ-ስርአቱ ላይ ወንዶች ብቻ የሚሳተፉበት በአል ነው፡፡

መጀመሪያ የሀገር ሽማግሌዎች(አለቆች) ችቦውን ከየቤታቸው ለኩሰው ሲያወጡ ሌሎች አባቶች የተለኮሰ ችቧቸውን ይዘው በቅደም ተከተል ወደ ተዘጋጀው የደመራ ቦታ ያመራሉ፤ ከተያያዘ በኋላ ለልጆቻቸው/ለወጣቶች ያስረክባሉ፡፡ በዚህ መሀል ግን አባት በህይወት እያለ ልጅ ቀድሞ ችቦ አይለኩስም፤ ነውር ነው፡፡ በስራ ምክንያት ቢርቅ እንኳን ከቤታቸው ችቦ አይወጣም፤ በህይወት ከሌለ ግን የቤቱ ታላቅ ወንድ ልጅ (ታላቅ ሴት ከሆነች ተከታዩ ወንድ) መለኮስ ይችላል፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ የገጠመኝ ነገር ከአንድ ዓመት በፊት (2010 ዓ.ም) አዲስ አበባ ለመስቀል በዓል አንድ ጎረቤታችን አባቱ በስራ ምክንያት የደመራ እለት ቤታቸው አልነበሩም ፡፡ ሆኖም ወንዱ ልጃቸው ለደመራ እለት ችቦ ለኩሶ ያወጣና ደመራውን አከበሩ፤ በማግስቱ አባትየው ከስራ ሲመለሱ ልጃቸው ችቦ ማውጣቱን ይሰሙና ቤት ውስጥ ፀብ ተፈጠረ፡፡ "እንዴት እኔ በህይወት እያለሁ ችቦ ያበራል፤ነውር ነው" አሉ፡፡ ለምን ሲባል "የአባቱን እድሜ ያሳጥራል፤ የቤቱን ስልጣን አባቱ ሳይሞት ልጁ ተረከበ ማለት ነው" ብለው ተናገሩ፡፡ በልጃቸው ድርጊት ክፉኛ ስላዘኑ አብረው በአንድ ማዕድ አልመገብም አሉ፡፡ ተቀያይመው ስለነበረ ልጁም ስራ ሳያገኝ ቆየ፡፡ በዚህ ጊዜ "እኔ አዝኜበት ነው ይቅር እንባባል" ብለው ሽማግሌ ተሰብስቦ ልጁም ይቅርታ ጠይቆ ምህረት አደረጉለት፤ ክፉ እንዳይገጥመው መረቁት፡፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ልጁ ስራ እንዳገኘ ሰማሁ፡፡

ሌላኛው ገጠመኝ፡- በአንድ ወቅት በ2008 አካባቢ የአባቴ እህት ልትጠይቀን መጥታ ድሮ ከአባቴ ጋር በልጅነታቸው ስላደረጉት ነገር አጫውታን ነበር፡፡ በዛ አገር ደንብ ለአቅመ አዳምና ለአቅመ ሄዋን ያልደረሰ ልጅ የበቆሎ እሸት መቁረጥ አይችልም ነውር ነው፡፡ እናም እናትና

አባታቸው ወደ ጎረቤት ለቡና ሲሄዱ አባቴና ታናሽ እህቱ ተደብቀው ወደ በቆሎው ማሳ ይሄዱና እሷ እንድትቆርጥ እሱ ደግሞ ሰው ከመጣ ሊነግራት ተስማሙና ወደማሳው ገቡ፡፡ ከዚያም በቆሎውን ገና ስትቆርጥ እባብ ከየት መጣ ሳይባል በላይዋ ላይ ተጠመጠመባት፡፡ ሁለቱም ተደናግጠው ሲጮሁ አባታቸው መጣ፤ ልጅቱ እንዳትንቀሳቀስ ሙሉ ሰውነቷን ይዟታል፡፡

አባትየው ከመሬት አፈር አነሱና በሁለት እጃቸው ይዘው "ልጆቹ ምንም አያውቁም እኔ ነኝ ጥፋተኛ እሷን ልቀቃት ሳታውቅ ነው ያጠፋችው" አሉት፡፡ እሳቸው የሀገር ሽማግሌ(አለቃ) ስለነበሩ አይነካቸውም አሉ፡፡ በእጃቸው ላይ ያለውን አፈር "በዚህ ይለፍ" ብለው "እፍፍ" ሲሉበት እባቡ ከሷ ላይ ተነስቶ አፈሩን ላስ አድርጎ ወደ መሬት ገባ፡፡ በኂላም ልጆቹን ገስፀው/ተቆጥተው ወደቤታቸው ተመለሱ፡፡ ስለእባቡ ስጠይቃት በድሮ ጊዜ ድንበር ይጠብቃል፣ ማሳውን ጠላት እንዳይነካው፣ ያለተፈቀደለት ሰው እዳይነካ ይጠብቃል ይባላል፡፡ ለዛ ነው እኛ ላይ የመጣብን አለችኝ፡፡ በአሁን ጊዜ ግን ከእባብ ጋር የተያያዘ ነገር እንደቀረ አጫውታኛለች፡፡

በዚህም የተነሳ የማህበረሰቡን ባህልና ወግ ጠንቅቄ ባለማወቄ ለምን የሚል ጥያቄ አጫረብኝ፡፡ "ነውር" የሚባሉ ነገሮች ምንድን ናቸው? ቢደረጉ የሚያስከትሉት ነገር ምንድነው? በማክበራቸው የሚያስገኙት ጠቀሜታ ምን እንደሆነ ለማወቅና በጥናት ለሌላው ህብረተሰብ ባህልና ወጉን ስርአቱን ለማስተዋወቅ ጉጉት አደረብኝ፡፡

ሁለተኛው፡- በንባብ ካገኘሁት ልምድ ነው፡፡ ይህም ለተለያዩ ኮርሶች ማሟያነት የተለያዩ አጫጭር ጥናቶችን ስንሰራ መፅሀፎችን፣ መጣጥፎችንና ጥናቶችን በማነብበት ወቅት ከነውር ጋር የተያያዙ ጥናቶችን ጥቂት ካልሆነ በስተቀር በስፋት አላገኘሁም፡፡ እንዲሁም በማህበረሰቡ ዙሪያ የተሰሩ ጥናቶች ስዳስስ በነውር ላይ የተሰራ ጥናት ባለማግኘቴ በርዕስ ጉዳዩ ዙሪያ ለማጥናት ተነሳሳሁ፡፡

## 1.3 የጥናቱ አላማ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ የዶርዜን ማህበረሰብ በነውር ዙሪያ ያለውን እውቀት፣ አስተሳሰብና አመለካከት፣መመርመር ሲሆን ሌሎችም ንዑሳን አላማዎች አሉት፡፡

- ነውር ያረፈባቸውን ነገሮች መለየት እና ነውር የተባሉበት ምክንያት መፈተሽ፣
- የማህበረሰቡን የስነምግባር ማስተማሪያ ዘዴዎቻቸውን ማሳየት፣
- ከጥፋት መመለሻ እሴቶች፣ ቅጣቶችና ማስፈፀሚ ዘዴዎችን መመርመር፣

- ነውሩን ጠብቀው የሚኖሩ የማህበረሰብ ክፍሎች የሚያገኙትን ጥቅም ወይም ነውር ለማህበረሰቡ ያለውን ፋይዳ ማሳየት ናቸው፡፡

## 1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ

በዚህ ጥናት ይገኛል ተብሎ የታሰበው ዋነኛ ጠቀሜታ የዶርዜ ማህበረሰብ ስለነውር ያለውን የህይወት ፍልስፍና እና አስተሳሰብ በማጥናት ማህበረሰቡን ማስተዋወቅ ሲሆን ሌሎችም ጠቀሜታዎች አሉት፡፡

- በማህበረሰቡ ነውሮች አማካኝነት የማህበረሰቡን ህግና ደንቦች፣ ልማዶች፣ እሴቶች ለሌላው ህብረተሰብ የሚያስተዋውቅ ይሆናል፡፡
- ነውር የተባሉ ጉዳዮችንና ምክንያቶቻቸውን ይገልጻል፡፡
- ደንብና ሕጉን ለማያውቁ የማህበረሰቡ ተወላጆች ለማስተማርና በነውሮች አማካኝነት የሚገለፁ ጠቃሚ እሴቶችን ለማስቀጠል፣
- ነውሮች በአሁን ጊዜ የመከበር አቅማቸው እየቀነሰ ስለመጣ ጨርሰው እንዳይጠፉ የማህበረሰቡን ባህልና እሴት በመሰነድ ከትውልድ ወደ ትውልድ ለማስተላለፍ ይረዳል፡፡
- በዞኑ እና ብሎም በክልሉ ለሚቀረፁ ፖሊሲዎች ከህግ ፣ ከፍትህ፣ ሚዛናዊ ክፍፍልና እኩል ተጠቃሚነትን በተመለከተ መነሻ ሃሳብ በመሆን ያገለግላል፤ ተብሎ ይታሰባል፡፡
- ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር በተያያዘ እና በተጠኝው ማህበረሰብ ዙሪያ ጥናት ለሚያካሂዱ አጥኚዎች እንደግብአት ያገለግላል ተብሎ ይታሰባል፡፡

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት ከቦታ አንፃር በዶርዜ ማህበረሰብ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ የዶርዜ ወረዳ በ11 ቀበሌዎች የተከፋፈለ ሲሆን ከዶርዜ ማህበረሰብ ውጪ ሌሎች አጎራባች ማህበረሰቦችን አያካትትም፡፡ በስሩ ባሉት 11 ቀበሌዎች መካከል የጥናቱ አካባይ የሚሆነው በርካታ የህዝብ ቁጥር አላቸው የሚባሉትን ቀበሌዎች ዶርዜ ሀይዞ፣ ዶርዜ ሒርጶ፣ ዶርዜ አማራ፣ ዶርዜ ሆሎኦ፣ ዶርዜ አይራ እና ዶርዜ ቦዶ ከተማ ናቸው፡፡

ከርዕሰ ጉዳይ አንፃር ይህ ጥናት የዶርዜ ማህበረሰብ ካሉት ባህሎች መካከል ማህበራዊ ደንቦችና ህጎች (ነውሮች) ላይ ትኩረት ያደረገ ነው፡፡

## 1.6 ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ ሀሳቦች

ይህ ጥናት ለማጥናት መረጃዎችን በምሰበስብበት ወቅት የተለያዩ ነገሮች አጋጥመው ነበር፡፡ ከዚህ በፊት ወደ ዶርዜ አካባቢ የመስቀል በአል ለማክበር በተለያየ ጊዜ እሄድ ስለነበር አካባቢውን ለማወቅ አልተቸገርኩም፡፡ በፊት የማውቃቸውን የአባቴን ጓደኞች አቶ አስፋው ሶሬ እና አቶ ጋሞ ጋጎ የተባሉትን ሰዎች አገኘኋቸው፡፡ በእነሱ አማካኝነት በየቀበሌዎች የሚገኙትን የሀገር ሽማግሌዎች ስለባህሉና ደንቡ በደንብ ያውቃሉ የሚባሉትን በጥቆማ እያጠያየቁ ይወስዱኝ ነበር፡፡ በዚህም የተለያዩ መረጃዎችን በቃለመጠይቅ ለመሰብሰብ ችያለሁ፡፡

ያጋጠመኝ ችግር ለመረጃ ስብሰባ በሄድኩበት ወቅት በአካባቢው ከማንነት ጋር በተያያዘ ረብሻ ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት እኔ ለሄድኩበት ጉዳይ ብቻ ለመሰባሰብ ፈቃደኛ አልነበሩም፡፡ ስለዚህ እድር የሚጣልበትን ጊዜና ለሽምግልና የሚሰባሰቡበትን ቀን በመጠበቅ መጠየቅ እንደምችል ነገሩኝ፡፡ ያሉትን ጊዜያት በመጠቀም የተጣሉ ሰዎችን ሲያስታርቁ በመገኘት በሌላ ጊዜ ደግሞ ለእደር ሲሰባሰቡ የሄድኩበትን ጉዳይ በማስረዳት የተወሰኑ መረጃዎችን በቡድን ውይይት ሰብስቢያለሁ፡፡

## 1.7 የጥናቱ አደረጃጀት

ይህ ጥናት በስድስት ምዕራፎች የተዋቀረ ሲሆን የመጀመሪያው ምዕራፍ የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱ አላማ፣ የጥናቱ ጠቀሜታ የጥናቱ ወሰን እና ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ ሀሳቦች የቀረቡበት ነው፡፡ ምዕራፍ ሁለት የክለሳ ድርሳን ክፍል ነው፡፡ በስሩ የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ሲሆን የሀገር ውስጥ ጥናቶችና የውጭ ሀገር ጥናቶች የተቃኙበት ሲሆን በፅንሰ ሀሳባዊ ዳራ ማህበራዊ ልማዶች፣ ልማዳዊ ህጎች፣ የነውር ምንነት፣ የነውሮች መፈጠር ምክንያትና ፋይዳ፣ የነውር አይነቶች፣ የነውር ለውጥና ተከታታይነት እና ማህበራዊ ቅጣቶችና ሽልማቶች ተካተውበታል፡፡ እንዲሁም በንድፈ ሀሳባዊ ዳራ ፍካሬ ልቦና ንድፈ ሀሳብና ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ የታየበት ክፍል ነው፡፡

በምዕራፍ ሶስት የጥናቱ ዘዴ ሲሆን የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ቃለመጠይቅ፣ ምልከታ፣ቡድን ውይይት እና መዛግብት ፍተሻ ናቸው፡፡ ቀጥሎ የናሙና ዘዴና የመረጃ መተንተኛ ዘዴ

የተገለፀበት ነው፡፡ በምእራፍ አራት የጥናቱ አካባቢያዊ ዳራ አካባቢውን የሚያስተዋውቁ ነገሮች የመልክዓምድር አቀማመጥና የአየር ሁኔታ፣ የአለቃ ሹመትና ሽረት ስርአት፣ የአለቃ ዋና አገልግሎት እና የጋብቻ ስርአት የተካተቱበት ነው፡፡

በምእራፍ አምስት የመረጃ ትንተና ክፍል ነው፡፡ በውስጡ የዶርዜ ማህበረሰብ የነውር አይነቶችና ምክንያቶቻቸው፣ የዶርዜ ማህበረሰብ ማህበራዊ ቅጣቶችና ሽልማቶች፣ የነውሮች ፋይዳ፣ የነውር አይነቶች ላይ የታዩ ለውጥና ተከታታይነት የታየበት ክፍል ነው፡፡

ምዕራፍ ስድስት ደግሞ ማጠቃለያና የይሁንታ ሀሳብ የሰፈረበት ሲሆን በማጠቃለያው ክፍል የጥናቱ ግኝቶች ተጠቅሰዋል፡፡

## 1.8 የመስክ ተሞክሮ

ይህ ጥናት በሚጠናበት ወቅት መረጃ ለመሰብሰብ ወደ ተጠኚው ማህበረሰብ ለጉዞ ተነሳሁ፡፡ መጋቢት 2 2011 አ.ም ከመኖሪያዬ ከአዲስ አበባ ወደ አርባ ምንጭ 505 ኪ.ሜ ተጓዝኩ፡፡ በዚያ ለሁለት ቀን ቆይቼ ከጋሞ ዞን አስተዳደር ፅ/ቤት የተለያዩ አካባቢያዊና ስታስቲካዊ መረጃዎችን ሰበሰብኩ፡፡ መጋቢት 5 ከአርባ ምንጭ ጨንቻ 40 ኪ.ሜ ተጉዤ 7 ኪሜ ያህል ሲቀረኝ ዶርዜ የሚባል አካባቢ ወረድኩ፡፡ የአባቴ ቤት በአካባቢው ስለነበረ በዚያ አረፍኩ፡፡ በመጀመሪያ ለሶስት ሳምንት ቀጥሎ ከሚያዝያ 2 እስከ 11 ድረስ ቆይታ አድርጊያለው፡፡

በቆየሁበት ጊዜ ከዚህ በፊት የማውቃቸው የአባቴ ጓደኞች አቶ አስፋው ሶሬ እና አቶ ጋሞ ጋጎ በየቀበሌው አብረው እየተዘዋወሩ ከመረጃ አቀባዮች ጋር ያገናኙኝ ነበር፡፡ መረጃዎቹን ለመሰብሰብ ማስታወሻ ደብተርና ፎቶ ለማንሳትና ድምፅ ለመቅረፅ ደግሞ የእጅ ስልኬን ተጠቅሜአለሁ፡፡

በመጀመሪያዎቹ ሁለት ሳምንታት ቃለመጠይቅና በሽምግልና ስርአት ላይ መጋቢት11 እና 18 ለእርቅ ሲሰባሰቡ በመገኘት ምልከታ አድርጊያለሁ፡፡ በመሀል ያሉትን ቀናቶች ሁለት ቡድን ውይይት አድርጊያለሁ፡፡ የሶስተኛውን ሳምንት ወደ ወረዳው በመሄድ የመዛግብት ፍተሻ አካሂጃለው፡፡ ቀጥሎ ሚያዝያ 2፣ 2011 ደግሞ ጥያቄ ያጫሩ ጉዳዮች ስለነበሩ መረጃዎችን ለማመሳከር እንደገና የማጣራት ስራ ገባሁ፡፡

በቃለመጠይቁ ነውር የሚባሉ ጉዳዮችና ምክንያቶቻቸውን፣ በምልከታው ከጥፋት መመለሻ እሴቶችና ማስፈፀሚያ ዘዴዎችን፣ በቡድን ውይይት ደግሞ ሁሉም ህብረተሰብ የማይስማማባቸው የነውር አይነቶች በመገኘታቸውና የነውሮችን ለውጥና ተከታታይነት በተመለከተ ሌሎችም ተያያዥ ጉዳዮችን በመጠየቅ አስፈላጊው መረጃ ተሰብስቧል፡፡ በመዛግብት ፍተሻ ደግሞ አካባቢያዊ ዳራውን እና አካባቢውን የሚመለከቱ ጥናቶች ተቃኝተውበታል፡፡ ከሚያዝያ11 በኋላ ቀሪውን ጊዜ አዲስ አበባ የሚገኙ የዶርዜ ተወላጆች መረጃ እንዲሰጡኝ በመጠየቅ እና ለሽምግልና በሚሰባሰቡበት ወቅት በመታደም መረጃዎችን አግኝቻለው፡፡

ቀጥሎ በድምፅ የተቀዱ መረጃዎችን ወደ ፅሁፍ በመቀየር፤ በጋሞኛ ቋንቋ የተገኙትን አብረውኝ ሲዘዋወሩ የነበሩ መረጃ ሰጪዎች/ሁለቱንም ጋሞኛና አማርኛ ቋንቋ አቀላጥፈው የሚናገሩ/ ስለነበሩ በነሱ አጋዥነት ተተርጉሟል፡፡ ሌሎች የተሰበሰቡ መረጃዎችን ለየብቻ በርእስ በማደራጀት የተነሳሁበትን አላማ መሰረት በማድረግ ተተንትነዋል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳን

ይህ ክፍል በሶስት ክፍሎች የተደራጀ ነው፡፡ የመጀመሪያው የጥናቱን ርዕሰ ጉዳይ በሚመለከት ከዚህ በፊት የተካሄዱ ከዚህ ጥናት ጋር ተዛማጅ ጽሁፍች የተዳሰሱበት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ግንኙነት ያላቸው ጽንሰ ሃሳቦች የተቃኙበት ነው፡፡ ሶስተኛው ደግሞ ጥናቱን የሚመሩ የመረጃ መተንተኛ የሆኑ ንድፈ ሃሳባዊ ማዕቀፎች የቀረቡበት ነው፡፡

## 2.1. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት/Related literature

በዚህ ክፍል ከነውሮች ጋር በተያያዘ ከዚህ በፊት የተጠኑ ጥናቶች የተቃኙበት ነው፡፡ እነሱም በሀገር ውስጥ ባሉ ነውሮች ላይ የተሰሩ ጥናቶች ሁለት የተገኙ ሲሆን በውጭ ሀገር ነውሮች ላይም ሁለት ጥናቶች በዚህ ርዕስ ስር ተካተዋል፡፡

### 2.1.1 የሀገር ውስጥ ጥናቶች

የመጀመሪያው ተጠቃሽ ጥናት ሞላ ጀምበሬ በ2007 ዓ. ም ያጠናው ነው፡፡ ጥናቱ፣ "የነውር እሳቤ በሊቦ ከምከም ወረዳ ማህበረሰብ እምነት" በሚል ርዕስ የተካሄደ ሲሆን፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂዩማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፍክሎር ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር ለፎክሎር የፒ. ኤች. ዲ. ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ነው፡፡

ጥናቱ በሊቦ ከምከም ወረዳ ማህበረሰብ አስተሳሰብ፣ እውቀትና እምነት ውስጥ ነውር የያዘውን ሰፊ ትርጉምና ገዥ ቦታ በመመርመር የማህበረሰቡን የህይወት ፍልስፍና መግለፅ ዋና አላማ በማድረግ የተካሄደ ነው፡፡ ጥናቱ አይነታዊ ገላጭ የአጠናን ዘዴን የተከተለ ሲሆን፤ የጥናቱ መረጃዎች የተሰበሰቡት በቤተ መዛግብት ዳሰሳ፣ በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅ እና በተተኳሪ የቡድን ውይይት አማካኝነት ነው፡፡ በጥናቱ የተሳተፉ ሰዎች የተመረጡት በአላማ ተኮር የናሙና ስልት ነው፡፡ ምግብ፣ ሞትና የግብርና ስራን የተመለከቱ ነውሮች እንዳሉ ጠቅሶ ማህበረሰቡ ነውር የሚላቸው የምግብ አይነቶች ለጤና ጠንቅ ስለሆኑ፤ ከሞት ጋር ለተያያዙ ድርጊቶች ወደ ሞት ስለሚያመሩ፤ ከስራ ጋር

ለተያያዙ ድርጊቶች በረከትን ስለሚያሳጡ የሚል መንስኤ እንደሚያደርጉ በጥናቱ ተረጋግጧል።

ማህበረሰቡ ነውሮችን የሚፈጥረው የአባላቱን ባህሪና አስተሳሰብ ለመግዛት፤ የልጆቹን ሰብዕና ለመቅረፅ፤ ስጋዊና መንፈሳዊ ፍላጎቶቹን ለማርካት፤ በአጠቃላይም ለአኗኗሩ መርህ፣ ለግንኙነቱ ደንብና ህግ ሆነው እንደሚያገለግሉት በማሰብ ነው። በመሆኑም ማህበረሰቡ ነውሮች ከጥቅም በስተቀር የጎንዮሽ ጉዳት ሊኖራቸው ይችላል የሚል እምነት የለውም። ይሁን እንጅ ነውሮቹ በጥልቀት ሲመረመሩ የየራሳቸው የሆነ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ሚና ያላቸው እንደሆኑ ጠቅሷል።

በአጠቃላይ ግን ነውሮች የማህበረሰቡን ጥንተ ማንነት፣ ባህል፣ ደንብ፣ አስተሳሰብ ወዘተ. የሚያሳዩና በአጠቃላይም የማህበረሰቡ የህይወት ፍልስፍና ምን እንደሚመስል ለመረዳት የሚያስችሉ ናቸው። ከዚህ በመነሳትም ነውሮችን ሁሉ ጎጅ አድርጎ ከመውሰድ ይልቅ አዎንታዊ ሚና ያላቸውን በመለየት እነሱን ማክበርና ማስፋፋት ተገቢ መሆኑን፤ አሉታዊ ሚና ያላቸውን ደግሞ በሂደት ሊቀሩ የሚችሉበትን ሁኔታ መፍጠር እንደሚያስፈልግ የሚጠቁሙ ይሁንታዎች በመሰንዘር ጥናቱ ተቋጭቷል።

የእኔ ጥናት ከሞላ ጥናት ጋር ተመሳሳይ ርዕሰ ጉዳይ ይዞ የተነሳ ነው። መረጃ መሰብሰቢያ እና መተንተኛ ዘዴው አይነታዊ ስልት የተከተለ ሲሆን ንሞና ዘዴው አላማ ተኮር የናሙና ዘዴ ነው። ከዚህ ጥናት ጋር በርዕሰ ጉዳይና አጠናን ስልት ተመሳሳይ ነው፤ ይሁን እንጂ ጥናቱ ትኩረት ያደረገባቸው አካባቢዎች የተለያዩ ናቸው። የሞላ ጥናት በሊቦ ከምከም ወረዳ ላይ የተሰራ ሲሆን የእኔ ጥናት ደግሞ በዶርዜ ማህበረሰብ ላይ የተሰራ ነው። እነዚህ አካባቢዎች በቦታም የተለያየ አቅጣጫ ላይ ያሉ፣ በቋንቋና ባህልም የተለያዩ ማህበረሰቦች ናቸው። በመሆኑም ነውሮች እንደ ማህበረሰቡ አኗኗርና ባህል መሰረት አድርገው የተፈጠሩ በመሆናቸው በጥናቶቻችን ላይ የተጠቀሱት ነውሮች ልዩነት አላቸው።

በሞላ ጥናት የተጠቀሱት ነውሮች ምግብ፣ ሞትን እና ስራን የተመለከቱ ጉዳዮች ሲሆኑ በእኔ ጥናት ውስጥ እንደዚህ አይነት ጉዳይ ያላቸው ነውሮች የሉም። ማለትም በጥናቴ የተገኙት የነውር አይነቶች ስድስት ሲሆኑ ክብርን ከማስጠበቅ አንፃር የሚገለፁ ፣ በሌላ ወገን ላይ ከሚደርሱ ነገሮች አንፃር፣ ዝምድናን ከመጠበቅ አንፃር፣ ትዳርን ከማስጠበቅ ጋር፣ ለሴቶች የሚከለከሉ ነገሮች፣ ከእምነት ጋር የሚገናኙ ነውሮች ናቸው። ለዚህም ልዩነቱ የመጣው

የተለያየ ባህልና ቋንቋ ባላቸው የማህበረሰብ ክፍሎች ላይ የተሰሩ በመሆናቸው ነው፡፡ ሌላው ልዩነታችን የርዕሰ ጉዳይ አተያያችን ሲሆን በሞላ ጥናት ውስጥ የነውር አይነቶችና ምክያቶቻቸው ተጠቅሰው የሊቦ ከምከም ማህበረሰብ እምነት በነውሮች ላይ ያላቸውን እሳቤ በስፋት የተቃኘበት ነው፡፡ በእኔ ጥናት ደግሞ የዶርዜ ማህበረሰብ ነውሮች የሚላቸው ነገሮች እና ምክንያቶቻቸው፣ በነውር መተላለፍ የሚደርሱ ቅጣቶች፣ ከጥፋት መመለሻ እሴቶች እንዲሁም ከነውሮች ጋር በተለያዩ በሰዎች ላይ በእንስሳት ላይ የደረሱ እውነተኛ ገጠመኞች ተካተውበታል፡፡

ስለሆነም፣ በሞላ ጥናት ውስጥ ነውር የተላለፈ የማህበረሰቡ አካል ምን እንደሚቀጣ እና ከነውር ጋር ተያያዥ የሆኑ ገጠመኞች ባለመጠቀሳቸው የእኔ ጥናት ይህንን ክፍተት ለመሙላት የተሰራ ነው፡፡ ስለዚህ፣ ከተነሳንበት ርዕሰ ጉዳይና አላማ አንፃር በቀጥታ የሚገናኙ ተመሳሳይ ጥናቶች ቢሆኑም ከተጠቀሱት የነውር አይነቶች እና ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች ልዩነት እንዳለን ማወቅ ይቻላል፡፡

ሁለተኛው ጥናት ደግሞ ዋልተንጉስ መኮነን (2007) "ተፈጥሮን መናቅ፣ ሥጋን ማክበር፤ ለክፈ አይን አጋላጭ ክስተት፤ በምስራቅ ጎጃም በሚገኘው የጎዛምን ማህበረሰብ እምነት" በሚል ርዕስ የሶስተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናታቸውን ሰርተዋል፡፡ የጥናታቸው ዋና አላማ ተጠኝው ማህበረሰብ በክፉ ዓይን እምነት ላይ ያ|ውን እሳቤና እምነቱ እንዲከሰት ያደረገውን ምክንያት መግለፅ ነው፡፡ አላማቸውን ከግብ ለማድረስም የተ|ያዩ ንድፈ ሃሳቦችንና የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዳዎችን በመጠቀም መረጃዎችን ሰብስበው ትንተናና ማብራሪያ አቅርበዋል፡፡ በጥናታቸው የትንተናና ማብራሪያ ክፍልም በተጠኝው ማህበረሰብ ውስጥ ለክፉ አይን የሚያጋልጡ የተለያዩ አውዶች እንዳሉ አንስተዋል፡፡ የክፉ አይን አጋላጭ አውዶች ያሏቸውን ሲያነሱም የዚህ ጥናት ርእሰ ጉዲይ ከሆኑት ነውሮች ጋር የተያያዙ የተወሰኑ ሃሳቦችንም አቅርበዋል፡፡

በጥናታቸው ግኝት መሰረት በተጠኝው ማህበረሰብ ውስጥ ለ ክፉ አይን ያጋልጣል ከሚባሉ በርካታ ጉዳዮች መካከል ነውሮችን መጣስ እንደ ምክንያት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ በዚሁ መነሻነትም ማህበረሰቡ ከክፈ አይን ጋር በተያያዘ የሚተገብራቸው ያሏቸውን የተወሰኑ "ነውሮች" በጥናታቸው ውስጥ አንስተዋል፡፡ ለምሳሌ በጨለማ ዋሽንት መንፋትም ሆነ ክራር መምታት፤ በክረምት ጋብቻ መፈፀም፤ ማዕድ ላይ ምንም ሳያስቀሩ ወይም

ሳያስተርፉ መብላት፤ የከብትንም ሆነ የበግን የመጀመሪያ ግልገል ገበያ አውጥቶ መሸጥ፤ በግራ እጅ ማንኛውንም ስራ ማከናወን፤ ወዘተ. በማህበረሰቡ እምነት ነውር እንደሆነ ጠቅሰዋል፡፡

ነውር የሆኑበት ምክንያትም የተጠቀሱት ነገሮች ለክፉ አይን አጋላጭ የሆኑ ክስተቶች ናቸው ተብሎ ስለሚታመን እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ በመጨረሻም ማህበረሰቡ የክፉ አይን ጥቃትን የሚከላከልባቸው በርካታ መንገዶች እንዳሉት ያነሱ ሲሆን፤ ከነሱም መካከል የማህበረሰቡን ነውሮች ማክበር አንዱ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

የዋልተንጉስ ጥናት ርዕሰ ጉዳዩ ይዞ የተነሳው ለክፉ አይን አጋላጭ ክስተቶችን የተመለከተ ጥናት ነው፡፡ በጥናቱም ለክፉ አይን ከሚያጋልጡ ነገሮች መካከል ነውሮችን መጣስ እንደሆነ ጠቅሰዋል፡፡ በቀጥታም ባይሆን በተዘዋዋሪ መንገድ ነውሮች የዳሰሱበት ሁኔታ ይስተዋላል፡፡ ስለሆነም ከኔ ጥናት ጋር በቀጥታ የሚገናኝ ባይሆንም በተወሰነ መልኩ ተቀራራቢነት ስላለው በዚህ ክፍል ተካቷል፡፡

ስለዚህ ከእኔ ጥናት ጋር በቀጥታ የሚገናኘው የሞላ ጀምበሬ ጥናት ነው፡፡ በዚህም በጥናቱ ውስጥ ባሉት የትኩረት ነጥቦችና የነውር አይነቶች ልዩነት ያላቸው ቢሆንም ከተነሳንበት ርዕሰ ጉዳይና አላማ አንፃር የሚቀራረቡ ናቸው፡፡

### 2.1.2 በውጭ ሀገራት ነውሮች ላይ የተሰሩ ጥናቶች

የመጀመሪያው ጥናት Suvi Keturi and Tiina Lehmonesn(2012):- “A Study of Taboo Content in Finnish EFL Textbooks for Upper Secondary School ” ለሁለተኛ ዲግሪ ከፊል ማሟያ በፈረንሳይ ባሉ የሁለተኛ ደረጃ የመማሪያ መፃህፍት ላይ ትኩረት አድርጎ የተሰራ ጥናት ነው፡፡ የጥናቱ አላማ የሁለተኛ ደረጃ የእንግሊዝኛ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የትኞቹ ርእሰ ጉዳዮች ነውር ነክ እንደሆኑ መመርመር ነበር፡፡ ከሶስት ታላላቅ አሳታሚዎች የሚታተሙትን ስድስት የተለያዩ መማሪያ መፃህፍት አይነቶችን በብዛት 44 ለናሙናነት ተጠቅሟል፡፡ ሁለት የፊንላንድ መማሪያ መፃህፍት ደራሲዎችን ቃለመጠይቅ አድርገዋል፡፡

በጥናቱ እንደታየው በፊንላንድ ባሉ የእንግሊዝኛ መማሪያ መፃህፍት በይዘት በጣም እንደሚለያዩና ስለነውር የሚያነሱ ጉዳዮች አነስተኛ እንደሆኑ ይጠቅሳል፡፡ ለዚህም ፖለቲካዊና

ሀይማኖታዊ መገለጫዎች እንደምሳሌ ይጠቀሳሉ፡፡ በቃለመጠይቁ ደግሞ አሳታሚዎች ራሱ በመፅሀፎቹ ይዘት ላይ የመወሰን መብት እንዳላቸውና ደራሲዎችም ርዕሰ ጉዳዮችን በመምረጥ ነፃነት እንዳላቸው ይገልፃል፡፡ በጥናቱ ማጠቃለያም በመማሪያ መጻህፍቱ ላይ የታዩ አላስፈላጊ ርዕሰ ጉዳዮችን ቢወገዱ እና እሴታቸውን የጠበቁ ጉዳዮች ቢካተቱ የሚል ድምዳሜ ሰጥተዋል፡፡

ይህ ጥናት ከኔ ጥናት ጋር የሚገናኘው ከነውር ጋር ተያያዥ ጉዳይ ይዞ መጠናቱ ሲሆን በይዘት ልዩነት አለን፡፡ ይህ ጥናት በእንግሊዝኛ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የነውር ይዘት ያላቸው ጉዳዮች ላይ ትኩረት ያደረገ ነው፡፡ የኔ ጥናት ደግሞ ከቋንቋ ጋር ተያያዥ ነውሮችን የማይመለከትና ነውር ተብለው የሚከለከሉ የተለያዩ ነገሮች ላይ ትኩረት ያደረገ ነው፡፡ ሌላው ልዩነታችን በተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች ላይ መሰራቱ ነው፡፡

ሁለተኛው ጥናት ደግሞ Oluwakemi Akintana, Sarah Jewittb, Mike Clifford (2018) Culture, tradition, and taboo: Understanding the social shaping of fuel choices and cooking practices in Nigeria. ጥናቱ በናይጀሪያ አዶ ኤኪቲ ውስጥ የሚኖሩ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ማህበረሰቦች ዘንድ የእንጨት ማገዶ አጠቃቀምና የምግብ አዘገጃጀት ልማዳቸውን በተመለከተ ያለውን ደንብ የሚመረምር ጥናት ነው፡፡

የማገዶ ምርጫዎች ለጤና ችግር እያመጡ በመሆናቸው እነዚህን የሚመለከቱ ባህላዊ ደንቦችን በማተኮር የተሰራ ነው፡፡ በጥናቱ ተሳታፊ ምልከታ በማካሄድ በአስራ ዘጠኝ መንደሮች ውስጥ አራት የጎሳው ተወላጅ ከሆኑ የቤት ባለቤቶች ጋር ቃለመጠይቅ ተደርጓል፡፡ የተገኘው ውጤትም ከአየር ብክለት ጋር በተያያዘ የሚመጡ በሽታዎች መንስኤ ባህላዊ የምግብ አዘገጃጀት ስርአትና እንጨቶችን ለማገዶነት ስለመጠቀሙ ነው ይላል፡፡

የአካባቢ ብክለትና የጤና ችግሮች ቢኖሩም በአብዛኛው ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ህብረተሰቦች የሚጠቀሙት እንጨት ነው፡፡ እነዚህንና መሰል ችግሮች ለመከላከል የአካባቢ ጥበቃ ላይ ትኩረት የሚያደርጉ ባህላዊ ህጎችና ደንቦች ያላቸው አስተዋፅኦ ከፍተኛ በመሆኑ ተጠናክረው ቢቀጥሉ የሚከሰተውን ችግሮች መቅረፍ እንደሚቻል ይገልፃሉ፡፡

ይህ ጥናት በቀጥታም ባይሆን በተዘዋዋሪ መንገድ ባህላዊ ህጎችና ደንቦችን የሚነካ ነው፡፡ የኔም ጥናት ባህላዊ ደንቦችና ህጎች/ ልማዳዊ ህጎችን የተመከተ ጥናት በመሆኑ በሁለቱም ጥናቶች

ህበረሰቡን ለመቆጣጠር ያላቸው አስተዋፅዖ ከፍተኛ መሆኑን ይገልፃሉ፡፡ ይሁን እንጂ በጥናቶቹ መካከል የተነሳንበት ርዕሰ ጉዳይና የትኩረት ነጥቦች እንዲሁም የቦታ ልዩነት አላቸው፡፡

## 2.2. ፅንሰ ሀሳባዊ ዳራ

በዚህ ርዕስ ስር የማህበራዊ ልማዶችን ምንነት፣ ልማዳዊ ሕጎች፣ የነውር ምንነት፣ የነውር መፈጠር ምክንያት እና ፋይዳ፣ የነውር አይነቶች፣ ማሕበራዊ ቅጣቶችና ሽልማቶች/Social sanction and rewards፣ የነውሮች ለውጥና ተከታታይነት/Change and continuity የሚመለከቱ ርዕሰ ጉዳዮች በስፋት የቀረቡበት ነው፡፡

### 2.2.1. ማህበራዊ ልማዶች/Social norms/

ማህበራዊ ልማዶች ሰዎች አጥብቀው የያዟቸው እምነቶችና ልማዶች መነሻ ምንጫቸውና ትርጉማቸው ምንድነው? ሰዎች በአንድ ነገር ለምን ያምናሉ? የሚያምኑባቸው ነገሮችስ ምንድናቸው? የተወሰኑ ልማዶችንስ ለምን ይከተላሉ? የሚሉና መሰል ጥያቄዎችን ለመመለስ የሚሞክር የፎክሎር ዘርፍ ነው (ፈቃደ፣1991፡13-14) ፡፡ እነዚህ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ አገልግሎት ላይ ከመዋላቸው በፊት ምንጩ ምን እንደሆነ፣ ምን ምን እነደሆኑ፣ ምክንያቱን፣ ብሎም ምን አይነት ተግባር እንዳላቸው ፅንሰ ሀሳቡን ጠቅሎ የያዘ እንደሆነ የሚገልፅ ነው፡፡

ማህበረሰቡ ለህይወቱ ይጎዱኛል የሚላቸውን የሚያርቅበት፣ ይጠቅሙኛል የሚላቸውን ደግሞ የሚያቀርብበት በኑሮው ውስጥ ዘወትር የሚተገብራቸው ልማዶች አሉት፡፡ በእነዚህ ልማዶች ላይ የራሱን ማብራሪያ የሚሰጥበትና ለራሱ ህግና ደንብ፣ ስርዓትና መመሪያ በማበጀት የሚመራባቸው ናቸው፡፡ ሆኖም በማህበረሰቡ ባህል፣ ታሪክ፣ መልክአ ምድራዊ አቀማመጥ፣ ፆታ፣ እድሜ፣ ማህበራዊ ደረጃ፣ በአስተዳደራዊ ስርዓት ወዘተ… ላይ የተመሰረቱ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ ደንቦች እንደ ማህበረሰቡ አኗኗር እና አካባቢያዊ ሁኔታ የተለያዩ ናቸው፡፡

Engert (2016፤341) ልማዶች የጋራ እውቀቶችን የሚፈጥሩ ሚዛናዊ ዘዴዎች (equilibrium stratégies that have been made common knowledge.) ናቸው ይላሉ፡፡ ልማዶች ሚዛናዊ የሀብት ክፍፍል፣ ፍትሃዊ ስርዓት እንዲኖር የሚያደርጉ፣ በማህበረሰቡ የእለት ተለት ኑሮ ውስጥ ዘወትር የሚከወኑ ስርዓቶች መሆናቸውን ይጠቅሳሉ፡፡ ጠቃሚ እሴቶችን ለማስከበር፤ የሚወደድ የሚጠላውን ጠብቆ ለማቆየት የሚጠቀሙባቸው ስልቶች ናቸው፡፡

ማህበራዊ ልማዶች ባህሪን የሚቀርፁ፣ ግለሰቦች በልማዶቹና ደንቦች መመዘኛዎች ውስጥ ያሉ ናቸው። Bicchieri, C (2016፡ 32) ሰዎች ፍላጎታቸውንና ስሜቶቻቸውን የሚገልፁበት እና ጠብቀው የሚያቆዩአቸው ናቸው። ከማህበራዊ ልማዶች መካከል ልማዳዊ ህጎች አንዱና ዋነኛ ተጠቃሽ ናቸው።

### 2.2.2. ልማዳዊ ሕጎች/Customary Law/

በአብዛኛዎቹ የአፍሪካ አገሮች የሕግ ምንጮች ልማዳዊ ሕጎችና ማህበራዊ ደንቦች ናቸው። "The sources of law in most African countries are customary law, Customary law has great impact in the area of personal law in regard to matters such as marriage, inheritance and traditional authority." (Ndulo, Muna (2011፡87

ልማዳዊ ህጎች በጋብቻ፣ በውርስ እና በባህላዊ የስልጣን ስርዓት ላይ ትልቅ ሚና ያላቸው ናቸው። እነዚህ ህጎች ከጥንት ሲወርድ ሲዋረድ የመጡ ናቸው። ለእያንዳንዱ ተግባራቶቻቸው ባህሪን የሚቀርፁት የባህል ህጎችን መሰረት በማድረግ ነው። ይህም በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉትን ስርዓቶች ለመምራት እና ባህሉንና እሴቱን ጠብቆ እንዲሄድ የሚጫወቱት ሚና ከፍተኛ በመሆኑ ነው።

Ezra Rosser (2008፤19) ልማዳዊ ህጎች በብዙ የጉሳ ፍርድ ቤቶች ተፈጥሯዊ በሆነ መንገድ ይግባኝ የሚጠየቅበት ነው። ይህም ባህላዊው ፍትህ በጉሳው/ በማህበረሰብ ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኝ የሚያደርግ እና ባህላዊ ህግን ስለሚያከብር ጭምር ነው። በዚህም በፍርድ አሰጣጡ ላይ ቅር የተሰኘ ካለ ቅሬታ ማቅርብ የሚቻልበት ህግ በመሆኑ እና ልማዳዊ ህጎችን የሚያከብር ሰርዓት የሚካሄድበት ስለሆነ በባህላዊው ፍርድ ቤት የተሰየሙት ሽማግሌዎችም ሆኑ ፍርድ ሰጪዎች ላይ ተአማኒነት እንዲኖረው ያደርጋል። እነዚህ ልማዳዊ ህጎች በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው በመሆኑ በመንግስት ለሚቀረፁ ህጎችም መነሻ መሰረት ሆነው የሚያገለግሉና ተፈፃሚነት ያላቸው ናቸው።

Wipo (2013;2) ልማዳዊ ህግ በአገሬው ተወላጆች እና በአከባቢው ማህበረሰብ ውስጥ እንደ አስገዳጅ ደንቦች የሚቀበሉ የባህሎች፣ ልማዶች እና እምነቶች ስብስብ ነው:: ልማዳዊ ሕግ የእነሱን ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት ለማስኬድ የሕይወት ዋነኛ መንገድ ነው:: እነዚህ ህጎች የተለያዩ ህጎች ስብስብ እንደሆኑና በማህበረሰቡ ዘንድ ሰፊ ቦታ የሚሰጣቸው መተዳደሪያ ደንቦች መሆናቸውን የሚገልፅ ነው።

WIPO (2013፤6) ቀጥሎም ልማዳዊ ህግ የአካባቢው ማህበረሰቦችን ህይወት ውጤታማ በሆነ መንገድ ሊመራ የሚችል ሲሆን በራሱ በሀገሩ ተወላጅ እና ማህበረሰብ አማካኝነት የተቀረፀና በአኗኗሩ በሚመች መልኩ የሚመራበት የህይወቱ አንዱ አካል ነው። እንደ አቋም ሊቆጠር ይችላል:: እንደዚህ ያሉ ሕጎች የተደነገጉ ብቻ ናቸው:: የልማዳዊ ህግ አስገዳጅነቱ /ውጤቱ ሙሉ በሙሉ ሊታወቅ የሚችለው ድርጊቱ ሲጣስ ብቻ ነው በማለት ይገልፃሉ። ይህም ማህበራዊ ደንቦችና ህጎች ከማህበረሰቡ የመነጩ፣ በይዘታቸውም የማህበረሰቡን ህይወት የሚገልፁ፣ ለአኗኗራቸው መሰረት በመሆን የሚያገለግሉ ናቸው:: በመሆኑም የተከለከሉ ነገሮች በማይከበሩበት ወቅት ልማዳዊ ህጎቹ ተግባር ላይ ይውላሉ። በዚህ ጊዜ የልማዳዊ ህጎች ተግባር/ጥቅም ምን እንደሆነ ውጤቱ ይታወቃል ማለት ነው።

Ezra Rosser (2008፤18) "Tribal courts formed by customs and traditions, customary law's meaning is also based upon its service in defining the role of tribal courts" የጎሳ ፍርድ ቤት በባህልና ወግ የተመሰረተ ቢሆንም ልማዳዊ ሕግ ትርጉሙ በአገልግሎቱ ላይ የተመሰረተና የጎሳዎች ፍርድ ቤት ሚና ምን እንደ ሆነ ማሳየት ነው። በዚህም ባህሉንና እሴቱን መሰረት በማድረግ የሚመሰረቱ በመሆናቸው የሚጫወቱት ሚና ከፍተኛ በመሆኑ በህብረተሰቡም ዘንድ ተአማኒነትና ተቀባይነት አላቸው። ብሎም በመንግስት ለሚቀረፁ ህጎችም ምንጭ በመሆን የሚያገለግሉ ናቸው።

### 2.2.3. የነውር ምንነት /The meaning of taboo

የነውር ምንነት በተመለከተ ኪዳነወልድ ክፍሌ (1948፣ 643) "ነውር በቁሙ ሕፀፅ፣ ገመና፣ ነውረኛነት የመልክ፣ የሕዋስ፣ የግብር..." በማለት ሲፈታው ደስታ ተክለወልድ (1962፣857) "ነውር በሰው በእንስሳ ላይ ያለ ዕብጠት፣ ጉድለት፣ ላይን የሚያስቀይም ክፉ ግብር፣ሀጢአት፣ ስካርን፣ ምንዝርን የመሰለ፤ ነውራም/ነውረኛ ነውር ያለበት፣ ነውር አድራጊ፣ ባለነውር፤ ነውር ነው ማለት እንኳን ሊሰሩት ሊሰሙት አይገባም" በማለት የተከለከለ ክፉ ነገር እንደሆነ ይገልፁታል።

Oxford Online Dictionary of English (2010/11፤11) ነውሮች አንድ ማህበረሰብ አካባቢያዊ ልምዱን መሰረት አድርጎ የሚፈጥራቸው ባህላዊ ደምቦች ናቸው። በማለት ሲተረጉም Frued (2004፣21) ነውር (tabbo) የሚለው ቃል በተለያዩ በሁለት አቅጣጫ ማየት እንችላለን። አንደኛው የተቀደሰ (sacred)፣ አንደቅዱስ የሚታሰብ/የተሰጠ ('consecrated') ማለት ሲሆን

በሌላ በኩል በጣም ረቂቅ ('uncanny')፣ አደገኛ/የሚፈራ ('dangerous')፣ ክልክል (forbidden')፣ ርኩስ ('unclean') ወ.ዘ.ተ… በማለት ይተረጉመዋል፡፡

"Taboo is an English word coming from the Tongan word tabu. in the Polynesian peoples' that mean forbidden, such when a thing is not allowed to be eaten, touched or entered." Asima Habibovic (2010፥5-6). Taboo የሚለው የእግሊዝኛ ቃል ታቡ ከሚለው የቶንጋን ቃል የመጣ ሲሆን ትረጉሙ የተከለከለን ነገር፣ መደረግ የሌለበት ከመብላት፣ ከመንካት ወይም ከመግባት መከልከል በማለት ይገልፃል፡፡

ከላይ ከተሰጡት ፍቺዎች ወይም ትርጉሞች በመነሳት ነውር የሚለውን ቃል ፈፅሞ የማይደረግ ነገር፣ የማይፈቀድ ነገር፣የተከለከሉ ነገሮች እንዳይጣሱ የሚከላከል አጥር፣ ክልክል ወይም ድንጋጌ ነው ማለት ይቻላል፡፡

"A taboo is an "unthinkable" action. Even the thought of violating a taboo triggers a punishment. We consider a model in which taboos are part of the definition of one's identity." Fershtman (2011፡139) ነውር የማይታሰብ ድርጊት ነው ይህንን መዳፈርና መጣስ ቢኖር እንኳን ቅጣትን ያስከትላል፡፡ ነውርን የማንነት መገለጫ ሞዴል አድርገን ማየት እንችላለን፡፡ የመቆየቱ ጥንካሬ የሚወሰነውና የሚለካው በሚታዘዙት ግለሰቦችና በሚሰጠው አክብሮት ነው፡፡ ይህም የመኖር ህልውናው የሚታወቀው ማህበረሰቡ በሚሰጠው ቦታና በሚውለው አገልግሎት ላይ የሚጫወተው ሚና የጎላ ሲሆን ነው፡፡

ነውሮች እንደ ከባድ ማህበራዊ ማዕቀቦች የተደገፉ፣ ጠንካራ ማህበራዊ ደንቦች ተደርገው ሊታዩ ይችላሉ፡፡ በዚህም የማህበራዊ ደንቦች ማስከበሪያ በመሆን ስለሚያገለግሉ እንደ ህግ የሚታዩም ናቸው፡፡

### 2.2.4. የነውሮች መፈጠር ምክንያትና ፋይዳ

ሰዎች ህይወታቸውን ለመምራት የተለያዩ ነገሮችን ይፈጥራሉ፡፡ እነዛንም ነገሮች ሲፈጥሩ ከአኗኗራቸው ጋር አመቺ እንዲሆን በማድረግ ባህላቸውን፣ እሴታቸውን፣ አካባቢያቸውን፣ የአየር ንብረቱን፣ በአካባቢው የሚያገኙትን ነገሮች መነሻ አድርገው ነው፡፡ ሰዎች ከፈጠሯቸው ነገሮች መካከል የባህላቸው አንዱ አካል ነውሮች ናቸው፡፡ ስለነውሮች መፈጠር ምክንያት ሞላ (2009፣ሥ) ሲጠቅስ "ማህበረሰቡ ነውሮችን የሚፈጥረው የአባላቱን ባህሪና አስተሳሰብ ለመግዛት፤ የልጆቹን ሰብዕና ለመቅረፅ፤ ስጋዊና መንፈሳዊ ፍላጎቶቹን ለማርካት፤

በአጠቃላይም ለአኗኗሩ መርህ፣ ለግንኙነቱ ደንብና ህግ ሆነው እንደሚያገለግሉት በማሰብ ነው፡፡ በመሆኑም ማህበረሰቡ ነውሮች ከጥቅም በስተቀር የጎንዮሽ ጉዳት ሊኖራቸው ይችላል የሚል እምነት የለውም…” በማለት ይገልፃል፡፡

ይህም ነውሮች የሚፈጠሩት ህግና ደንብ በመሆን እንዲያገለግሉት ሲሆን በአካባቢው ካሉት ነገሮች በመነሳት ከአኗኗሩ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚገናኙ ነገሮች ላይ በመመርኮዝ ነው፡፡ ማህበራዊ ደንቦችና ህጎች፣ ነውሮች ተብለው የወጡት በቃል ሲሆን በተግባር ላይ የዋሉና ከትውልድ ወደ ትውልድ በቃል የሚተላለፉ ናቸው፡፡ እነዚህን ህጎችና ደንቦች ለልጆቹና ለሌሎች የማህበረሰቡ አባላት የሚያስተላልፈው ወይም የሚያስተምረው (ይህ ብታደርግ እንዲህ ያለ ነገር ይደርስብሀል፤ ብታከብር ደግሞ እንዲህ ያለ ነገር ታገኛለህ) በማለት አድርግ አታድርግ በሚል ስልት ነው፡፡

በመሆኑም ነውሮች የኑሮ ቀውስና መፋለስ እንደይኖር የሚከላለከሉ፣ የሚመቹ የማይቆረቁሩ እንደ ዘዴ፣ መላ፣ ብልሀት ያሉ የማይጨበጡ የቀልጣፋ ስርዓት ጠባዮች ናቸው፡፡ እንደ አለንጋ የሚጋረፉ ተግሳጾች፣ ከራስ ጋር ተስማምቶ ለመኖር፣ ሚዛን ጠብቆ የመራመድ፣ ቅን ህሊናን ለመፍጠር፣ ለምኞትና ለስሜት ልጓም የሚሆኑ፣ የቅንነትና የልብ ንፅህና፣ የፍቅር፣ የስምምነት፣ የመግባባትና የመደጋፍ እሴት መገለጫዎች ናቸው፡፡

### 2.2.5. የነውር አይነቶች/Types of taboo

በአንድ ማህበረሰብ ያሉ ባህሎች፣ እሴቶችና ልማዶች እንደየ አካባቢው ሁኔታ የተለያየ መልክና አይነት አላቸው፡፡ በመሆኑም ነውሮችም እንዲሁ እንደማህበረሰቡ አኗኗር ሁኔታ፣ የአየር ንብረት፣ ማህበራዊ ሁኔታና ባህል መሰረት አድርገው የሚፈጠሩ ስለሆኑ የተለያዩ ናቸው፡፡ ነውሮችን አምኖና ተቀብሎ በሚኖረው ማህበረሰብ አኗኗር፣ ማንነት እና ህልውናው ላይ የተመሰረተ ስለሆነ የተለያየ ህግና ደንብ ይኖራል፡፡ ለዚህም ነው የአንዱ ነውር ለሌላው ምንም ያልሆነው፡፡

የነውር አይነቶችን አስመልክቶ Suvi Keturi and Tiina Lehmonesn (2012፤56) እንደሚገልፁት “The types of taboos are difficult to categorize since they partially overlap. Some taboo topics, for example, have corresponding taboo words, whereas others do not. (Andersson and Trudgill 1990:56.) For instance, cannibalism is a forbidden act, but the word cannibalism is not taboo.

Furthermore, the act of prostitution and the corresponding word prostitute and whore are both taboo."

የነውር ዓይነቶች በከፊል ከሚደረጉት በቀር ለመመደብ አስቸጋሪ ናቸው። አንዳንድ የነውር ርእሶች በቃላት የሚገለፁ፣ የሚከለከሉ አሉባቸው, ሌሎች ግን አይደረጉም። ለምሳሌ ያህል የሰው ሥጋ መብላት (cannibalism) የተከለከለ ድርጊት ነው፤ ነገር ግን ካኒባሊዝም (cannibalism) የሚለው ቃል የተከለከለ አይደለም። በተጨማሪም የዝሙት አዳሪነት እና ዝሙት አዳሪ የሚለው ቃል ሁለቱም ነውር ናቸው። (ትርጉም በኔ)

ከዚህ ሀሳብ የምንረዳው የነውር አይነቶች አንዳንዶቹ በንግግር ደረጃ የሚከለከሉ ሲሆኑ ሌሎች ደግሞ በተግባር/በስራ የሚከለከሉ ናቸው። እነዚህ እንደየቦታውና ሁኔታው የተለያዩ ናቸው። በአንዳንድ ቦታዎች ከሰው ፊት በአደባባይ የማይወሩ ክልክል የሆኑ ቃላት በሌላው ቦታ ደግሞ እንደልብ የሚወሩ የማይታፈሩበት ሁኔታ አለ። እንዲሁም በአንዱጋ የሚከለከሉ ድርጊቶች በሌላው ምንም ችግር እንደሌለውና እንደሚያደርጉት ይገለፃል። ለዚህም ልዩነቱ የመጣው የተለያየ አካባቢና የአኗኗር ዘዬ በመኖሩ ነው።

MARY DOUGLAS (1966;8) ደግሞ ነውሮች ሀይማኖታዊና ባህላዊ ይዘት ያላቸው እንደሆኑ ይገልፃሉ። በሀይማኖት ተቋማት የሚከለከሉ ነገሮች በባህሉ ውስጥም ክልክል ሆነው ይነገራሉ። እንደምሳሌ ሲጠቅሱ የአሳማ ስጋ መብላት በሀይማኖት ክልክል ነው ርኩስና አጋንንት የሰፈረበት ተደርጎ ይቆጠራል፤ በባህሉም ዘንድ ይህንን ማድረግ ክልክል ነው። ለዚህም ምክንያቱ ሀይማኖትና ባህል በሰው ልጆች ህይወት ውስጥ ያሉና የተቆራኙ ጉዳዮች በመሆናቸው ነው።

Fershtman (2011: 140) "The list of taboos and their importance may change over time. Some taboos may weaken or even disappear, while others may become stronger and more dominant." የነውሮች አይነትና ያላቸው ፋይዳ በጊዜ ሂደት የሚለወጥ ነው። የተወሰኑ ነውሮች ሊዳከሙና ከነጭራሹ ሊጠፉ፤ ሌሎች ደግሞ የበለጠ ሊጠነከሩ ይችላሉ። እንደ Fershtman አገላለፅ የተለያዩ የነውር አይነቶች አሉ ይሁን እንጂ ከበፊት ጀምሮ የነበሩት በቆይታ ብዛት እየተቀየሩ የሚመጡ ናቸው። ከፊሉ ለረጅም ጊዜያት የሚቆዩ ሲሆኑ የተቀሩት ደግሞ ሊጠፉም ይችላሉ። እንደጊዜው ሁኔታና የሰዉ አኗኗር አካባቢያዊ ምክንያት አይነታቸው ይቀያየራል።

አንዳንድ ነውሮች የማህበረሰቡን ባህልና እሴት፣ እድሜ፣ ፆታ፣ ማህበራዊ ደረጃ፣ የሚጠቀሟቸውን ነገሮች ( ለምሳሌ፡- ምግብና መጠጥ የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሳቁስ) መሰረት አድርገው የሚፈጠሩ ናቸው፡፡ እንደሚጠናበት ማህበረሰብ ባህልና እምነት አስተሳሰብ እውቀትና ፍልስፍና የተለያየ ይዘት ይኖራቸዋል፡፡ በመሆኑም የነውር አይነቶችን እንደዚህ ናቸው ብሎ መመደብ አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ ስለዚህ በዚህ ጥናት በትንተናው ክፍል የተገለፁት የነውር አይነቶች የተጠኘውን ማህበረሰብ ባህልና እምነት አስተሳሰብ መሰረት አድርገው እንደማህበረሰቡ አመዳደብ አይነት የተገለፁ ናቸው፡፡

### 2.2.6. የነውሮች ለውጥና ተከታታይነት/Change and continuity

ተከታታይነት (Continuity)፡- ተከታታይነት በጊዜ ሂደት ውስጥ የልማድን ቀጣይነት/ የማያቋርጥ ሂደት የሚገልፅ ሃሳብ ነው፡፡ ፅንሰሃሳቡ በልማድ ውስጥ ያለ ጊዜንና የልምዱን ድግግሞሽ ይመለከታል፡፡ ልምድ ደግሞ በጊዜ ሂደት ውስጥ በሚደረግ ድግግሞሽ የሚፈጠር ነው፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ የልምዶች ድግግሞሽ፣ የእያንዳንዱ እንቅስቃሴ መኖር ልምድን ቀጣይነት እንዲኖረው ያደርገዋል፡፡ Sims and Stephens(2005, 65) በየትኛውም የጊዜ ርዝመት የሚደረግ ድግግሞሽ ልምድን ይፈጥራል፡፡ የልምድ መደጋገም ደግሞ ተከታታይነትን ይፈጥራል፡፡ ተከታታይነት የነበረውን መስሎ መቀጠል እንዳልሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ምክንያቱም ልምድ በተደገመ ቁጥር ራሱን መስሎ አይወጣም፡፡ በቡድኑ ውስጥ የልምዱን ትርጉም ወይም ጥቅም ያያያዙ ነገሮችን የሚመለከት ነው ይላሉ፡፡

በመሆኑም ተከታታይነት የልምዶችን ድግግሞሽ የሚያሳይ ፅንሰሃሳብ ሲሆን ከልምዶች መካከል ነውሮች አንዱ አካል ናቸው፡፡ ከትውልድ ወደትውልድ እየተላለፉ የመጡ፤ በተከታታይ ሲጠበቁና ሲከበሩ የነበሩ፤ በአሁንም ጊዜ የሚከበሩ ነውሮች አሉ፡፡ እነዚህን ነውሮች በልማዶቻቸው እና በእሴቶቻቸው አማካኝነት ይዘው ያቆዩአቸው ናቸው፡፡ ነውሮች በተከታታይ እየተከበሩ ሲመጡ ቀድሞ የነበረውን አተገባበር ይዘው ላይቀጥሉ ይችላል፡፡ ሆኖም የሚሰጣቸው ትርጉምና የሚሰጡት ጠቀሜታ ቀጣይነት ይኖረዋል፡፡

አንዳንድ ጊዜ የልምዶች ድግግሞሽ የሚቋረጥበት እና የሚጠፉበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል፡፡ በዚህም ደግሞ የልምድ ሌላኛው ባህሪ ለውጥ የሚከሰት ይሆናል፡፡

ለውጥ (Change)፡- የኢትዮጵያ ቋንቋና ጥናት ምርምር ማዕከል፣ አማርኛ መዝገበቃላት (1993፣ 21) ‹‹ለውጥ›› የሚለውን ቃል አዲስ ሁኔታ፣ የተለየ ነገር፣ ልዩነት ሲል ይፈታዋል፡፡ አንድ ነገር ቀድሞ የነበረውን ሁኔታ፣ ባህርይ፣ መልክ በሌላ ቀየረ፣ ተበላሸ፣ ቀድሞ ከነበረው አሻሻለ ይለዋል፡፡ Oxford Advanced Learner's Dictionary ደግሞ አሮጌውን ስልት በመተው አዲሱን መያዝ ይላል፡፡ ለውጥ የሚለው ፅንሰ ሃሳብ የልዩነትን መፈጠር የሚያመለክት እንደሆነ የሚገልፅ ነው፡፡ ለውጥ ሲባል በፊት የነበረው ነገር መቀየር ሲሆን አቀያየሩም በሌላ መተካት፣ መበላሸት ወይም መሻሻል ሊሆን ይችላል፡፡

Tolken (1996፣ 45) በማንኛውም ሁኔታ ልምዱ ላይ የሚደረጉ ፈጠራዎች ለውጥ ናቸው ይላሉ፡፡ በነበረው ተጨባጭ ሁኔታ ላይ በጊዜ ብዛት የተፈጠሩ ማሻሻያዎች፣ የተተኩ ነገሮች መፈጠራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ Sims and Stephens (2005፣85) በውጫዊና ውስጣዊ ሁኔታዎች ምክንያት ልምድ ይለወጣል፡፡ በፎክሎር እሳቤ መሰረት ልምዶች የሚኖሩት ቡድን ካለ ነው፡፡ ቡድኑ በዝምድና፣ በጎሳ፣ በሃይማኖት፣ በቦታ ወዘተ የተሳሰረ በመሆኑ ሁልጊዜም አንድ አድርጎ የሚይዘው ልምድ አለው፡፡ ልምዱ ለእያንዳንዱ አባል ቡድኑን የመጠበቅ ሃላፊነት እንዲሰማው የማድረግ ጠንካራ አቅም አለው፡፡ ስለዚህም ምንጊዜም ቢሆን ቡድኑ ልምዱ እንዳይጠፋበት የመጠበቅ ተግባር ያከናውናል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ከተገለፁት ሃሳቦች በመነሳት ወደ ርዕሰ ጉዳዩ ስናመጣ በተለያዩ ጊዜና ሁኔታዎች አማካኝነት በነውሮች ላይ የተለያዩ ለውጦች ይከሰታሉ፡፡ ነውሮች ሁል ጊዜ ቋሚ ወይም እንደነበሩ ሆነው የሚቀጥሉ ሳይሆኑ ባለው ተጨባጭ ሁኔታና ባለው ጊዜያዊ ፍላጎት የመለወጥ፣ የመሻሻል እና ከነጭራሹ የመክሰም ባህሪ የሚታይባቸው ናቸው (Osei,2006፡ 44-45)፡፡ ይህም በማህበረሰቡ የኑሮና አካባቢያዊ ሁኔታ ጋር ተያይዞ ቀድሞ ሲከበሩ የነበሩ በአሁን ጊዜ የመቅረት ወይም በሌላ የመተካት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡

አሁን ያለው የማህበረሰቡ አኗኗር በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና በፖለቲካዊ ሁኔታዎች፤ እንዲሁም የመኖሪያ አካባቢዎችን በሚቀያየሩበት ወቅት አመለካከቱና አስተሳሰቡ እየተቀየረ ይመጣል፡፡ ለነውሮች የሚሰጠው ቦታና አክብሮት ይጨምራል ወይም ይቀንሳል፡፡ ነውር በማህበረሰቡ ዘንድ የመከበር አቅሙ ይዳከማል፡፡ በመሆኑም በዚህ ጥናት ከዚህ በፊት ሲከበሩና ሲጠበቁ የነበሩ በአሁን ሰዓት የቀሩ ወይም የተለወጡ ነውሮችን እና ለውጡ የተከሰተበትን ምክንያት በተመለከተ መረጃዎችን ተመርኩዞ ትንተና ቀርቧል፡፡

### 2.2.7. ማሕበራዊ ቅጣቶችና ሽልማቶች/Social sanction and rewards

ማህበራዊ ልማዶች በማህበራዊ ቅጣቶች አማካይነት የሚጸኑ ናቸው (social norms are enforced through social sanctions) ፤ ልማዱን (ህጉን) የጣሰ ሲኖር አግባብነት ያላቸው ቅጣቶች አስከፊ /አስደሳች ገደብ የሚጥሉ (The relevant sanctions create a range of unpleasant (but sometimes pleasant) emotional states in people who have violated norms.) ናቸው። (Cass (2013:15) ይህም ማህበራዊ ቅጣቶችና ሽልማቶች ልማዶችና ህጎች እንዲከበሩ የሚያደርጉ፣ ሲጣሱ የሚቀጡ ሲሆኑ ያከበሩትን ደግሞ የሚሸልሙ ናቸው።

LUIS G. NARDIN (….፤2) “A sanctions…, whose primary aim is promoting norm compliance. A sanction can be negative or positive.” የቅጣቶች አላማ ልማዶችን ማስከበርና ማስጠበቅ ነው፤ ቅጣቱ አወንታዊ ወይም አሉታዊ ሊሆን ይችላል። ማህበራዊ ቅጣቶች ዋነኛ ተግባራቸው የማህበረሰቡን ልማዶችና ደንቦች ማስከበር ሲሆን ሲጣሱም እንደ ጥፋቱ አይነት የተለያዩ እና አስተማሪ ወይም አስከፊ ቅጣት የሚጥሉ ናቸው። በተቃራኒው ደግሞ ማህበራዊ ሽልማቶች ልማዶችና ደንቦች ሲከበሩ የሚሸልሙ ናቸው።

## 2.3. ንድፈ ሀሳባዊ ዳራ

በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር ጥናቱን የሚመሩ የመረጃ መተንተኛ ንድፈ ሀሳቦችን ምንነትና የተመረጡበትን ምክንያት በሚመለከት መረጃ የቀረበበት ነው። የፎክሎር ጥናት ከተለያዩ የማህበረሰብ የጥናት መስኮች ጋር ንድፈ ሀሳቦችንና የመተንተኛ ስልቶችን የሚጋራ የጥናት ዘርፍ ነው። በመሆኑም ለጥናቱ የተመረጡት ንድፈ ሀሳቦች ፍካሬ ልቦና እና ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ (Functional theory) ናቸው። ምንነታቸውና የተመረጡበት ምክንያት እንደሚከተለው ቀርቧል።

### 2.3.1. ፍካሬ ልቦናዊ ንድፈ ሀሳብ/ Psychoanalytical theory

ይህ ንድፈ ሀሳብ የሲግመንድ ፍሮይድ አስተሳሰብን መሰረት ያደረገ ንድፈ ሀሳብ ነው። ሰሎሞን (2007፣77) ፍሮይድ (1958) በመጥቀስ “ህልሞች በሰው ልጅ በከፊል ንቁ(sub conscious mind) ውስጥ ያሉ አስተሳሰቦችን የሚያንፀባርቁ እንዲሁም ሚቶች፣ አምልኮዎች፣ ተረቶችና ሀራም/taboo የሆኑ ጉዳዮች በሰው ልጅ የኢ-ንቁው አእምሮው ክፍል ውስጥ ለረጅም ጊዜ ተሸሽገውና ታምቀው የቆዩ ድብቅ ፍላጎቶችን የሚገልፁ መሆናቸውን ይገልፃል።”

ሰዎች በአእምሯቸው ውስጥ ያለውን አስተሳሰብ፣ ስሜትና ፍላጎት ለመግለፅ በተለያዩ ባህላዊ፣ማህበራዊና ሀይማኖታዊ አጋጣሚዎች አማካኝነት የተለያዩ መገለጫዎችን እንደመሳሪያነት ይጠቀማሉ፡፡ ከነዚህም መካከል ባህላዊ መገለጫዎች ይጠቀሳሉ፡፡ እነዚህ የማህበረሰቡን እምነት፣ ፍላጎት፣ አስተሳሰብና አመለካከት ወዘተ የሚገለፅበት ሲሆን ከመገለጫዎች መካከል ማህበራዊ ደንቦችና ህጎች ዋነኛ ተጠቃሽ ናቸው፡፡

ማህበረሰቡ ይጎዱኛል የሚላቸውን የሚያርቅበት፣ ይጠቅሙኛል የሚላቸውን ደግሞ የሚያቀርብበት በኑሮው ውስጥ ዘወትር የሚተገብራቸው ልማዶች ናቸው፡፡ በህይወቱ ላይ ተፅዕኖ ያሳድሩብኛል፤ ይጎዱኛል ብሎ ለሚያስባቸው/ለሚፈራቸው ነገሮች፣ ስጋት ውስጥ ከሚከቱት ነገሮች ለመከላከል ሲል የራሱን ህግ ያወጣል፡፡ እነዚህ ደግሞ ከስነልቦና ጋር ተያያዥ ጉዳዮች በመሆናቸው በነውሮች አማካኝነት የሚከለከሉና የሚፈቀዱ ነገሮችን ይገልፁባቸዋል፡፡

ሰሎሞን (2007፣78) "የፍሮይድን ፍካሬ ልቦና መሰረት በማድረግ በተለያዩ ሀገራት የሚገኙ ተረቶች፣ ሚቶች፣ ፌስቲቫሎች፣ ጨዋታዎች፣ ውዝዋዜዎች፣ ሙዚቃዎች፣ እንቆቅልሾች፣ እምነቶች፣ ህልሞችና ሌሎች ሎሮችም ባላቸው ትዕምርቶች ማስተላለፍ የተፈለጉ ስነ-ልቦናዊ ጉዳዮችን ለመተንተን አስችሏል፡፡" ነውሮች በሰነድ ያልሰፈሩ ልቦናዊ ህጎች ሲሆኑ የሰው ልጅ አእምሮ ላይ የሚቀረፁና የሚሰርፁ በመሆናቸው ስነልቦና ላይ የሚጫወቱት ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ ማህበረሰቡም ነውር የተባሉ ነገሮችን አምኖና ተቀብሎ ስለሚኖር የተከለከሉ ነገሮች ቢጣሱ ይደርሳል ተብሎ የሚታሰቡትን በማሰብ ያከብረዋል ይጠብቀዋል ማለት ነው፡፡ ስለዚህ በስነልቦና ላይ የሚያሳድሩት አወንታዊና አሉታዊ ተፅዕኖዎች አሉ፡፡ በመሆኑም ስነልቦናዊ ጉዳዮች ከሚገለፁባቸው መንገዶች አንዱ ነውሮች ስለሆኑ በፍካሬ ልቦና ንድፈ ሀሳብ ለመቃኘት አመቺ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

### 2.3.2.ተግባራዊ/ጠቀሜታዊ ንድፈ ሀሳብ/Functional theory

"ጠቀሜታዊ ንድፈ ሀሳብ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ያሉ የተለያዩ ሎሮች ለማህበረሰቡ የሚሰጡትን ጠቀሜታና በቡድኑ ውስጥ ያላቸውን አውዳዊ ትርጓሜ በማሳየት ላይ ትኩረት የሚያደርግ ነው፡፡" ሰሎሞን (2007፣75) ይህ ንድፈ ሀሳብ በማህበረሰቡ ዘንድ የሚገኙ ሎሮች ለምን አገልግሎት እንደሚውሉና ማህበረሰቡ ምን አይነት ትርጓሜ እንደሚሰጣቸው የሚመረምር ነው፡፡ ፎክሎሩ የሚኖረውን ፋይዳ/ተግባር የሚያመለክት ነው፡፡

የፎክሎርን ተግባራት በተመለከተ Bascom (1954;346) ፎክሎርና ትርጉሙ ከሰው ጋር የተሳሰሩና ፎክሎር የማስተማር፣ የማዝናናት፣ የማስተላፍ፣ ባህላዊ ማንነትን የማስጠበቅ ተግባር እንዳለው ይገልፃሉ፡፡ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ምን አይነት ሎር እንዳለ፣ ለምን አገልግሎት እየዋለ እንደሆነ ለማወቅ ይረዳል፡፡ ( Okpewho(1992;173 ) ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ በአንድ ፎክ ቡድን ውስጥ የሚከወን ማንኛውም ነገር ያለውን ተግባርና አገልግሎት ለመመርመር የሚረዳ ነው በማለት ይገልፃል፡፡

ንድፈ ሀሳቡ ፎክሎር በማህበረሰቡ ውስጥ ምን ተግባር እንዳለውና ምን አይነት ትርጓሜ እንደሚሰጡት መመርመር ዋና ትኩረቱ ነው፡፡ ስለሆነም ከሚጠቀሱት ሎሮች መካከል ነውሮች ዋነኛ መተዳደሪያ ደንቦች በመሆናቸው በተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ መሰረት ምን አይነት ሚና እንዳላቸው፣ የሚሰጣቸው ትርጓሜ ምን እንደሚመስል እንደማህበረሰቡ አስተሳሰብና አመለካከት መመርመርና ማወቅ ይቻላል ማለት ነው፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

# የጥናቱ ዘዴ

ይህ ጥናት "ነውር እንደ ማህበራዊ ደንብ ማስጠበቂያ ስልትነት በዶርዜ ማህበረሰብ" በሚል ርዕሰ ጉዳይ የተዘጋጀ ሲሆን በማህበረሰቡ የቋንቋ አገላለፅ፣ ባህሉንና እሴቱን ጠብቆ እንደማህበረሰቡ አተያይ፣ አመለካከትና አተረጓጎም የሚገልፅ ነው፡፡ በመሆኑም አይነታዊ የምርምር ዘዴን ይከተላል፡፡

ያለው (2001፣19) "በምርምር ሂደት ሁሉም ነገሮች በቁጥር የሚገለፁ ወይም የሚወከሉ አይደሉም፡፡ ተመራማሪው ለማጥናት የፈለገው ጉደይ በመጠን ሳይሆን በአይነት የሚገለፅ ይሆናል፡፡ ስለዚህ በአይነታዊ ምርምር ተመራማሪው የሚያጠናቸው ጉዳዮች ሁሉ በመጠን ይህን ያህል ተዛምዶ ወይም ልይይት (variation) አላቸው ተብሎ ያገኛቸውን መረጃዎች በስታቲስቲካዊ ዘዴ አይገልፃቸውም፡፡ መረጃዎቹን ተንትኖ የጥናቱን ውጤት ላንባቢ የሚያቀርበው ትረካዊ ወይም ገለፃዊ መንገድን ተከትሎ ነው፡፡ የመረጃ አሰባሰቡ ሂደትም ሆነ አተናተኑ ከመጠናዊ ምርምር ይለያል፡፡" ስለዚህ በዚህ ጥናት የተሰበሰቡ መረጃዎች ከቁጥርና ከመጠን ይልቅ ፅንሰ ሀሳባዊና ፅሁፋዊ መረጃዎች ናቸው፡፡ በመሆኑም አይነታዊ የምርምር ዘዴን የተከተለ ነው፡፡

## 3.1. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ

በዚህ ጥናት መረጃዎች የተሰበሰቡት በቀዳማይና ካልዓይ የመረጃ ምንጮች ነው፡፡ በቀዳማይ ስር ምልከታ፣ ቃለመጠይቅና ቡድን ተኮር ውይይት ናቸው፡፡ በካልዓይ ደግሞ መዛግብት ፍተሻ ነው፡፡

### 3.1.1. ምልከታ

"የምልከታ ዘዴ መረጃ ሰብሳቢው ሰው መረጃ ለመሰብሰብ ከሚፈልግባቸው ተጠኝዎች ጋር ወይም አካባቢ በመሆን የሚያደርጉትንና የሚናገሩትን ነገር በቅርበት ሆኖ እያየና እየሰማ በመዘገብ መረጃ የሚሰበስብበት ዘዴ ነው፡፡" ያለው (2001፣188) በመሆኑም፣ በዚህ ጥናት ወደ ተጠኙው ማህበረሰብ በመሄድ ምልከታ በማካሄድ አስፈላጊው መረጃ ተሰብስቦበታል፡፡ የተሰበሰበው መረጃም ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር በተያያዘ ነውር የተላለፉትን ሰዎች ወደ ቀድሞ

ማንነታቸው እንዲመለሱ ማስፈፀሚያ ዘዴዎችን፣ የቅጣት አይነቶችና እንዴት እንደሚቀጧቸው የአፈፃፀም ሂደቱን በተመለከተ ምልከታ ተካሂዷል፡፡

በዚህም የተመረጡት አውዶች ሰዎች የሚሰበሰቡባቸው አጋጣሚዎች በክብረ በአል/በተለይ የመስቀል በዓል(2011) እና የፆም ፍቺ በአል አከባበር(2011 ፋሲካ)፣ ለቅሶ፣ የሽምግልና ስርዓት(መጋቢት 11፣18 እና25)፣ የደቦ ስራ ላይ(2011 ሚያዝያ ወር ሰርግ ላይ ) እንዲሁም ቡና ጠጡ ላይ ሲሰባሰቡ በመገኘት መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ በነዚህም ምልከታዎች ላይ መሳተፍ በምችልባቸው አጋጣሚዎች ተሳታፊ ተመልካች በመሆን፣ መሳተፍ በማልችልባቸው ሁኔታዎች ደግሞ ዳር ቆሞ ተመልካች በመሆን ምልከታ አካሂጃለው፡፡

በተጨማሪም ከጥፋት መመለሻ ዘዴዎችንና ቅጣቶች ለማየት ቅንብር ተፈጥሯዊ መቼት ተግባር ላይ ውሏል፡፡ ለዚህም ደግሞ የሽምግልና ስርአቱን እንዲያሳዩኝ በመጠየቅ (ሚያዝያ 3 2011) ኢ-ንቁ ተሳታፊ በመሆን አስፈላጊው መረጃ ተሰብስቧል፡፡

### 3.1.2 ቃለመጠይቅ

ቃለመጠይቅ የምንፈልጋቸውን መረጃዎች ከተጠኝዎች በቃል በመጠየቅ መረጃን የምንሰበስብበትና የምንመዘግብበት ሂደት ነው፡፡ ያለው (2001፣187) በመሆኑም በዶርዜ ማህበረሰብ ውስጥ ህግና ደንቡን የሚያውቁ ቁልፍ ሰዎችን፣ የሀገር ሽማግሌዎችን በመጠየቅና ማብራሪያ እንዲሰጡበት በማድረግ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ የተሳተፉ ሰዎችም አብይ መረጃ አቀባዮች 17 ንዑሳን ደግሞ 14 በአጠቃላይ 31 ሰዎች ለቃለመጠይቁ ተሳትፈዋል፡፡ በተጨማሪም በነውሮቹ ዙሪያ ገጠመኝ ያላቸውን የተወሰኑ ግለሰቦች የሕይወት ተሞክሮ በመጠየቅ ነው፡፡ የተሰበሰቡትም መረጃዎች፡-

- ነውር የሚባሉ ነገሮች ምን እንደሆኑና ለምን ነውር እንደተባሉ?
- ነውሮችን ያከበረ ወይም የጠበቀ የሚያገኘው ጥቅም ምን እንደሆነ?
- ነውሮች ቢጣሱ ያስከትላሉ ተብሎ የሚታሰቡን ነገሮችና ተፅእኖዎች?
- ከዚህ በፊት ሲከበሩ የነበሩ በአሁን ጊዜ የቀሩ ወይም የተለወጡ ነውሮች ምን እንደሆኑና
- ስለነውሮቹ ማህበረሰቡ የሚሰጠው ፍቺ፣ ቅጣቱና ማስፈፀሚያ ዘዴዎችን ወዘተ በምልከታ ያልተገኙ መረጃዎች የተሰበሰቡበት ነው፡፡

### 3.1.3. ቡድን ውይይት

“ቡድን ተኮር ውይይት የሚካሄደው በችግሩ ዙሪያ በቂ መረጃ ሊኖራቸው ይችላል ተብለው የሚታሰቡ ሰዎችን በመውሰድ በሚነሳው ጥያቄ ዙሪያ በቡድን በመሆን እየተወያዩ መረጃ እንዲሰጡ ለማድረግ ሲሆን፣ ከቃለመጠይቅ የሚለየው ዋናው ነጥብ በርካታ ሰዎች በአንድ ጊዜ መሳተፋቸውና ጠያቂው ግድብ የሆነ ሚና መኖሩ ነው” ያለው (2001፣197) በዚህ ጥናት ወቅት አሻሚና ጥያቄ የሚያጭሩ ጉዳዮች በመግጠማቸው ቁልፍ ሰዎችን በቡድን በማሰባሰብ እንዲወያዩ ተደርጓል፡፡

በዚህ ሁለት ቡድን ውይይት የተደረገ ሲሆን በአንደኛው 6 ሰዎች በሁለተኛው 5 ሰዎች መጋቢት 11 እና 18 ተወያይተዋል፡፡ የተነሱት ጉዳዮች ሁሉም የማህበረሰቡ ክፍል የሚቀበላቸው ወይም የማይቀበላቸው ነውሮች በመኖራቸው ምክንያቱን ለማወቅ፤ የነውሮችን ለውጥና ተከታታይነት፣ ተፈፃሚነቱን በተመለከተ፤ አሁን ካለው የአኗኗር ሁኔታ ጋር የማይጣጣሙ/ አከራካሪ በሆኑ ጉዳዮች ዙሪያ በማወያየት መረጃዎችን ለመሰብሰብ ተሞክሯል፡፡

### 3.1.4 መዛግብት ፍተሻ

“መዛግብት ተመራማሪው ስላለፈም ይሁን ወቅታዊ ጉዳይ መረጃ ለመሰብሰብ ሲነሳ ሊጠቀምባቸው የሚችሉ ጠቃሚ ነገሮች ናቸው፡፡ መዛግብት በፅሁፍ መልክ ከየቤተ-መፅሀፍቱ፣ ቤተ-መዛግብቱ ወይም ከሌሎች መሰብሰቢያ ቦታዎችና እንደ ሁኔታውም ከግለሰቦች ሊገኙ የሚችሉ የመረጃ ምንጮች ናቸው፡፡” ያለው (2001፣196) ስለዚህ በዚህ ጥናት በሰነድ ተሰብስበውና ተሰንደው የተቀመጡ የማህበረሰቡን አጠቃላይ ገፅታ መልክአምድራዊ አቀማመጥ፣ የሕዝብ ብዛት፣ መተዳደሪያ ደንቦችና ህጎች ፣ የአየር ሁኔታ፣ የሚመረቱ ነገሮች፣ አካባቢው ተለይቶ የሚታወቅባቸውን ነገሮች ከጨንቻ ወረዳ አስተዳደር ፅ/ቤት በመጠየቅ የተገኙ መፅሄቶችና በራሪ ወረቀቶች በአካባቢው እና በርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ የተካሄዱ ጥናቶች የተዳሰሱበት ነው፡፡

## 3.2. የናሙና ዘዴ

ለዚህ ጥናት የተመረጠው የንሞና ዘዴ አላማ ተኮር ንሞና ነው፡፡ ምክንያቱም የጥናቱን አላማ መሰረት በማድረግ እና ጥናቱ ትኩረት የሚያደርግባቸውን ነጥቦች በመታገዝ የተሰበሰበበት ነው፡፡ “ናሙና ስንል በልዩ ልዩ ምክንያቶች የተነሳ የጥናቱን አካላይ አባላት በሙሉ በመውሰድ

በጥናታችን ተሳታፊ ለማድረግ ሳንችል ስንቀር ወይም ማሳተፍ አስፈላጊ ሳይሆን ሲቀር ነገር ግን አጠቃላዩን ብንወስድ ልናገኝ እንችላለን ብለን የምናስበውን መረጃ ሊሰጡን የሚችሉ ሰዎችን ስርዓታዊና ተጠየቃዊ መንገድ በመከተል መርጠን በጥናታችን እንዲካተቱና መረጃ እንዲሰጡን የምናደርጋቸው የጥናቱ አካላይ ውሱን ክፍል ናቸው፡፡" ያለው(2001፣123)

በመሆኑም የጥናቱ ተሳታፊዎች የማህበረሰቡ የሀገር ሽማግሌዎችና ሌሎች የማህበረሰቡን ህግና ደንብ ጠንቅቀው የሚያውቁ የማህበረሰብ ክፍሎች ለማግኘት ጥረት ተደርጓል፡፡ ከነውር ጋር በተያያዘ ገጠመኝ ያላቸውን ሰዎች ለመረጃው ማጠናከሪያነት ተካተውበታል፡፡ እነዚህ ተጠኚዎች የተመረጡት ማህበረሰቡ ያውቃሉ ጥሩ መረጃ መስጠት ይችላሉ የሚላቸውን ሰዎች በጥቆማና በአመላካች ናሙና ነው፡፡ ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ግንኙነት ያላቸውን የተለያዩ ጥናቶችና መዛግብቶችም ተካተዋል፡፡ በመረጃ ስብሰባው ወቅት በአጠቃላይ የተገኙት ነውሮች 72 ሲሆኑ በጥናቱ ውስጥ ለናሙናነት የተመረጡት 52ቱ ናቸው፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ተመሳሳይ ይዘት ያላቸውን ነውሮች በመቀነስ ከጥናቱ አላማ ጋር በቀጥታ የሚገናኙትን በመውሰድ ነው፡፡

## 3.3. የመረጃ መተንተኛ ዘዴ

የተሰበሰቡትን መረጃዎች በአይነት በአይነቱ በማደራጀት አይነታዊ/ገላጭ የመረጃ መተንተኛ ዘዴ ተግባር ላይ ውሏል፡፡ "አይነታዊ መረጃዎች በመልካቸው አብዛኛውን ጊዜ ከቁጥር ይልቅ በቃላት የሚሰበሰቡ ናቸው፡፡ ….በአንድ ውስን ቦታ ስለተከሰተ ችግር ወይም ስለሚከናወን ሂደት ጠንካራ፣ ሰፊና የዳበረ ማብራሪያ ይሰጣሉ፡፡ ከሁነቶች መከሰት ጀምሮ እስከሚቀጥለው ሂደት በቅደም ተከተል ለማብራራትና የትኛው ሁኔታ ምን ውጤት እንዳመጣ በግልፅ ለማሳየት አይነታዊ መረጃዎች ጠቃሚ ናቸው፡፡" ያለው(2001፣425) ለዚህም ገላጭ የተመረጠበት ምክንያት የተገኙትን መረጃዎች በመመርኮዝ የዶርዜን ማህበረሰብ ወግና ልማድ ባህል የሕይወት ፍልስፍና እና የነውር እሳቤያቸውን ለመተንተን እና ለመግለፅ አመቺ በመሆኑ ነው፡፡ በተጨማሪም በትንተናው ክፍል በንድፈ ሀሳብ የታገዘ ትንተና የቀረበበት ነው፡፡

# ምዕራፍ አራት

## 4. የዶርዜ ማህበረሰብ አካባቢያዊ ዳራ

የዶርዜ ህዝብ የሚገኘው በደቡብ ብ/ብ/ህ/ክልላዊ መንግስት በጋሞ ዞን በጨንቻ ወረዳ ሲሆን በጋሞ ብሔረሰብ ስር ካሉት ማህበረሰቦች መካከል አንዱ ነው። ቋንቋቸው ጋሞኛ ሲሆን ከኦሞአዊ የቋንቋ ቤተሰብ የሚመደብ ነው። አንዳንድ የማህበረሰቡ ሽማግሌዎች ዶርዜ /ኡሽቻ ዴሬ ዶርዜ/ እንደሚባል ሲጠቅሱ፤ ዶርዜ ማለት ዶሪዜ ከሚለው የብሔሩ ቋንቋ የመነጨ ሲሆን ትርጉሙም ጥሩውን ይመርጣል/ይፈልጋል ማለት ነው። ሌሎች ደግሞ ዶርዜ በአካባቢው ለሽመና ጥበብ ባለሙያዎች የተሰጠ ስያሜ ሲሆን አካባቢውም በዚሁ መጠሪያ ይታወቃል ይላሉ። ዶርዜ የከተማ አስተዳደር ጨምሮ 11 ቀበሌያት ያሉት አካባቢ ነው።

### 4.1. የመልክዓምድር አቀማመጥና የአየር ሁኔታ

የጋሞ ጎፋ ዞን በደቡብ ብ/ብ/ህ/ክልላዊ መንግስት በደቡብ ማዕከላዊ አካባቢ የሚገኝና ከክልሉ ቆዳ ስፋት 10% የሚሸፍን ነው። የአካባቢው ተፈጥሮአዊ መልክዓ ምድር ተራራማ መሬቶች የበዛበትና አብዛኛው ደጋና ወይና ደጋ የአየር ንብረት ያለው ነው። ዶርዜ ደጋማ የአየር ንብረት ያለው ነፋሻማ ሲሆን በደቡባዊ ክፍል ሞቃታማ፣ በስተደቡብ ምዕራብ በኩል የወይና ደጋ አየር ንብረት ያለበት ነው። የጋሞ ጎፋዞን ማስታወቂያና ባህል መምሪያ (2001፣1-2)

በዚህ አካባቢ እንሰት፣ ገብስ፣ ስንዴ፣ በቆሎ፣ ስራስር፣ ጥራጥሬ፣ ፍራፍሬና ቅመማ ቅመም ይመረታል። እነዚህን ጨምሮ የእንሰት ውጤቶችን (ቆጮና ቡላ) ፣አዝዕርትና አትክልት እንዲሁም ጤፍ ለምግብነት ይውላሉ። በዶርዜ አካባቢ ለሚኖር አባወራ የሽመና ስራ ትልቅ የቤተሰብ የገቢ ምንጭ ነው። (የጋሞ ጎፋዞን ማስታወቂያና ባህል መምሪያ 2001፣7) ፤ዶን ስፐርበር ፣ R.S Jackson et al1969፣7) (“the major cash income in to the area (dorze) comes from weaving”

በሀገራችን ኢትዮጵያ ለመጨረሻ ጊዜ በ1999 ዓ.ም በተካሄደ የቤትና ህዝብ ቆጠራ ውጤቶች መሰረት ከጠቅላላው የዶርዜ ህዝብ መካከል በቦታው ያሉ የዶርዜዎች ብዛት በወቅቱ 20,791 መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ። ከ62% በላይ የሚሆነው ተወላጅ በተለያዩ የሀገራችን ከተማ የሚኖር ከተሜ ነው። ማህበረሰቡ የክርስትና እምነት ተከታዮች ናቸው። (CSA 1999ec;409)

## 4.2. የመሪዎች/የአለቆች አመራረጥና ሹመት ስርዓት

### 4.2.1. ዴሙሳ (ንጉስ)

ዴሙሳ የሁሉ ታላቅ አለቃ መሪ ነው፤ ዎጋ-አዴ/ታላቅ አባት ይባላል፡፡ ከጥንት ጀምሮ ከቤተሰብ በውርስ የሚመጣ፣ ደመራ የሚለኩስ የአለቆች አለቃ ነው፡፡ ኢራ ካዎ/የዝናብ ንጉስ ተብሎም ይጠራል፡፡ ይህም በአካባቢው ዝናብ እንዲዘንብ የሚያደርግ በመሆኑ ነው ይላሉ፡፡ በአንድ ቦታ ለይቶ እንዲዘንብ ማድረግም ይችላል የሚል እምነት አላቸው፡፡ ቋሚ አለቃ ስለሆነ የሚቀየር ወይም በምርጫ የሚሾም አይደለም ሌሎች ተከታይ አለቆች ግን ሊቀየሩ ይችላል፡፡ የዴሙሳ ሚስት ከሼ ተብላ ትጠራለች፡፡ ከሼ ማለት እንደዋርካ ጥላ ሰፊ ነገር ማለት ነው፡፡ ዴሙሳው (ዋና አለቃው) ቢሞት ታላቅ ልጃቸው ይወርሳል፡፡ ልጅ ከሌለ ወንድም ወይም ወንድም ከሌለ የወንድም ልጅ ይወርሳል፡፡ የዋና አለቃው (ዴሙሳው) ልጅ በእድሜ ትንሽ ቢሆንም ህዝቡ ያከብረዋል፡፡ ህዝቡ ሀጥያት/ኀሜ ከሰራ ከፈጣሪ ለምኖ የሚያስታርቀው፣ ምህረት የሚለምነው እሱ ነው፡፡ ዴሙሳን የበደለ ሰው ነውር ነው አይለቀውም ይላሉ፡፡ ዴሙሳ ያላስታረቀውን ለዴሙሳ እንቢ ያሉ ተከሳሾች ሌላ አያስታርቃቸውም፡፡ የተመረጡ የአለቆችን ሹመት የሚያፀድቅ የሚመርቅ ነው፡፡

### 4.2.2. የአለቃ አመራረጥ

አለቃ የሚመረጠው በሁለት አይነት መንገድ ሲሆን አንደኛው በፈቃደኝነት አለቃ መሆን የፈለገ ሰው ጥያቄ ሲያቀርብና ሰውም ሲፈቅድለት ነው፡፡ ሁለተኛው በእያንዳዱ ሸንጎ ውስጥ ያሉ እንደራሴዎች/ሽማግሌዎች እከሌ አለቃ ይሁን ብለው ሲመርጡ ነው፡፡ መራጭ ሽማግሌዎች በፊት አለቃ የነበሩ፣ የእድሜ ባለፀጎች ሲሆኑ ለቀጣዩ ጊዜ እንደራሴ ሆነው ይቀመጣሉ፡፡ ለአለቅነት በማህበረሰቡ ዘንድ ደህና ባህሪ ያለው፣ ደህና ሀብት ያለው ከሌላ ዘር (ባርያ ዘር ከሚባሉት) ያልተቀላቀለ፣ ቅድመ ዘር ማንዘሩ የተጣራ/የጀግና ዘር፣ በዘሩ ባሪያ/ ፋቂ የሚባል የሌለበት፣ የማይጣላ ዘር ያለው ይመረጣል፡፡ እድሜ ማንኛውም ሰው ከወጣት ጀምሮ ይቻላል፡፡

አለቃ ሆኖ የሚመረጥ ሰው በግራው የሚለብስ ከሆነ አይመረጥም ለሀገሩ ክፉ ነገር ይደርሳል ይባላል፣ ግራን በክፉ ነገር ስለሚሳል ነው፡፡ ስለዚህ በቀኙ መልበስ አለበት፡፡ አለቃ መሆን የፈለገ ሰው ጎረቤት ሰብስቦ አብልቶ አጠጥቶ አለቃ መሆን እፈልጋለው ይላል፡፡ ያኔ የአካባቢው ሰው ጋረቶ ጋረቶ( ይቅናህ ይቅናህ) እያሉ ይመርቁታል፡፡

### 4.2.3. የአለቃ ሹመት

ከሹመት ስርዓቱ በፊት ቅድመ ዝግጅት ስላለው እስከ ሶስት ቀን ሱሪ አይታጠቅም፤ በ3ተኛው ሱሪውን ለብሶ ቀን በድቡሻ (በአደባባይ) ይወጡና በእንደራሴዎች ፊት ሱሪውን እንዲያወልቅ ይደረግና ሽርጥ ይለብሳል። ብቅል ተፈጭቶ፣ ተቦክቶ ይጨበጥና ያደርቁታል፣ ያንን ይሰብራል በዚህ ጊዜ ማሌ ወጥሬስ (ጭብጡን ሰበረ) ከተባለ አለቃ መሆኑ ይታወቃል። ከዚያም ለዴሙሳው( ንጉስ/ዋና አለቃ) ያሳውቃሉ ወደ ቤቱ ሙሉ ጠላ ብር ይዘው ይሄዱና እግሩን ይስሙታል በኋላ ይመርቃቸዋል። ሁለተኛ አለቃ ወይ ራሱ ይመርጣል አልያም ህዝቡ እንዲመርጥ ይደረጋል። እኔም ኡዱዋ (ሁለተኛ አለቃ) ገባለው የሚል ካለም ይመረጣል። ማታ ዴሙሳው/ዋና አለቃው ወደ አንደኛው አለቃ ቤት ሄዶ ድግስ እየበላ፣ እየተጨፈረ ያመሻል።

በንጋቱ አለቃው ጋሻና ጦር በሬ ምግብና ጠላ ይዘው ከሚስቱ ጋር ይወስዳሉ። ወደ ሚሰበሰቡበት ቦታ (ጨሬ) ይጓዛል። በሬው ታርዶ ከተባለ በኋላ ወደ መጨራ(ደመራ የሚከናወንበት ሜዳ) ሄደው የቀድሞ አለቆች ገዳቹ ጥሩ ነበር በሉ ይሄንን ተቀበሉና መርቁ ይባላል። ተመራርቀው ይሸኛሉ አዲሱን ይቀበላሉ። አለቅነቱን እስከሚሽር ድረስ ሱሪ አይለብስም ሽርጥ ነው የሚታጠቀው /የሽርጡ ስም አሰራ ይበላል/ ከላይ የሚለብሱት በሰማያዊ ጥለት በሱፍ ክር የተሰራ ጋቢ /ቁቤ/ ይለብሳሉ። ገና አፈላ ከቡልኮ በታች ከጋቢ ከፍ ያለ መጠን ያለው ከላይ ይለብሳል። ሴቶች ቁቤ (ጋቢ) ይለብሳሉ ከታች ተነስቶ እላይ ድረስ የሚታጠቁት ነው።

የተመረጡት አለቆች እስከ ስድስት ወር ገበያ አይወጡም በሰፈሩ ውስጥ ይዘዋወራሉ። ገበያ የሚወጡት እንደራሴዎች ሲፈቅዱ ነው። ሁለቱም አለቆች ከሚስቶቻቸው ጋር በማር የተዘጋጀ ጠላ (ቦርዴ) ይዘው ወደገበያ ይወጣሉ። አለቃው ሲወጣ በአንገቱ ላይ ከከብት ጭራ እና ከሰጎን ላባ የተሰራ ጉቼ ለብሶ ይወጣል። ገበያ ሲወጡ እየተፎከረ ሽለላ እያቀረቡ መንግስት ሲገባ እንደሚቀበሉት ህዝቡ እልል እያለ ይቀበላል። መጀመሪያ ሚወጣበት ገበያ ሶፌ ጋዬ(ሶፌ ገበያ) ይባላል። የሁለቱም ሚስቶች ጠላውን/ቦርዴ በአንድ እቃ አብረው ይጠጣሉ፤ ይህም ሶፌ ይባላል። ሶፌ ገበያ ከወጡ በኋላ ሲመለሱ የበግ ቆዳ (ዚቶ) ይለብሳሉ ሶፌ ከጨረሱ በኃላ የድንጉዝ ሱሪ ይታጠቃሉ።

አንደኛው የተመረጠው አለቃ አቱማ ይባላል፣ ሁለተኛው/ምክትሉ አለቃ ኡዱዋ/ ሁዱጋ፣ ሶስተኛው አለቃ ቢታኔ ይባላል፡፡ የአለቃው ሚስት ኢሽሬ የሚል የማዕረግ ስም ይሰጣቸውና ከሰፈሩ ስም ጋር ተያይዞ ትጠራለች፡፡ የዶርዜ አመራ ቀበሌ አመራ-ኢሽሬ፣ የዶርዜ አይራ ቀበሌ አይራ-ኢሽሬ፣ የዶርዜ ሂርጾ ቀበሌ ከሆነ ሂርጾ-ኢሽሬ፣ የዶርዜ ሀይዞ ከሆነ ዶርዜ-ኢሽሬ ወ.ዘ.ተ ይጠራሉ፡፡ አለቃው ከአመራ ቀበሌ ከሆነ ቂሶ ይባላል፡፡ ቀበሌያቸው ቤተክርስቲያን አቅራቢያ ስለሆነ  አሰያየሙ ከቤተ ክርስቲያ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ሁሉም ቀበሌዎች በየራሳቸው ሁለት አለቃ ይኖራቸዋል፡፡

በአካባቢው ፀብ ቢነሳ ነገሩን ለማብረድ በአለቃው ስም ከያዟቸው ነገሩ ይቆማል፡፡ ለምሳሌ አቱማ አመት፣ ኡዱዋ አመት…በማለት ፀቡ ይበርዳል፡፡ በህግ አምላክ እንደማለት ነው፡፡ በኋላ ወደ አለቃው ቤት በመሄድ እርቅ ይፈፅማሉ፡፡ መህላ ሲምሉ በአለቃው ስም ከሆነ እውነት ነው ማለት ነው፡፡ (ቃለ መጠይቅ አቶ አስፋው ሶሬ 30/7/11)

### 4.2.4. የአለቃ ዋና አገልግሎት (ስራ)

- ዶርዜዎች የሚሰበሰቡበት ፍርድ የሚሰጥበት ዋና ቦታው ዶርዜ ላካ ይባላል፡፡ በዚህ ቦታና ሌሎች መሰብሰቢያ ቦታዎች ላይ ህዝብ በወጣበት በተሰበሰበበት ጊዜ ይመርቃሉ፣ ያስታርቃሉ፣ ፍርድ ይሰጣሉ፡፡
- ከዴሙሳው ጋር በመሆን ህዝቡን ይመራሉ፣
- ሁለቱም አለቆች ለየብቻ የሚያርዱት ቦታ አላቸው በየቦታቸው እርድ ይፈፅማሉ፣ ማንኛውም ሽምግልና ስርአት የሚፈፀመው በአለቃው ነው
- አቱማው በየፌርማታው (ሚዓ) ያርዳል፡፡ አንዱ ባረደበት ሌላኛው አያርድም፤ ሁለቱም በጋራ የሚያርዱበት የጋራ ቦታ አላቸው፡፡
- አቱማ አመት(መህላ ነው) በአንደኛ አለቃ ስም ከማሉ በሁለቱም አለቃ ፊት ይዳኛሉ፡፡ ኡዱዋ አመት (መህላ በሁለተኛው አለቃ ይዳኛሉ)

### 4.2.5. የአለቃ አቀያየርና የስልጣን ሽረት

አለቃ የሚቀየረው በነበረው ቆይታ የሰራው ስራና የገጠሙ ነገሮች ታይተው ሲሆን ጥሩ ከሰራ በሱ ዘመን መጥፎ ነገር ካልገጠመው ጥሩ ገድ ካለው ይቆያል ይላሉ፡፡ አስከ 7 አመት ይቆያል አለቃው እራሱ እኔን ደክሞኛል ሽኙኝ ቀይሩኝ ብሎ ህዝቡን ይጠይቃል፡፡ ያኔ ያሰናብቱታል፣

የተመረጠው አለቃ ገዱ ጥሩ ካልሆነ መጥፎ ነገር ከገጠመ መሀን ከበዛ፣ ድርቅና ረሀብ ከተከሰተ ወዲያው ያሰናብቱታል፡፡ (ቃለ መጠይቅ አንዛ አለሙ 2/8/11)

ድሮ በህዝቡ መሀል ወረርሽኝ በሽታ ከመጣ በምን ምክንያት ነው የመጣው ብለው በአዋቂ ቤት ይጠይቃሉ፡፡ በህዝቡ ላይ የመጣ መቅሰፍት ነውር ነው ከተባለ እንዲመለስ ህዝቡ ብር ያዋጣና ለአለቃው ይሰጣል፡፡ አለቃው የመጣውን መቅሰፍት ለመመለስ በግ ገዝቶ በየማረፊያ ቦታ መሰብሰቢያ ቦታ (ሚፃ) ሄዶ ከህዝቤ ላይ ልቀቅ ወደ መጣህበት ሂድ ብሎ ካረደ በሽታው ከአካባቢው ይወጣል፡፡ በግቢያቸውና መንገድ ላይ የህፃን ልጅ አይነ ምድር ካልታየ ሚስት ካልወለደች ምን ሰርቼ ነው ልጅ የጠፋው ብሎ አዋቂ ቤት ይጠይቃል፡፡ በግ አርደህ እቤቴ የገባው ክፉ ነገር ይውጣ ብለህ ደሙን አፍስስ ይላል፡፡ ያንን ካደረገ በኋላ ልጅም ይወለዳል፡፡ አሁን ግን አዋቂ ቤት መሄድ ቀርቷል ቤተክርስቲያን ስለተስፋፋ ሄደው ፈጣሪ ይቅር ይበለን በማለት ይፀልያሉ፡፡ (ቃለ መጠይቅ ገርቦ ገብሬ 2/8/11)

## 4.3. የጋብቻ አፈፃፀም

በዶርዜዎች ዘንድ ጋብቻ በሁለት መንገድ ሊፈፀም ይችላል፡፡ ተጋቢዎቹ ሳይተዋወቁ ወይም ቀድመው የተዋወቁ ሲሆን ነው፡፡ በዘር ተመሳሳይ የሆነ መጋባት አይቻልም ለጋብቻ ዘር ይቆጠራል፡፡ ለጋብቻ ስርአት ልጅቷና ልጁ የሚተዋወቁ ከሆነ ከተስማሙ በኋላ ልጁ ለአባትየው የእከሌን ልጅ ወድጃለሁ ሽማግሌ ላክ ይለዋል፡፡ አባትየው ሽማግሌ (ላዛንሳ) ጠርተው ሙሉ ጠላ ይዘው ይሄዳሉ፡፡ ሲሄዱ ቤተሰቦቿ ጋ ላምና በሬ ለመለዋወጥ ነው የመጣነው ይላሉ ይህ መግባቢያ ዘዴ ነው፡፡

የማይተዋወቁ ከሆነ የሁለቱም ቤተሰቦች በሽምግልና ተስማምተው ይጨርሳሉ፡፡ በሌላ ቀን የተጫጩ ሙሽሮች በርቀት የሚተያዩበት ገበያ ይወጣሉ፤ ይህ ኢንግጫ ጋዩ ይባላል፡፡ በምትዳርበት ቀን ወደ ጎረቤት እቃ እንድታመጣ ይልኳታል፡፡ በምትወጣበት ጊዜ የወንዱ ጓደኞች/ሚዜዎች ጠልፈው እየጨፈሩ ይወስዷታል፡፡ እንድትለምድ እስከ ወር ድረስ በሙሽራ ቤት ለብቻቸው በባሏ ቤተሰብ እየተቀለቡ ይቆያሉ፡፡

ሙሽሪት ወር ሙሉ በባሏ ቤተሰብ ቤት ተቀልባ አምራ የባሏ ቤተሰብና እሷ ሆነው በሬ ታርዶ አንዱ ጎን ንቅል ተሸክመው ወደ ሴቷ ቤት ይሄዳሉ፡፡ በልተው ጠጥተው ከጨፈሩ በኋላ ወደ ቤታቸው ይመለሳሉ፡፡

በሌላ ጊዜ በድጋሚ ከወር በኂላ የእሷም የእሱም ቤተሰብ ሙሉ ቤተሰብ ገበያ (ሶፌ ጋዬ) ይገናኛሉ፡፡ የባሏ ቤተሰቦች እህቶቹ/አክስቶቹ እሷን ቅቤ ይቀቧታል፤ በዛው አጋጣሚ ሙሉ ቤተሰብ ይተዋወቃል ጠላ አስረው ይጠጣሉ፤ የሚያመጡት የባሏ ቤተሰቦች ናቸው፡፡ የባል ዘመድ ሆና የልጅቷን ልብስ ጥሎሽ የምትወስድ አለች ሚነሳ ትባላለች፡፡ ጥሎሽ ከተሰጠ በኂላ አባቷ ቡልኮ፣ እናቷ ጋቢ ይሰጣሉ፡፡ የእሷ ቤተሰቦች ለባልየው ቡልኮ ለእሷ ደግሞ ጋቢ ይሰጣሉ፡፡ የባሏ አክስት ቅቤ ከቀባቻት በኂላ ገበያውን ከባሏና ከሚዜዎቻቸው ጋር 3 ጊዜ ይዞራሉ፡፡

አባት የሚሰጡት የሚጠጣ ማር፤ እናት ቅንጩ ሰርታ ታቀርባለች የሁለቱም ምግብና መጠጥ ካጫ ይባላል፡፡ ዮሻ በአንገት የሚለበስ ከወፍራም ጨሌ የተሰራ ነው ዘመዶቹ ያለብሷታል፡፡ ሶፌ ጋዬ ገበያ ትወጣለች መጀመሪያ ገበያ ከወጣች በኂላ ሰፈሩን ሰውን መቀላቀል ትችላለች፡፡ ፓሻ ከኂላ ያለ ትልቁ የበሬ ስጋ ሲሆን አንዱን ጎን ባልየው ለቤተሰቦቿ በወሩ ይዞ ይሄዳል፡፡ አብረው ከበሉ ከጠጡ በኂላ የሰርጉ ስርአት ያልቃል፡፡ ከዚያ በኂላ ወደ ቤተሰቦቿ ቤት መምጣትና ገበያ መውጣት ትችላለች፡፡ (አቶ አስፋው ሶሬ 30/7/11)

# ምዕራፍ አምስት

# የመረጃ ትንተና

## 5.1. የዶርዜ ማህበረሰብ የነውር አይነቶችና ምክንያቶቻቸው

ነውር እንደየ ማህበረሰቡ ባህል እሴት ታሪክ አስተሳሰብና አመለካከት የተለያየ መሆኑን በቀደሙት ምዕራፎች ተጠቅሷል፡፡ ነውር በማህበረሰቡ ቋንቋ በጋሞኛ ጎሜ ይሉታል፡፡ ትርጉሙ የተከለከለ ነገር፣ ሀጥያት፣ ክፉ ስራ ማለት ነው፡፡

በመረጃ ስብሰባ ወቅት የተገኙት ነውሮች ዘርፈ ብዙ በመሆናቸው በአይነት ለመለየት አስቸጋሪ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ስለዚህ ለትንተናው አመቺ ይሆን ዘንድ ከያዙት መልዕክት አንፃር ለመመደብ ተሞክሯል፡፡ ስለሆነም በዚህ ምዕራፍ ስር የተካተቱት የነውር አይነቶች ይዘታቸውን መሰረት በማድረግ የቀረቡ ናቸው፡፡

### 5.1.1. ክብርን ከማስጠበቅ አንፃር የሚገለጹ ነውሮች

በዶርዜ ማህበረሰብ ዘንድ ክብርን ማስጠበቅ አንዱ መተዳደሪያ ደንባቸው ነው፡፡ በዚህም እናትና አባትን፣ ታላላቆችን፣ የሀገር ሽማግሌዎችን፣ መሪዎችን፣ የተከበሩ ቦታዎችን ወዘተ ክብር ይገባቸዋል ተብለው ለሚታሰቡ ነገሮች ደንቦችንና ህጎችን ያወጣሉ፡፡ ወላጆች የቤተሰብ አስተዳዳሪና ልጆች እንዲፈጠሩ ምክንያት በመሆናቸው፣ ከወላጅ ቀጥሎ በእድሜ ታላቅ የሆኑ ከሚሰጣቸው ቦታ አንፃር እንደየ እድሜ ቅደም ተከተላቸው ያላቸውን ሀላፊነት እንዲጠበቅላቸው ሲባል ነው፡፡ የጎሳ መሪዎች /የአካባቢው አለቆች/ የአካባቢው አስተዳዳሪ ስለሆኑ ትልቅ ቦታና ክብር ይሰጣቸዋል፡፡ እነሱ በሚያዙት መንገድ መታዘዝ፣ ለእነሱ አክብሮት መስጠት፣ ለእነሱ የተፈቀደውን ድርጊት ሌሎች አለማድረግ ናቸው፡፡ እነዚህን መጣስ ስልጣን እንደመጋፋት እንደመናቅ ይቆጠራል፤ ቢራገሙም ይደርሳል የሚል እምነት አላቸው፡፡

ከሚከበሩ ቦታዎች ጋር በተያያዘ ደግሞ ሀይማኖታዊ ስርዓት የሚከወንባቸው በመሆናቸው ለሀይማኖቱና ለክብረ በአሉ ክብር ለመስጠት ሲባል ክልከላዎች ይወጣሉ፡፡ የሚወጡት ህጎችም የማህበረሰቡን ባህልና እሴት ታሪክ አኗኗር መሰረት ያደረጉ በመሆናቸው እነዚህን ማክበርና መጠበቅ ማስጠበቅ የግድ በመሆኑ መጣስ እንደነውር ይቆጠራል፡፡ ለቅጣትም ይዳርጋል፡፡

አንዳንድ ደንቦች በራሳቸው ነውር በመሆንም የሚያገለግሉ ናቸው፡፡ በዚህ ስር የሚጠቀሱት ደንቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

1. **አባት በህይወት እያለ ልጅ እርድ አይፈፅም**

አባት የቤቱ አባወራ አስተዳዳሪ በመሆኑ በህይወት እስካለ ድረስ ለእሱ የተፈቀደውን ነገር ልጆች ማድረግ አይችሉም፡፡ “አባት ንጉስ ነው” የሚል አባባል አላቸው፡፡ አባት ቢሞት እንኳን ታላቅ ወንድ ልጅ እንደ አባት ይቆጠራል ስለዚህ የአባቱን ተግባራት ማከናወን ይችላል፡፡ ይህ የነውር አይነት በቤት ውስጥ ለተለያዩ ፕሮግራሞች በሚታረዱ በሬ፣ በግና ፍየል የሚመለከት ነው፡፡ ይህም ከአባት በስተቀር እነዚህን ማረድ ፈፅሞ ክልክል በመሆኑ እንደነውር ይቆጠራል፡፡ ነውር የሆነበት ምክንያት የአባትና የእናታቸውን እድሜ ያሳጥራሉ ይባላል፡፡ ታላቅን እናትና አባትን፣ እንዲያከብሩ ነው ይላሉ፡፡ ልጅ ነውሩን ከጣሰ ቤተሰቡ ላይ በአባቱ ለይ ሞትን ጠራ ስለሚባል አባቱ ያዝንበታል ይረግሙታል፡፡ በስራ ምክንያት የተራራቁ ከሆነ በሌላ ሰው ያሳርዳል ወይም ከአባቱ ፈቃድ ይሰጠውና ማረድ ይችላል፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዘው የሚጠቀሱ ነውሮች አባት እያለ ልጅ እጣን ማጨስ ፣ እናት እያለች ሴት ልጅ ጠላ ውስጥ ብቅል አትጨምርም የሚሉት ናቸው፡፡ እናት የቤቱ እማወራ አስተዳዳሪ ስሆነች እሷም የራሷ የቤት ውስጥ ሀላፊነት አለባት፡፡ ለእሷም የእናትነቷ ክብር እንዳይጣስ፣ በየሄዱበት ቦታ ባህላቸውን እሴቱን ጠብቀው እንዲቆዩ ሲሆን ልጆቻቸው በተራቸው ወላጆች ስለሚሆኑ የቤተሰብን ሀላፊነት ከስሩ ከመሰረቱ እንዲያውቁ ነው፡፡ ወደ ከተማ ለስራ ሲሄዱ ባሉበት ቦታ ሆነው ባህልና ወጉን ጠብቀው እንዲቆዩ፣ ልጆች እናትና አባት እያሉ ሁሉንም ነገር የሚያደርጉ ከሆነ ቤተሰባቸውን ይረሳሉ፣ አያከብሩም ስለሚባል በየሄዱበት ቦታ ቤተሰባቸውን እንዲያስታውሱ እንዲያከብሩ ነው፡፡

2. **አባት እያለ ልጅ ደመራ አይለኩስም**

በማህበረሰቡ ዘንድ በሀይማኖትም በባህልም ከሚከበሩ በአላት መካከል የመስቀል በአል አንዱ ነው፡፡ ዘመን መለወጫቸው ስለሆነም ከሌሎች በአላት በተለየ መልኩ አመቱን በሙሉ ለዚህ በአል በደንብ ይዘጋጁበታል፡፡ ለእርድ ከብቶችን በማድለብ፣ ከእንሰት ቆጮና ቡላ፣ ቅቤ፣ ለደመራ የሚሆን ችቦ፣ የሚለብሱትን ቡልኮና ጋቢ ወዘተ ለበአሉ የሚያስፈልጉ ነገሮችን ያዘጋጃሉ፡፡ በዚህ በአል ላይ በዋነኝነት የደመራ ስነስርዓት የሚከወንበት በመሆኑ እያንዳንዱ አባወራ ከየቤቱ ችቦ እየለኮሰ ወደ አደባባይ ይዘው ይሄዳሉ፡፡ ይህንን ስነስርአት ማከናወን

የሚችሉት ከሀገር ሽማግሌዎች በመቀጠል ሌሎች አባወራዎች ይቀበላሉ። ነገር ግን አባት በህይወት ሳለ ልጅ ከቤት ችቦ ለኩሶ ማውጣት ነውር ነው።

ነውር የሆነበት ምክንያት ችቦውን ያወጣው ልጅ እድሉ አይቀናውም አባቱን አላከበረም ይባላል። አባት ብቻ ነው መለኮስ የሚችለው አባት በሕይወት ከሌለ ታላቅ ወንድ ልጃቸው ችቦ ማውጣት ይችላል። እንዲሁም ሴት ችቦውን ከነካች ቱና/ርኩስ ነው ይባላል ስለዚህ ሌላ ችቦ ይወጣል።

የኔ ገጠመኝ፡- የመስቀል ደመራ እለት አባቴ ስራ ነበር። ከዚያም ወንድሜ ችቦውን ለኩሶ ወደ ደመራ አወጣ። በማግስቱ አባቴ ይህን ሲሰማ በጣም ተናደደ፣ ተቀየመው፣ አዘነበት፤ ከዚያ በኋላ ስራ አልቀናም ብሎት ብዙ ተንከራተተ። በሌላ ጊዜ አባቴ እኔ አዝኜብህ ነው ያልቀናህ ስለዚህ ቤተሰብ ይሰብሰብ አለ። ሁላችንም በተሰበሰብንበት ወንድሜም ይቅርታ ጠይቆ፤ አባቴም የተቀየምኩትን ነገር ፈትቻለው ይቅር ብያለው ተባብለው ታረቁ። ከዚያ በኋላ ብዙም ሳይቆይ ስራ አገኙ። በመሆኑም ይህን ደንብ መተላለፍ ነውር ሲሆን ባጠፋው ግለሰብ ላይም የሚደርስበት ጉዳት እንዳለ ማወቅ ይቻላል።

3. **ለአቅመ አዳምና ለአቅመ ሄዋን ያልደረሰ ልጅ ማሳ ገብቶ እሸት አይቆርጥም**

ይህ ደግሞ በእድሜ ለጋ የሆኑ ልጆች ወላጆቻቸው ወይም ታላላቆቻቸው ሳይፈቅዱ መንካት የሌለባቸውን ነገር ለማመልከት ነው። ምክንያቱም ይቀሰፋሉ፣ ቤተሰብ አላከበሩም ይባላል። እንዲሁም ከልጅነታቸው ጀምሮ ቤተሰብ ያልፈቀደውን ነገር የሚነኩ ከሆነ ስርቆት ይለምዳሉ ለታላቅ ታዛዥ አይሆኑም ስለሚባል ነው። ነውሩ ከተጣሰ በአካባቢው የሚገኙ እንስሳት (ለምሳሌ እባብ) ይተናኮሏቸዋል ። ገጠመኝ፡-

> አባቴ የሰፈሩ አለቃ ነበር ይፈራል። ድሮ ልጅ እያለን ማሳውን ይጠብቃሉ የሚባሉት (ስማቸውን በውል አይጠሩም) በልብ የሚሳቡና የጫካ አውሬ ናቸው። እናም እናትና አባታችን ቡና ለመጠጣት ጎረቤት ሲሄዱ እኔና ታናሽ እህቴ ተደብቀን የበቆሎ እሸት ለመቁረጥ ሄድን። እኔ ቆሜ እየጠበኳት እሷ እሸቱን ስትቆርጥ ባለችበት ቦታ እባብ ተጠመጠመባት፤ ከዚያም ደንግጬ አባቴን ጠራሁት በጣም ተናዶ ወደ ማሳው ገባና ከመሬት አፈር አንስቶ ልጆቹ ምንም አያውቁም እኔ ነኝ ጥፋተኛ እሷን ልቀቃት ብሎ በሁለት እጃቸው አፈሩን ይዞ እያለ ለመነው፤ ከዚያም እባቡ ከእህቴ ላይ ወርዶ የአባቴ እጁ ላይ መጣና

አፈሩን ላስ አድርጎ ወደ መሬት ገባ፡፡ እኛም በሰላም ወደ ቤት ተመለስን፡፡ አሁን ግን ከእባብ ጋር የተያያዘ ይህ አይነት ነገር የለም በቤተክርስቲያን ስለተከለከለ አሁን ቀርቷል፡፡ አቶ ደንበሌ(ቃለ መጠይቅ 2/8/11)

ስለዚህ ከልጅነታቸው ጀምሮ ታላቅን ቤተሰብን ማህበረሰብን እንዲያከብሩና ደንብና ህጉን እንዲያውቁ ማድረጊያ ዘዴ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ይህንንም በተለያዩ መገልገያ ነገሮች ማሳያነት ያስተምሯቸዋል፡፡

4. **ላም ወልዳ ወተቷን መጀመሪያ አባት ሳይቀምስ ልጆች መጠጣት**

የዶርዜ ማህበረሰብ የገቢ ምንጭ ከሆኑት መካከል የከብት ርባታ ሲሆን ከነሱ በሚያገኟቸው ግብአቶችም አጠቃቀም ዙሪያ ነውሮች አሉ፡፡ በመጀመሪያ በሚታለብ ወተት እና በሚወጣው ቅቤ አባወራው ከቀመሰ በኋላ ሌሎች የቤተሰብ አባላት መጠቀም ይጀምራሉ፡፡ እንዲሁም ላም እንደወለደች የልጅ ሚስት አታልብም፡፡ የቤተሰቡ መጀመሪያ እናትና አባት ስለሆኑ በቤት ውስጥ የሚገኙ ለምግብነት የሚውሉ ነገሮች መጀመሪያ ወላጆች ይቀምሳሉ፡፡ የወላጅና የልጆችን ማህበራዊ ደረጃን ቅደም ተከተሉን ለማስጠበቅ ሲባል ነው፡፡

እነዚህን መተላለፍ ነውር ነው፡፡ ምክንያቱ ለእናትና አባት ለታላቅ ቅድሚያ እንዲሰጡ እንዲያከብሩ ነው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ እህል ከማሳ ሲገባ አባትና እናት ሳይቀምሱ ሌሎች መጠቀም መተላለፍ ነውር እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡

5. **ወንድ ልጅ በአባቱ አልጋ ላይ ከሚስቱ ጋር መተኛት**

በዶርዜ ማህበረሰብ ዘንድ የአባወራ አልጋ ላይ ማንኛውም ሰው መጥቶ መተኛት አይችልም፡፡ በተለይ ትዳር የመሰረተ ልጅ መቀመጥም ሆነ መተኛት አይፈቀድለትም፡፡ ይህን አቶ አስፋው እንደገለፁልኝ ከሆነ “የአባት አልጋ እኮ ክቡር ነው ማንም እንደፈለገው የሚተኛበት አይደለም፡፡ ደግሞ ትዳር የመሰረተ ልጅ ራሱ በቤቱ አባወራ ስለሆነ ካገባ በኋላ ቤተሰብ ሊጠይቅ ሲመጣ ለብቻ የሚተኛበት መኝታ ወይም የሙሽራ ቤት ይዘጋጅለታል፤ በዚያ ማረፍ ነው፡፡ ሁለተኛው ምክንያት እሱ የተወለደበት አልጋ በመሆኑ ከሚስቱ ጋር እንዳይተኛ ስለሚከለከል ነው” ይላሉ፡፡ አቶ አበራም ይህን ሀሳብ ይደግፋሉ፡፡

ምክንያቱም ትዳሩ አይባረክለትም፣ ልጆቹ የተባረኩ አይሆኑም፣ አባታቸውን የሚያከብሩ አይደሉም ይባላል፡፡ እንዲሁም አግብቶ የወጣ የልጃቸው ልብስ  በአባቱ አልጋ ላይ

አይቀመጥም፡፡ ነውሩ ከተጣሰ ከቤተሰቡ ይቀያየማል አባቱ ያዝንበታል፡፡ በዚህ ነውር ምክንያት ቤተሰቡን እንዲያከብር ማሳወቂያ ነው፡፡ በተጨማሪም ያገባች ሴት ከወለደች በአባቷ አልጋ ላይ አትታረስም፡፡ ለዚህ ምክንያቱ እናቷ የታረሰችበት በመሆኑና የአባቷን ክብር ይነጥቃል ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ ገጠመኝ፡-

> አንድ ጎረቤታችን ወንድ ልጅ ወልዳ በአባቷ ቤት ነበር የታረሰችው፡፡ ሁሉም ሰው እቤት ውስጥ በመሆኗ እያዘኑ ነበር፡፡ አባቷም ልጃቸውን የት እጥላታለሁ ብለው ተቀበሏት በኋላ ግን ልጁ በተወለደ በአመቱ አባቷ ሞቱ፡፡ ከዚያ በኋላ ቤተሰብም ማህበረሰቡብ በአባቷ ቤት ወንድ ልጅ ስለታረሰችና ደሟ ስለፈሰሰ ነው እያሉ ምክንያቱን ያቀርባሉ፡፡ (አልማዝ 3/4/11)

ይሁን እንጂ በአሁን ጊዜ ይህ ነገር እየቀነሰ የመጣ ሲሆን ብዙሀኑ በሀኪም ቤት ስለሚወልዱ በቤታቸው ሳምንት ከቆዩ በኋላ ወደ ቤተሰባቸው ቤት በመሄድ መታረስ በመጀመራቸው ነው፡፡ ስለሆነም አንዲት ሴት ስትወልድ ሃኪም ቤት ሁሉን ህክምና አጠናቃ ስለምትመለስ በቤተሰቧ ቤት ለብቻዋ መኝታ ተዘጋጅቶላት የተቀረውን እንክብካቤ ማግኘት እንደምትችል ይገልፃሉ፡፡

### 6. በጎተራ የተቀመጠ እህል መጀመሪያ አባውራ ሳይቀምስ ሌላ አይቀምስም

እህል ተወቅቶ ወደቤት ከገባ በጎተራ የሚቀመጠውን ለቤት የሚሆነውን ለይቶ ያስቀምጣል፡፡ በጎተራ የተቀመጠውን ሌላ ሰው ከፍቶ መውሰድ አይችልም፡፡ ለቤት የሚሆነውን ቀንሶ ነው የሚሰጠው፡፡ ወ/ሮ ከረሴ ከንዶ እና ወ/ሮ ዲላዬ እንደነገሩኝ በማህበረሰቡ ዘንድ እህል ተወቅቶ እንደገባ ለቅምሻ ያህል አባወራው በድንጋይ ወፍጮ ፈጭቶ እንድትጨርሰው ለባለቤቱ ይሰጣል፡፡ ተፈጭቶ ካለቀ በኋላ የተፈጨው ቅምሻው ያርሾ ወይም ዜሮ ይባላል፡፡ ቅንጨ አርገው ወይም በሶ ይሰራና ቀምሶ መጀመሪያ በኮባ ቅጠል ጠቅልለው ምሰሶው አጠገብ፣ የቤቱ በር ላይ ሁለት ቦታ፣ መሀል በር ላይ፣ የውጭ በር ላይ ሁለት ቦታ ያስቀምጣሉ፡፡ አስቀምጦ ከተመለሰ በኋላ ልጆች አንስተው መብላት ይችላሉ፡፡ ይህ ሁሉ የሚሆነው ሰው ሳይቀምስ ነው፡፡ ፈጣሪ ቤተሰቤን በሰላም አስቀምጥልኝ ክፉ እንዳይነካኝ እያለ እየመረቀ ነው፡፡ ምክንያተም ከበፊት ጀምሮ የነበረ ደንብ ነው መጀመሪያ መሬቱን ደጁን ካቀመሰን በኋላ ነው እኛ መብላት ያለብን ይላሉ፡፡ ስለሆነም ከጥንት የወረሱትን ደንቦቻቸውን መጠበቂያ ዘዴ አድርገው ይጠቀሙበታል ማለት ነው፡፡

ገጠመኝ፡- እህል ተወቅቶ ሲገባ ለቅምሻ አዘጋጅቼ ለባለቤቴ እንዲፈጭ ሰጥቼው ፈጭቶ ካዘጋጀ በኋላ በየቦታው ሳያስቀምጥ ቆይ መጣሁ ብሎ ወደ ጓደኞቹ ሄደ፡፡ እኔ የተዘጋጀውን ሳታስተካክል ለምን ትሄዳለህ ብዬ ስጠይቀው መጣሁ ብሎ ወጣ፡፡ ሳይጨርስ በመሄዱ በጣም ቅር አለኝ አባውራ የሚያደርገውን እኔ ማድረግ አልችልም፡፡ ከዛ በኋላ ማታ ሲመጣ ለምን ተውክ ስለው "ሰው ስጠይቅ ታላቅ ሚስት/የመጀመሪያ ሚስት ናት አዲስ የገባ እህል መስጠት የምትችለው ስላሉኝ ነው የተውኩት" አለኝ ታዲያ ለምን ጀምረህ ተውከው ብዬ ተናደድኩ፡፡ ከዛ በሌላ ቀን ወደ ከተማ (አዲስ አበባ) ሲሄድ መኪናው ተገልብጦ አደጋ ደረሰበት፡፡ ሁለት ጥርሶቹ ወለቁ የጀመረውን ትቶ ስለሄደ ተቀይሜው ስለነበረ ነው አደጋው የደረሰው፡፡ በኋላ ስልክ ደውሎ ይቅርታ ጠየቀኝ፡፡ (ወ/ሮ ዲላዬ 27/7/11)

ስለዚህ ሙሉ የሆነ ነገር የተሞላ ጠላ፣ ቦርዴ ከታሰረ በኋላ በጎተራ የተቀመጠ እህል ባል እያለ ሚስት እና ልጆች አይከፍቱም፤ ቅርጫ ከመጣ በኋላ ባል ሳይቀምስ ሌላ ሰው መጠቀም አይችልም ማለት ነው፡፡ እንዲሁም በቤት ውስጥ ማንኛውም የተሰራ ነገር እሸት በቆሎ እየጠበሱ ሳለ አባት/ታላቅ ሳይቀምስ ሌሎች መቅመስ አይችሉም፡፡ ምክንያቱም ታላቅን አላከበረም ይታመማል፣ እውነቱን ካላወጣ እድሉ አይቀናውም ይላሉ፡፡

## 7. ዱሙሳ/ ንጉስ በሚያርፍበትና በሚያርድበት ቦታ መቀመጥ፣ ተክል መትከል፣ ከብት ማረድ

ዱሙሳ በአካባቢያዊ ዳራው ላይ እንደተገለጸው የአካባቢው ንጉስና ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ንጉስ ነው፡፡ ለሱ ካላቸው ቦታና ክብር አንፃር እሱ በሚያርፍበት ቦታ ሁሉ ሌላ ሰው መቀመጥ ለማንኛውም ድርጊት ማከናወን አይችልም፡፡ የንጉሱ ርግማን ይደርሳል ስለሚባል አይደፍሩትም፡፡ ይህ ነውር የሆነበት ምክንያት "ለንጉስ ለመታዘዝ ለማክበር ነው የአካባቢው መሪ ስለሆነ የግድ መታዘዝ ያስፈልጋል እሺ ለሽምግልና በሚቀመጥበት ቦታና እርድ በሚፈፀምበት መሆን እራሱ የንጉሱን ስልጣን መጋፋት ነው፡፡ ነውር ነው…" (አቶ ጋሞ 8/7/11 ቃመ)

በመሆኑም ለንጉሱ ክብር ለመስጠት ነውሩን መጠበቅ ያስፈልጋል ይህን ነውር መተላለፍ አልተቀበሉም፣ አላከበሩትም፣ ንቀውታ ማለት ነው፡፡ ተዳፍሮኛል፣ ንቆኛል፣ ብሎ ይረግመዋ፣ እድሉ አይቀናም ይላሉ፡፡ እንዲሁም በተመረጡና በተከበሩ ቦታዎች ለከብት ችካል መትከል በግ/ከብት ማረድ አይቻልም፡፡ አለቃውን አልተቀበሉትም፣ አላከበሩትም፣ ንቀውታል ተብሎ

ይታመናል። ስለዚህ ተዳፍሮኛል ንቆኛል ብሎ ይረግመዋል እድሉ አይቀናም ይላሉ። ይህን ካደረጉ ሙሉ ቦርዴ ይዘው ይሄዱና አለቃውን ይቅርታ ይጠይቃሉ።

### 8. በቤት ውስጥ የታሰረን እቃ ለልጅ ሚስት መፍታት/መውሰድ አትችልም።

በማኅበረሰቡ ዘንድ ለምግብነት ለመጠጥ ከሚውሉ ነገሮች መካከል ቆጮ/ቡላ እና ቦርዴ ናቸው። እነዚህ እናት አዘጋጅታ አስራ ወይም ከድና ታስቀምጣለች። ይህንን ለምግብነት የደረሰ እለት የሚከፈትበት ቀን ሲደርስ መጀመሪያ ከፍታ የምታወጣው እናት ነች።

ከእንሰት የሚዘጋጀው ቆጮና ቡላ ታስሮ ነፍሳት፣ ቆሻሻ እንዲሁም ነፋስ እንዳይገባበት በኮባ ቅጠልና በማዳበሪያ ተጠቅልሎ ይቀመጣል። እስኪብላላ ድረስ እስከ ሁለት ሳምንት ወይም ወር ሊቀመጥ ይችላል። ከዚህ ላይ ለቤት የሚሰራውን ቀንሶ  ካልሰጠች በስተቀር ከፍቶ መውሰድ ክልክልነው።

እንዲሁም በቤት ውስጥ እሳት ለማንደድ ለምድጃ ትንሽ ጉድጓድ ይቆፈራል ይህን ጉልቻ በማስቀመጥ ጉድጓዱ እሳት/ ፍም እና አመዱ የሚጠራቀምበት ሆኖ ያገለግላ። በመሆኑም ይህን ለምድጃነት የሚያገለግለውን ጉድጓድ የምታዘጋጀው እናት ብቻ ናት ልጆች መቆፈር አይችሉም በመሆኑም ይህን ለምድጃነት የሚያገለግለውን ጉድጓድ የምታዘጋጀው እናት ብቻ ናት ልጆች መቆፈር አይችሉም በመሆኑም ይህን የነውር አይነት ከተጣሰ እናታቸውን አላከበሩም ንቀዋል ይባላል። ስለዚህ ወላጅን ማክበር እንዲማሩ ይከለከላሉ። በተጨማሪም ላም እንደወለደች እናት ወይም አባት ካለቧት በኋላ ሌሎች ያልባሉ ከወላጅ ቀድመው ልጆች ማለብ አይችሉም።

### 9. በሰው እግር ላይ ዘሎ ማለፍ መሻገር

ይህ ነውር የሆነበት ምክንያት ሰው በተቀመጠበት እግራቸውን ተሻግሮ ማለፍ እንደ ንቀት ይቆጠራል ወንድ የሴትን ሴትም የወንድን ማለት አትችልም። ወንድ የሚስቱን እግር ማለፍ ይችላል ይህም አንድ ናቸው። ስለዚህ መናናቅ እንዳይኖር በማለት እንደ ነውር ይቆጠራል።

## 5.1.2. በሌላ ወገን ላይ ከሚደርሱ ነገሮች አንጻር

በዚህ ርዕስ የተገለፁት ነውሮች በሁለተኛ ወገን ላይ አደጋ ወይም ክፉ ነገር ማድረስ ሲደረግ እያዩ ዝም ማለት ፈፅሞ የተከለከለ ነው እንደ ምሳሌ ያህል የሚከተሉትን ነውሮች እንመልከት በደረሰው ግለሰብ ላይ እራሱ መልሶ የሚደርስበት ክስተት፣ ቅጣትም ስላለ ነው።

1. በሰው ላይ ድንገተኛ አደጋ ሲደርስ እያዩ ዝም ማለት

የሰው ልጅ በህይወት ሳለ የተለያዩ የተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ አደጋዎች ሊደርሱበት ይችላል፡፡ በዚህ ወቅት የሚደርሰውን ነገር በቦታው ከተገኙ መታደግ ወይም ሌሎች ሰዎችን በመጥራት አደጋ የደረሰበትን ሰው ማትረፍ ያስፈልጋል፡፡ ይህንን አለማድረግ እንደ ነውር ይቆጠራል፡፡ በሰውና በንብረት ላይ የእሳት ወይም የጎርፍ አደጋ ሲደርስ እያየ ዝም ያለ ሰው አይኑ ይታወራል አንደበቱ ይዘጋል ይባላል፡፡ ያደረገ ካለም ለሽማግሌዎች በመግለጽ ይቅርታ ይጠይቃል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ገጠመኝ ነግረውኛል፡፡

> ጎርፍ መቶ ሰው ሲወስድ የሆነ ሰውዬ ሬሳውን አይቶ ዝም ብሎ ነበር፡፡ ጎረቤትና የአካባቢው ሰው ፍለጋ ወጣና አጥቶ ተመለሰ፡፡ ሰውየው አይቶ ዝም ስላለ አንደበቱ ተዘጋ በማግስቱ ህዝቡ እንደገና ፍለጋ ወጡ ከነሱ መሀል ያየው ሰውዬ መናገር አይችልም ነበር፡፡ ለምን እንደማይናገር ሲጠይቁት በምልክት ሬሳ እንዳየ ተናገረ በኋላ አንደበቱ ተፈታ ለምን አይተህ ዝም አልክ ሲሉት ‹ሬሳ ያየ ሰው በየአመቱ ቦታው ላይ ፍየል ማረድ አለበት ስለዚህ እኔ በየአመቱ የማረድ አቅም የለኝም ስለዚህ ነው› ከዚያም ሰዎች ፍየል አመጡና ሲያርዱ ሬሳው ከተደበቀበት ትንሽ ርቆ ወጣ ከህዝቡ ጋር አብረው ወሰዱ፡፡ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ሰውየው በቦታው ላይ በየአመቱ ፍየል ያርዳል፡፡ ይህም በድጋሚ ሌላ ሰው እዳይወስድ ነው፡፡ (አቶ ተሾመ 17/7/11)

ከዚህ የምንረዳው አደጋ ሲደርስ እያዩ ዝም ማለት በራሱ በማህበረሰቡ ዘንድ ለቅጣት እንደሚዳርግና በግለሰቡ ላይ የሚደርሰውን ነገር ታሳቢ በማድረግ ደንቡን መተላለፍ እንደማይገባ ያስጠነቅቃል፡፡ ይሁንና አደጋውን ያየ ሰው ቦታውን ለማመልከት በተለይ የጎርፍ አደጋ ሲሆን በቦታው ላይ ፍየል የማረድ አቅም የሌለው ሰው ዝምታን ይመርጣ፡፡ በመሆኑም በራሱ የሚደርሰውን ቅጣት አስቦ ለሰዎች በማሳወቅ ከጭንቀቱ ነፃ መውጣት ይችላ፡፡ ይህን አስመልክቶ ገጠመኙን ያጫወቱኝ አቶ ተሾመ “የሚቀርበውን መስዋዕት የማቅረብ አቅም ከሌለው አደጋው ለደረሰበት ቤተሰብ በማሳወቅ ከራሳቸው ወይም ጎረቤት ገንዘብ በማዋጣት የሚታረደው እንዲገዛለት ሊያግዙት ይችላሉ፡፡ ከዚያ በኋላ በየአመቱ የሚደረገውን እዛው ለህዝቡ ማድረግ እንደማይችል እንዳይጠብቁ በመናገር መገልገል ይችላል፡፡ ግን በምን አገባኝ ዝም ማለት ነውር ነው ማሳወ ያስፈልጋል” ብለውኛል፡፡ ስለሆነም አይቶም ሰምቶም በደፈናው መተው አይገባም ማለት ነው፡፡

## 2. ለሰው ክፉ መስራት

ሰዎች እንደ ተፈጥሯቸው የተለያየ ባህሪ ይኖራቸዋል፡፡ አንዳንዱ ደግና ሩህሩህ ጥሩ የሚባል ሲሆን ሌላው ክፉ የሚባሉ በሰው ላይ ክፋት የሚያደርጉ ይኖራሉ፡፡ ይህ በተፈጥሮም ሆነ በሰው ሰራሽ ምክንያትም ሊፈጠር ይችላል፡፡ በራሱ ላይ በሰው ምክንያት ጉዳት የደረሰበት መልሶ ለመጉዳት የሚያስብ እንዳለ ሁሉ ለፈጣሪ ሰጥቶ የሚተውም ሰው አለ፡፡ ስለሆነም በዶርዜዎች ዘንድ በሰው ላይ ክፋት ማድረስ አንዱ የነውር አይነት ነው፡፡ እነዚህም በልባቸው ክፋት አስበው የውሸት መመስከር፣ በሰው ላይ ግፍ ማድረስ /መበደል፣ መግደል/ እያወቁ አላቅም ማለት፣ ያዩትን መካድ፣ የሰው ንብረት ማውደም፣ ወዘተ መሰል ተግባራትን መፈፀም እንደ ነውር ይቆጠራል፡፡ ከማህበረሰቡም መገለል ሊያደርስ ይችላል፡፡ ለምሳሌ አንድ ገጠመኝ እንመልከት፡-

> ድሮ ልጅ እያለሁ አባቴ ሁልጊዜ ይበድለኛል፣ ያለምክንያት ይገርፈኝ ነበር፡፡ የሚያግዘኝ እናቴም አጠገቤ ስለሌለች ከሰው ጋር ተጣልቶ መቶም ይመታኛል፡፡ ከዚያ እኔ አለቀስኩ ለሱ አለቀስኩ ምናርጌ ነው ብየ አዘንኩበት ያ ነገር ለሱ ጎሜ/ነውር ሆኖበት ክፉ ነገር ታየው አቃዠው፡፡ ከዚያ ትልቅ ሰው ቤት ሄዶ ሲጠይቅ ልጅህ ባንተ ላይ አልቅሳለች አዝናብሃለች ሂድና ፍታ አሉት፡፡ ከዛ አባቱ ለልጁ ይቅርታ ስለማይጠይቅ ማር አመጣ እየቀመሰ በጣቱ ፍንጥር እያደረገ 3 ጊዜ ለእግዚአብሔር ይቅርታ የበደልኩትን አለ፡፡ ቀጥሎም በግ ገዝቶ ሁለተኛ አልነካትም አልገርፋትም በዚህ ይለፍ ብሎ አረደ ኃላም ቅዥቱ ለቀቀው፡፡ (ወ/ሮ አበራሽ 20/7/11)

በገጠመኙ የተገለጸው ነገር ነውሩን መጣስ በራሱ እንቅፋት እንደሚያነሳ እንደሚያስጨንቅ ማወቅ ይቻላል፡፡ "ሰውላይ ክፋት ማድረግ እኮ ፈጣሪም አይወደውም "ጉሜይ ጎሜና ይሪ አሲ ዴሬ ኦጌስ" (ትንሽ ሳቅ) አቶ አስፋው /ቃለ መጠይቅ 20/7/2011/፡፡ እኚህ ተጠኚ አማርኛውንም ጋሞኛውንም ቋንቋ መናገር ስለሚችሉ በሁለቱም ነው የገለፁት፡፡ የተሰመረበት ጋሞኛ ቋንቋ ሲሆን አባባል ነው፡፡ ትርጉሙም "ነውር አያስነውርም ብሎ ሰው ህዝብ ይጨርሳል" ማለት ነው ብለውኛል፡፡ ይህም አንዳንድ ሰዎች ነውር የተባለውን ነገር አይደርስም በማለት በንቀት እንደሚተላለፉት ነው፡፡ በመሆኑም በፈጣሪ ዘንድም በሰውም ዘንድ የሚጠላውን ነገር መፈፀም እንደማይገባ የሚገለፅበት የነውር አይነት ነው፡፡

### 3. ስርቆት

መስረቅ በሕግም እንደሚያስጠይቅ ይታወቃል፡፡ በመፅሐፍ ቅዱስም "አትስረቅ ዘፀ" የሚል ሕግ አለ፡፡ በተጠኚው ማህበረሰብ የሰው ከብት መስረቅ፣ የሠው ድንበር መግፋት፣ ከጎረቤት ወይም ከሌላ ቦታ ማሳ የበቀለ ነገር መስረቅ፣ የሠው ገንዘብ ወስዶ ማስቀረት እንደ ስርቆት ይቆጠራል፡፡ የራስን ገንዘብ ጭምር ይዞ ይሄዳ፡፡ ሀጥያት ነው ይላሉ፡፡ በሰረቀው ሰው ላይ እንዲሁም በልጆችም ሆነ ጉዳት ይደርስበትማል ይታመማሉ፣ ማንኛውም ነገር አይቀናቸውም ይባላል፡፡ ያጠፋው ሰው ካላመነ ወይም ከካደ ለፈጣሪ ሰጥተው ይተዋሉ፡፡ ለሚደርሰው ቅጣት ያንን ጥፋት ምክንያት ያቀርባሉ፡፡ ለምሳሌ፡- ቢታመም የሰው ድንበር ስለገፋሁ ነው በማለት ያስባል፡፡

በአካባቢው ነበርና እባስ አይጠፋም በመሆኑም የድንበር ጠባቂ ናት/ው የሚል እምነት አላቸው፡፡ ስለሆነም ሌላሰው በድብ የሰውን ንብረት ቢነካ ይተናኮሉታል፡፡ ያስደነግጡታል፡፡ ከባለቤቱ ደጃፍ ላይ ቁጭ ካለ የሆነ ነውር ተሰርቷል ማለት ነው እስኪ ይህን ገጠመኝ እንይ፡፡

> አንድ ሴትዮ ከሰው ሴት ጎመን ሰርቃ እቤቷ ውስጥ ለመክተፍ ስትገልጠው ጎመኑ ላይ እባብ ተገኘ፡፡ ከዛን ምን አርገሽ ነው እባብ የተገኘው ስትባል ከእከሌ ቤት ሰርቄ ነው አለች፡፡ በይ ሂጅና ይቅርታ ጠይቂ ያለበለዚያ እባቡ አይሄድም አሏት ከዛም ሄዳ ይቅርታ ስትጠይቅ እባቡ ሄደ፡፡ (አቶ ተሾመ 10/7/11)

በመሆኑም ይህን አይነት ጥፋት መፈጸም ነውር እንደሆነና መጠንቀቅ እንደሚገባ ይገልፃሉ፡፡

### 4. ቤተሰብ የሌላቸው ብቸኛ የሆኑ ሰዎች ላይ ግፍ ማድረስ

በዚህ ደግሞ ልጆች የሌላቸው፣ አቅመ ደካሞችን፣ ዘመድ በቅርብ የሌላቸውን ሰዎች ንብረታቸውን በጉልበት መውሰድ፣ ማግለል፣ ማንቋሸሽ ነውር ነው፡፡ ምክንያቱም ፍፉን በሰራው ሰው ላይ እስከ ልጆቹ ድረስ ክፉ ነገር ያሰርሳል ሞትን ያቀርባል፡፡ ይባላል ወ/ሮ ደቦቴ ደቃ የተባሉ ተጠኚ ሲገልጹልኝ

> ግፍ መስራት ሰይጣን እንዲከተለን ያደርጋል እንደውም በእኔ ላይ የደረሰውን ልንገርሽ ድሮ አባቴ በጣም ሀይለኛ ነበር፡፡ እናም አንድ ሴትዮ ብቸኛ ነበረች ከአባቴ ጋር የሩቅ ዝምድና ነው ያላቸው፡፡ የእሷን መሬት ከእራሱ ጋር አንድ

ላይ ወስዶ ያርስ ነበር። ምርቱን ግን ለራሱ ነው የሚወስደው። ሴትየዋ ስትሞት የሚቀርቧት ዘመዶች እያሉ ንብረቷ ለእኔ ነው የሚገባው ብሎ ወሰደ። ከትንሽ ጊዜ በኋላ አባቴ ታመመና አዋቂ ቤት ሄደው ሲጠይቁ የሰራው ነውር እንዳለ ተነገረው። በኋላም ሽማግሌ ሰብስቦ ከሁሉም ጥፋተኛ እኔ ነኝ ብሎ ይቅርታ ጠየቀ። ነገር ግን የመሬቱ ባለቤት ሴትዮዋ ስለሞተች ከእርሷ ጋር እርቅ ስላልፈፀመ ህመሙ አልተወውም። ትንሽ ቆይቶ ሞተ ሴትዮዋ በህይወት ብትኖር ኖሮ ከእርሷ ጋር ይታረቅና ከህመሙም ይድን ነበር አሉኝ። (ቃለመጠይቅ ወ/ሮ ደቦቴ ደቃ 18/7/11) በመሆኑም ይህን ነውር መተላለፍ እስከሞት እንደሚያደርስ ማወቅ ይቻላል።

### 5.1.3. ዝምድናን ከመጠበቅ ጋር ተያያዥ ነውሮች

ዝምድናን መጠበቅም ሆነ ሌሎች እንዳይሳሳቱ ማስጠበቅ እንደሚያስፈልግ ይገልጻሉ። በደም የሚገናኝ ዝምድናን እንዲሁም ከሌላ ቤተሰብ ጋር የሚፈጠር ዝምድናን መስመሩን እንዳይስት የሚጠነቀቁበት ነው። በዚህ የሚገለጹ ነውሮች፦

1) **በቤተዘመድ መሀል ጋብቻ**

ለጋብቻ እስከ ሰባት ቤት ይቆጠራል፣ ከህይማኖት ጋርም ያያይዙታል። በተለይ በወንዱ በኩል ትኩረት ይደረግበታል። ለዚህም ዘር በወንድ በኩል ይቆጠራ ስለሚባል ነው። ነውሩ ከተጣሰ ሞት ያመጣል፣ ትዳሩ የተሳካ አይሆንም፣ መናናቅ ይመጣል፣ አይከባበሩም ይባላል።

> ገጠመኝ፦ "አንዲት ልጅ ከአባቷ የክርስትና ልጅ ወለደች። ከዚያም ዘመድ መሆናቸው ሲረጋገጥ ቤተሰብና ቄስ መጥቶ ድጋሚ እንዳይወልዱ ተከለከሉ። ሌላ ገጠመኝ እህትና ወንድም በግብር (በወሲብ) ተገናኝተው ልጁ ከተወለደ በኋላ ሞተ በኋላ ወንድምና እህት በተከታታይ ሞቱ ይህም በቤተዘመድ መሀል ጋብቻ ስለማይፈቅድ ነበር።" (አቶ ተሾመ 17/7/11)

ይህ አይነት ነውር ከተጣሰ እንዲለያዩ ልጅ እንዳይወልዱ ይደረጋል። በአጋጣሚ የተወለደ ልጅ ካለ ሌላ እንዳይደገም በቄስ ይገዘታሉ።

2) ዴገላ (ፋቂዎች) ከሚባሉት ጋር ጋብቻ

ማህበረሰቡ ባለበት አካባቢ ፈቂ የሚባሉ ህብረተሰቦች አሉ፡፡ እነዚህ በከብት የቆዳ ስራ ላይ የተሰማሩ ቆዳ የሚፍቁ፣ ከሌላው ህብረተሰብ በስራቸውም በአመጋገባቸው የተለዩ ስለሆኑ ነው፡፡ ለዚህም የሞተ ከብት ስለሚበሉ፣ የሚጣሉ የማይበሉ የእንስሳት አካላትን ስለሚጠቀመው በዝምድና እንደቀላቀሏቸው አይፈልጉም፡፡ ነውር የሆነበት ምክንያት በፊት ባርያ ሆነው የተገዙ ስለሆኑ ነው ይህን ነገር የሚጠቀሙት ስለዚህ በጋብቻ  መቀላቀል የራስን ዘር ማርከስ ማቆሸሽ ነው ይላሉ፡፡ በመሆኑም የራስን ዘር ንፅህና ለመጠበቅ ሲባል ይህን ይጠብቃሉ፡፡

"ፋቂ የሚባሉት በአኗኗራቸው ስለሚለዩ ነው ከነሱ ጋር የተጋባ ከሰፈሩ ይገለላል፡፡ የሞተ ከብት የሚያነሱት እነሱ ናቸው ሰው ይጠየፋቸዋል፡፡ በእድርም አይቀላቀሉም፡፡ አሁን ግን አንዳንድ የሚጋቡ አሉ ሆኖም ይናቃሉ" (አቶ ጌሮ ጌምቤሮ/25/7/11 ቃለ መጠይቅ)

እነዚህ ህብረተሰቦች በአኗኗራቸው የተለዩ በመሆናቸው እንዲቀላቀሏቸው ስለማይፈልጉ እንደ ነውር ይቆጥሩታል፡፡ ባሁን ጊዜ ይህ ነገር እየቀነሰ መምጣቱን ሲጠቁሙ ያገቡትን በማህበራዊ አጋጣሚዎች በነገር ወጋ በማድረግ በመተረብ ያሾፍባቸዋል፡፡ የሚሰጣቸው ክብርና ቦታ ይቀንሳል ያ ነገር እንዳይደርስባቸው ሲሉ የማይጋቡም አሉ፡፡

3) በቤተሰብ መሀል ዝሙት መፈፀም

ይህ ወንዶች የዘመድ ልጅ ከደፈሩ የታላቁን ሚስት ታናሽ ከደፈረ ይታመማሉ፣ ይቀሰፋሉ፤ ቤተ ዘመድ አስቀይሟል ንቋል ይባላል፡፡ ነውሩን የጣሰ  በግ ይገዛና ሽማግሌ ሰብስቦ ይቅርታ ጠይቆ ካልታረቀ ቁጣው ከቤት አይወጣም ተብሎ ይታመናል፡፡ በመሆኑም ከቁጣ ለመዳን ጥፋቱን አሳውቆ ይቅር እንዲሉት የሚጠበቅበትን ቅጣት ይሰጣል ሽማግሌዎችም ፈጣሪም ይቅር ይበልህ ብለው በምርቃት ይሸኙታል፡፡

እንዲሁም ልጅ እናቱን ቢደፍር በባህሉ መሰረት ይከሰሳል፡፡ በኮርች (የተቦረቦረ እንጨት) ውስጥ እንዲሾልክ ይደረጋል፤ ከዛን ከቤተሰቡና ከማህበረሰቡ ይገለላል፣ ከቤተሰብ ጋር መገናኘት አይችልም፡፡ ኮርች ወይም በእንጨት መሀል እንዲያልፍ መደረጉ አልፎ መሄዱን ደንብ መጣሱን ለማመልከት ነው፡፡ ከቤተ ዘመድ ተቋርጧል (ዱዓ) ይባላል፡፡ ከወንዝ ማዶ እንዲሻገር ዳግመኛ እንዳይመለስ ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከማህበረሰቡ ያሰናብቱታል፡፡ ተመልሶ መምጣት አይቻልም፡፡

### 5.1.4. የትዳርን ሕልውና ከማስጠበቅ ጋር ተያያዥ ነውሮች

የቤተሰብ መሰረቱ ትዳር ነው፡፡ ቤተሰብ ማህበረሰብን ማህበረሰብ ሀገርን ይመሰርታል፡፡ ይህን ሰንሰለት ከስሩ የጠነቀረ የፀና እንዲሆን የተለያዩ ደንቦች ይወጡበታል፡፡ ምክንያቱም በታማኝነት የተሞላ ሕይወት እንዲሆን ከትዳር ለሚገኙ ልጆችም ተምሳሌት እንዲሆኑ ታሳቢ በማድረግ ነው፡፡ በዚህ ስር ከሚጠቀሱት ነውሮች መካከል

1) ከትዳር አጋር ውጭ መማገጥ

ባልና ሚስት ተወስነው እንዲኖሩ ከትዳር አጋር ውጭ በድብቅ ግንኙነት እንዳይኖር ለመከላከል ሲሉ ደንቦችን ያወጣሉ፡፡ ስለዚህ ትዳራቸውን ለማስጠበቅ በንፅህና የተሞላ እንዲሆን የግድ ይታዘዛሉ፡፡ ይህን በመጽሀፍ ቅዱስ "አታመንዝር" የሚለውን ሕግ ታሳቢ በማድረግ ሀጢያት ነው ይላሉ፡፡ የፈፀመ ሰው ይታመማል፣ ልጆች ከብቶች ይሞቱበታል ይባላል፡፡ ስለዚህ በአንዳንድ ሰዎች ላይ የደረሰው ጉዳት በማየት እንዲጠበቁ ያደርጋቸዋል ማለት ነው፡፡

የዶርዜ ማህበረሰብ ተወላጆች አብዛኞቹ በሌላ ከተማ የሚኖሩ ሲሆኑ ወንዶች ሚስቶቻቸው ገጠር ያለውን ንብረት እንዲጠብቁ በማድረግ ወደ ከተማ ይሄዳሉ፡፡ የሚገናኙትም ቆይተው ለበአል ወይም ለቅሶና ሌሎች ቤተሰባዊ ጉዳይ ሲገጥማቸው ነው፡፡ ተራርቀው የሚኖሩ ስለሚሆን ወንዱም በሄደበት ሴቷም ባለችበት ለትዳራቸው ታማኝ እንዲሆኑ ለማድረግ ነው በማለት ይገልጻሉ፡፡

ሚስት ገጠር ሆና ባል ከሩቅ ቦታ ሲመጣ ሙሉ ጠላ፣ ቦርዴ፣ ታቀርባለች ንፁህ ከሆነ ኮርቶ ይጠጣል፡፡ ያቀረበችውን ይበላል ንፁህ ካልሆነ/ያጠፋው ነገር ካለ ሽማግሌ ይጠራና የሰው ልብስ ለብሻለው ብሎ ይነግራታል፡፡ እውነቱን ተናግሮ ሙሉ ልብስ ነጠላ፣ ቀሚስ… በግ ወዘተ ካሳ ይከፍላል፡፡ ሽማግሌዎች ይቅርታ ብለናል ብለው የቀረበውን ከፍተው ይሰጣሉ ይታረቃሉ፡፡ እሷ የማገጠች ከሆነ የሚበላ የሚጠጣውን አቅርባ ወጥታ ትሄዳለች እሱ ከበላና ከጠጣ በኋላ ለምን ወጥታ እንደሄደች በሽማግሌ ይጠይቃል፡፡ እውነቱ ከወጣ በኋላ ጠላና በግ አምጥታ ከጎረቤት ጋር ሆነው ይቅር ተባብለው ይታረቃሉ ይበላሉ ይጠጣሉ፡፡

አብሮ እየኖሩ ለማገጠ በቤተሰብ መሀል ልጅ ሲታመም፣ ከብቶች ሲታመሙ በድብቅ የሰሩትን ይናገሩና ካሳ አቅርበው ይታረቃሉ፡፡ ገጠመኝ፡- "አንድ የማውቀው ሰውዬ ነበር በሚስቱ ላይ ማግጦ ስለደበቀ ልጆቹ በተከታታይ ሞቱበት አባት በሰራው ነው፡፡ እናትና አባት በሰሩት በደል በቤተሰብ ላይ አደጋ ቁጣ ይደርሳል፡፡" (አቶ አበራ 9/7/11)

**2. ሴት አግብታ ከወጣች በኋላ ከአማቷ ቤት ማንኛውም እቃ ወደ እናቷ ቤት መውሰድ**

ይህም ወደ ቤተሰቦቿ ለመጠየቅ በምትሄድበት ወቅት የአማቷን ንብረት አንድም ይዛ መሄድ የለበትም፡፡ ነውር የሆነበት ምክያት ተጠላለፈ፣ በቤት ውስጥ የሆነ ነገር ይከሰታል ስለሚሉ እንዲመለስ ያዛሉ፡፡ እንዲሁም ባልና ሚስት ከተጋቡ በኋላ ከብርድ ልብስ /ቡልኮ/ ውጪ የግል ልብስ ለብሶ መተኛት፣ ልጃቸውን መሀላቸው ማስተኛት አይቻልም ትዳራቸው አይቆይም ይለያያሉ ይባላል፡፡

**3. ሚስት ወይም ባል ተጣልተው ሳለ ከሌላ ሰው ጋር ከተገናኙ በኋላ ደግመው ሲታረቁ በግ ካልታረደ ነውር ነው፡፡**

በዚህ ነውር ላይ የተገለጸው በተለይ ሚስት ተጣልታ ከወጣች በኋላ ሌላ ግንኙት አድርጋ ኋላ ከባሏ ጋር ስትታረቅ በመሀል ላይ ለተፈጠረው ክስተት ማርከሻ ነው በማለት በግ ይታረዳል፡፡ ስለሆነም ወደየቤታቸው ሲመለሱ ሙሉ ጠላ/ ቦርዴ በግ ይዞ መምጣት እርቅ ስነ ስርዓቱን ማስኬጃ አድርገው ይጠቀሙታል፡፡ ይህ ካልሆነ ግን ትታመማለች ባልም ችግር ይገጥመዋል፡፡

እንዲሁም ሚስት ተጣልታ ከወጣች በኋላ እስከ ደመራ /መስከረም 16/ ካልተመለሰች ወደ ቤቷ መመለስ አትችልም፡፡ የተሸጠ መሬትም ከደመራ በኋላ አይመለስም፡፡ ምክንያቱም መስከረም 16 የማህበረሰቡ የዘመን መለወጫ ስለሆነ ያለፈውን ዘመን እንደተውን የሄደውንም በዛው መቅረት አለበት ይላሉ፡፡

**4. በባልና ሚስት አልጋ ላይ ሌላ ሰው መተኛት**

በአባወራ አልጋ ላይ ከባለቤቱና ከልጆቻቸው ውጭ ሌላ ሰው እንዲተኛ አይፈቀድም፡፡ የባልና ሚስቱን ክብር ተጋፍቷል፣ ቦታቸው ተደፍሯል ይባላል፡፡ በመሆኑም እንግዳ ሲመጣ የሚተኛበት መኝታ በማዘጋጀት ማንኛውም ሰው በዚያ ላይ ማደር ይችላል፡፡ እንዲሁም ለመጋባት ቃል የተገባቡ እጮኛሞች ከሁለቱ አንደኛው መካድ ነውር ነው፡፡ የካደው ይሰቃያል ይባላል፡፡ ሌላ እጮኛ ለማግኘት አይቀናውም ይላሉ፡፡

### 5.1.5. ለሴቶች የሚከለከሉ ነገሮች

አንዳንድ የነውር አይነቶች ፆታን መሰረት ያደረጉ ናቸው፡፡ ለአንዱ የሚፈቅዱ ለሌላው የሚከለከሉ ሲሆኑ ከንፅህና ጋር የሚያያዙ ናቸው፡፡ እነሱም፡-

1) ሴት የወር አበባ ላይ ሆና በወላጆቿ አልጋ ላይ መተኛት

ይሄ ነውር የሆነው ንፅህናን ለማመልከት ሲሆን በእናቷ አልጋ ላይ የልጅቷ ደም እንዳይፈስ እንደ ሀጢያትም ይቆጠራል፡፡ እንዲሁም ምድጃ ላይ እና ሳር ላይ ደሟ ጠብ ካለ ከብት ሳሩን ከበላ ነውር ነው፡፡ ለእሷ ጥሩ አይደለም ትታመማለች ትቀሰፋለች ይባላል፡፡ በተወለደችበት በእናቷ አልጋ ላይ ንፁህ ሳትሆን ከተኛች አልጋው ይረክሳል ይላሉ፡፡ የሴት ወር አበባ የተጠቀሙበትን ነገር ከብቶች ከበሉት ቱና (ርኩስ) ይባላል፡፡ ካጠፋች ለእናትና ለአባቷ ይቅርታ ትጠይቃለች፡፡

ከዚህ ነውር ጋር በተመሳሳይ Selvi and Ramachandran (2012) "Socio-cultural Taboos Concerning Menstruation: A Micro Level Study in the Cuddalore District of Tamil Nadu, India" በሚል ርዕስ በህንድ የተካሄደው ጥናት ሴቶች የወር አበባ በሚያዩበት ወቅት ህፃናትን መያዝ፤ ወደ ሃይማኖታዊ ስፍራዎችም ሆነ ስርዓተ ክንውን ወደሚፈፀምባቸው ቦታዎች መሄድ፤ ከሌሎች ሰዎች ጋር የመመገቢያም ሆነ የመኝታ ቁሳቁሶችን መጋራት ወዘተ. እንደሚከለከሉ አንስተዋል፡፡ ለእነዚህና መሰል ክልከላዎች የሚሰጡ ምክንያቶችም ሴቶች የወር አበባ በሚያዩበት ወቅት ንፁህ አይደሉም ተብሎ ስለሚታመን እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ በዶርዜ ባህልም መሰረት የወር አበባ ከሃይማኖትም ሆነ ከባህል አንፃር ንፁህ ካለመሆን ጋር የሚያያዝ እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡

2) ሴት ልጅ አግብታ መልስ ሳትጠራ ወደ ቤተሰቧ መምጣት

በዚህ ማህበረሰብ ዘንድ ልጃቸውን ድረው እናትና አባት መርቀው የሚሸኙት የመልስ እለት ነው፡፡ መልስ ለመጠራትም የጫጉላ ጊዜዋን ከጨረሰች በኋላ ነው፡፡ ስለዚህ ይሄ ሂደት ሳይጠናቀቅ በመሀል ከቤቷ መውጣት አትችልም፡፡ በሌላ አካባቢ የምትኖር እና ያገባች ከሆነች ወደ አባቷ ቤት ስትመጣ ሙሉ ጠላ እና በግ ካላመጣች ነውር ነው፡፡ በባዶ እጇ ከሄደች የአባቷ መሬት አድባሩ ቅር ይለዋል፡፡ ስለዚህ የአባቷን ቤት አክብራ ይዛ መምጣት አለባት፡፡ ካልሆነ ቱና /ርኩስ ነገር/ አለ ይላሉ፡፡

ገጠመኝ፡- "እኔ ያገባሁት አዲስ አበባ ነው፡፡ ልጅ ከወለድኩ በኋላ ነው ወደ ገጠር የተመለስኩት፡፡ አባቴ ቤት ስገባ አባቴ በጣም ቅር አለው ባዶሽን ለምን መጣሽ አለኝ በሳምንቱ በአባቴ ሕልም የሚያስጨንቅ ነገር ታየው፡፡ ትልልቅ ሰዎችን /አዋቂዎችን ሲያስጠይቅ በቤቱ የጎለደ ነገር ያልተሰራ ነገር አለ አሉት፡፡ ኋላም ለእኔ ነገረኝና በግ አምጥቼ አሳረድኩኝ በእንስራ

ሙሉ ጠላ አቀረብኩለት በዚህም ቅር የተሰኘው ነገር ለቀቀው እኔንም በስርዓቱ ማናገር ጀመረ፡፡ እኔ ጊዜ አልፏል ብዬ ነበር የተዉኩት ግን አባቴን አስጨንቆት ነበር፡፡” (ወ/ሮ አበራሽ 15/8/11 ቃለ መጠይቅ)

**3) ሴት እንዳትነካ የምትከለከላቸው ነገሮችን መንካት**

ለመስቀል ደመራ የሚዘጋጅ ምሰሶ አለ፡፡ ምሰሶውን ማቆምና ደመራ መለኮስ የወንዶች ተግባር ስለሆነ በማይገባት ቦታ መገኘት አትችልም፡፡ ለቦታውም ክብር ለመስጠት ነው፡፡ ሌላው የሚከለከለው ነገር የአባወራን ጦር እና ቢላዋን አትነካም፡፡ ለአባወራው የራሱ የሆነ ቢላዋ ይዘጋጅለታል እሱም ከብት የሚያርድበትና እንሰት የሚቆርጥበት ነው፡፡ ከነካች ጦሩ ወርውሮ አይመታም/ይስታል፣ ቢላዋም አይሰራም ንቃዋለች አላከበረችም ይላሉ፡፡

## 5.1.6. ከእምነት ጋር ተያያዥ ነውሮች

**1) ባዕድ አምልኮ**

ተጠኚው ማህበረሰብ የክርስትና እምነት ተከታይ ናቸው፡፡ ስለዚህ ከሀይማኖቱ ውጪ የሆኑ ሌሎች አምልኮዎችን ማድረግ ጠንቋይ ቤት መሄድ፣ በሰው ላይ መተት መስራት ነውር ነው፡፡ ምክንያቱም መልሶ ራስን ይጎዳል፣ ክፉ ስራ ነው፣ ፈጣሪ ይቆጣል፣ ልጆቹ ይታመማሉ ይላሉ፡፡

> “በፊት የሰሩት የሚታወቀው አዋቂ ቤት እየሄዱ ነበር፡፡ ልባቸው እያወቀ ሳያውቁ ዝም ካሉ በቆይታ ብዛት በቤተሰቦቻቸው ላይ ክፉ ነገር ከደረሰ ለማወቅ ለመጠየቅ ይሄዱ ነበር፡፡ ሆኖም በእርቅ ያልተፈታ የተደበቀ ነውር ለማውጣት ካልሆነ በስተቀር ሆን ብሎ በሰው ላይ ለማስደገም ተንኮል ጠንስሶ መሄድ ክልክል ነው” በማለት ይገልጻሉ (ጌሮ ጌምቤሮ 2/8/11 ቃለ መጠይቅ)

ይህም በማወቅ ወይም ባለማወቅ ያጠፉት ነገር ካለ፣ ከቤተሰቡ መሀል አንደኛው ሰው ነውር ሰርቶ ያልተናገረ ካለ በቤት ውስጥ ችግርና፣ ህመም ሲከሰት ለምን እንደተከሰተ ለመጠየቅ ይሄዱ ነበር፡፡ በቀደመው ርዕስ ለሴቶች የሚከለከሉ ነገሮች በሁለተኛው ተራ ቁጥር ላይ የተቀመጠው ገጠመኝ ሌላ ማሳያ ይሆናል፡፡ ልጅቷ ለአባቷ ሙሉ ጠላ እና በግ ይዛ መምጣት ያለባትን ባለማምጣቷና አባቷ ቅር ስላለው በህልማቸው ያቃዣቸው ጀመረ፡፡ አዋቂዎችን ሲጠይቁ በቤታቸው የተሰራ ነገር እንዳለና አድባሩ ቅር እንዳለው ተነግሯቸዋል፡፡ ኋላም

ጠላውም ሲመጣ በግም ታርዶ ከአባቷ ጋር ስትነጋገር ጭንቀቱም ቅዠቱም እንደለቀቃቸው ትገልጻለች፡፡

ስለሆነም ልክ እንደዚህ አይነት ጉዳይ ሲገጥማቸው ነው እንጂ ለአምልኮ አስቦ ሰው ላይ ክፋት ለመስራት መሄድ ማምለክ ነውር ነው፡፡ የሄደ ካለም ማህበረሰቡ በተለያዩ ማህበራዊ አጋጣሚዎች እንዳይቀላቀሉ እንዲገለሉ ይደረጋል፡፡ በአሁኑ ወቅት ግን የተለያየ አብያተ ክርስቲያናት እየተስፋፉ ስለሆነ አዋቂ ቤት ሄዶ መጠየቅ እየቀረ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

### 2) እባብ በቤት ቀዳዳ ገብቶ በዋናው በር ከወጣ

የዶርዜዎች የቤት አሰራር ከቀርከሀ ስለሚሰራ ከቤቱ በኋላ በኩል ለከብቶች ፍግ ማውጫ እንዲሆን የተወሰነ ቀዳዳ ይተውለታል፡፡ ሆኖም በዚህ በኩል የተለያዩ እንስሳት /ምሳሌ እባብ/ እንደሚገባ ይናገራሉ፡፡ በገባበት ከወጣ ችግር የለውም በዋናው በር ሲወጣ ግን ከቤት ውስጥ ሬሳ ይወጣል ድንገተኛ አደጋ ይደርሳል ይላሉ፡፡

በዚህ ማህበረሰብ ዘንድ ነብርና እባብ እንደ መልዕክተኛ ይቆጠራሉ፡፡ በቤት ውስጥ ጥፋት አጥፍቶ የደበቀ ሰው ካለ ከሁለቱ እንስሳት አንደኛው ብቅ ይላሉ፡፡ እንዲሁም ከንብረታቸው ከማሳ ላይ የተሰረቀ ነገር ካለ ነብር ደጃፍ ላይ መጥቶ ይቀመጣል፡፡ በዚህ ጊዜ ወደ ቦታው ሄደው ይመለከታሉ ልጆች ካጠፉም አባት/እናት ይቅር ብያለው ካሉ እንስሳቱ ወደ መጡበት ይመለሳሉ፡፡ ስለዚህ የገባውም እባብ በከብቶች በር በጓሮ ማውጣት አለባቸው፡፡

በቤታቸው በጓሮ በኩል ሸንኮራ፣ በቆሎ አይጠፋም፡፡ ያን እንዳትነኩ ተብለው ሳለ ልጆች/ጎረቤት ከነካ እባቡ በሸንኮራው ላይ ተጠምጥሞ ይጮሀል፡፡ ባለቤቱ እስኪመጣ ዞር አይልም፡፡ ይህም በድሮ ጊዜ ቤተክርስቲያን ከመስፋፋቱ በፊት እባቡን ስለሚያመልኩ የሆነ ጥፋት ከተሰራ፣ በቤተሰቡ ላይ የሚመጣ አደጋ ወይም ሞት ካለ ቀጥ ብሎ ይመጣል፡፡

> ገጠመኝ፡- “ድሮ ለአባቴ ቡና እያፈላው ሳለ ቤቱ በቀርከሀ ስለሚሰራ ግድግዳው ክፍተት ስላለው በቀዳዳ እባቡ ገባ፡፡ ከዚያ አባቴ በገባበት ቀዳዳ እንዲወጣ በበር እንዳይወጣ በእንጨት ሲመልሰው አልመለስም አለው ከዚያም በያዘው እንጨት ጠቅልሎ አነሳና እደጅ አውጥቶ በድንጋይ ላይ ቀጥቅጦ ገደለው መሞቱን ሲያይ ሳር ጨመረበት፡፡ አውጥቶ የገደለው ሞቴን ሊያቀርብ ነው የመጣው ብሎ ነው፡፡ እባቡ ባይሞት ኖሮ አባቴ ቶሎ ይሞት ነበር እንደ መልእክተኛ ይቆጠራል” አለችኝ፡፡ (ቃለ መጠይቅ ወ/ሮ አበራሽ 20/7/11)

3) ለቅሶ ባለበት ቤት በግ አለማረድ

ይህ የነውር አይነት ደግሞ ሬሳ ከወጣበት ቤት በግ ካልታረደ ነውር መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ምክንያቱም የሞት ሽኘት /ሞይትሌ ገሶ) ነው ይላሉ፡፡ ይህ ካልታረደ ቤቱ አልጸዳም፣ የሞት መንፈስ አልወጣም ይባላል፡፡ እንዲሁም በለቅሶ ወቅት የተዋሱት እቃም ካለ በጉ ሳይታረድ አይመለስም፡፡ ለዚህ ምክንያቱ የሞት መንፈስ ከሁሉም ነገር ላይ መነሳት አለበት፡፡ ሞት በደም ነው የሚካሰው ተብሎ ይታሰባል፡፡ ስለዚህ የበግ ደም ካፈሰሱ በኋላ ሁሉም ነገር ይፀዳዳል፡፡ የማንፃት፣ ሀዘን የመሸኘት መንፈሱን የማስወገድ ዘዴ ነው ይላሉ፡፡ በመሆኑም በቤት ውስጥ የተከሰተን ክፉ ነገር ለመርሳት ለማራቅ በግ ማረድ እንደ መፍትሄ የሚጠቀሙበት መሆኑን ማወቅ ይቻላል፡፡ በግ ብቻ የተመረጠበት ምክንያት ከፀባዩ ጋር እና በጻድቃን ስለሚመስል ቤቱን ጥሩ ነገር እንደሚገጥመው በማሰብ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡

በተጨማሪም ሳይታረድ የሞተ ከብት፣በግ፣ፍየል መብላት ነውር ነው፡፡ በደፈናው የሞተ የሰይጣን ነው ስለሚባል አባወራ ባርኮ ሳያርድ የሞተ ስለሆነ አይነካም፤ ይቀብሩታል፡፡ ብዙ ጊዜ ከብቶች ውሀ ለመጠጣት በሄዱበት ጎርፍ ስለሚወስዳቸው የወንዙ ነው፣ መንፈሱ ነው የወሰደው የሚል እምነት አላቸው፡፡

4) ወንዝ ያደረ እቃ መውሰድ

በአካባቢው ሻዬ የሚባል ወንዝ አለ ለማንኛውም አገልግሎት ለመጠጥም፣ ለምግብም፣ ልብስ ለማጠብም፣ ውሃ ለመቅዳት ከዚህ ወንዝ ይጠቀማሉ፡፡ ስለዚህ ትልቅ ክብር ይሰጡታል፡፡ ውሀው የእግዚአብሔር ነው ሌላ የተቀመጠ ነገር የሰይጣን ነው ይላሉ፡፡ ስለሆነም ልብስ ለማጠብ ሄደው እቃ ረስተው ከመጡ፤ ሌላ ሰው ትቶት የሄደ እቃ፣ አዛባ/ኩበት ካለ መውሰድ አይቻልም፡፡ የሰው ዕቃ ካለ ሰይጣን ነው ያስቀረው በመተት የተቀመጠ ሊሆን ይችላል ተብሎ ስለሚጠረጠር እና ይዘው ከመጡ ሰይጣን ተከትሎ ይመጣል ይባላል፡፡ ስለዚህ ከውሀ በስተቀር ሌላ ነገር ማምጣት ነውር ነው፡፡ ከወንዝ ጋር ተያያዥ ገጠመኙን እንመልከት፡-

> “ቆጮ ተዘጋጅቶ ከቤት አጠገብ በጉድጓድ ይቀመጣል/እንዲብላላ ነው፡፡ የተቀመጠውን መዳበሪያ ተሸፍኖ ነፋስ እንዳይገባው ድንጋይ ይደረግበታል፡፡ እኔ ከሻዬ ወንዝ ድንጋይ አምጥቼ አስቀመጥኩኝ፡፡ የሆኑ አዋቂ ሰውዬ መጥተው የሆነ ነውር ሰርተሻል አንቺ ቤት ክፉ ነገር ይሰማኛል፡፡ ያመጣሽው ነገር ካለ አውጪ አለኝ፡፡ እኔም ትዝ ብሎኝ ከወንዝ ድንጋይ እንዳመጣሁ ተናገርኩ በይ

መልሽ ሲሉኝ ድንጋይ ተሸክሜ ወደ ወንዙ ሄጄ ይኸው ያንተን መልሻለው ብዬ ወደ ወንዙ መረወርኩት ከዛ በኂላም ቅዠቱ ለቀቃቸው፡፡" (ወ/ሮ ከረሴ ከንዶ 27/7/11)

ይህ ገጠመኝ ለሌሎች ደንቡን እንዲጠብቁ ማሳያ በመሆኑ በአቅራቢያ ያሉትም በሌላ ሰው ላይ የደረሰውን በማየት እንዲጠነቀቁ ያደርጋል፡፡

5) መብረቅ የመታውን እንጨት ከባለቤቱ ውጪ መጠቀም

በክረምት ወራት አንዳንዴ መብረቅ እንደሚመጣ ይናገራሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ትልልቅ ዛፎችን የመታ እንደሆነ ጎረቤቶች መጠቀም አይችሉም የደረሰው የመብረቅ አደጋ በራስ ንብረት ላይ ይደርሳል ተብሎ ይታመናል፡፡ ስለዚህ አያነሱትም፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ የደረሰ ገጠመኝ አንድ ወጣት ነግሮኛል፡፡

"ድሮ አያቴ ወጣት እያለ የተከለው ዛፍ ነበር በጣም ረዥም ነው እድሜውን አያቴ እስኪሞት ድረስ ነበር፡፡ በነገራችን ላይ መብረቅ በአካባቢው ከመጣ የተመታ ነገር ካለ በሰፈሩ ለቅሶ ይመጣል ይባላል፡፡ እናም አያቴም እየደከመ እየታመመ መጣ፡፡ የሆነ ቀን እሱ የተከለውን ዛፍ መብረቅ መቶት ወደቀ አያቴም በሶስተኛው ቀን ሞተ፡፡ እስካሁን ድረስ ያ የወደቀው እንጨት አልተነሳም ባለበት በስብሷል፡፡ ሴት አያቴም አቅሟ ደካማ ስለሆነ ብዙ ትኩረት አልሰጡትም እንጂ አስፈልጦ ማስነሳት ትችል ነበር፡፡" (ወጣት ሲሳይ ሰይፉ 15/8/11 ቃለ መጠይቅ)

ከዚህ የምንረዳው መብረቅን እንደ ምልክትም እንደሚያዩት ሲሆን የወደቀውንም ነገር ሌላ ሰው ለራሱ ማንሳት እንደማይችል ነው፡፡

## 5.2. የዶርዜ ማህበረሰብ ማህበራዊ ቅጣቶችና ሽልማቶች

### 5.2.1. ማህበራዊ ቅጣቶች

ማህበራዊ ልማዶች በማህበራዊ ቅጣቶች አማካይነት የሚጸኑ ናቸው (social norms are enforced through social sanctions). (Cass (2013:15) ማህበራዊ ቅጣቶች የምንላቸው ማህበረሰቡ በራሱ አመለካከትና አስተሳሰብ የቀረፃቸውን ደንቦችና ሕጎች ማስከበሪያ ዘዴዎች ናቸው፡፡ ማስተማሪያ የሚሆኑ ተግሳጾች፣ ከዛ ካለፈም ተጨባጭ የሚሆኑ ድንጋጌዎች የሚወስኑበት ነው፡፡ በተጠኚው ማህበረሰብ ዘንድ ነውር የተላለፈ ሰው ቅጣት የሚጣልበት

ያከበረ ደግሞ ሽልማት የሚያገኝበት አካሄድ ስርዓት አለው። ይህንንም እንደየ ጥፋት አይነቱ፣ ሽልማቱም ቅጣቱም ይለያያል። በማህበረሰቡ የዳኝነትና ፍርድ ስርዓት አማካኝነት ይታያሉ።

በዶርዜ ውስጥ አስራ አንድ ቀበሌዎች አሉ። በየቀበሌው የሽምግልና ስርዓትና ሸንጎ አለ በሁሉም ቀበሌ ያለው የፍርድ አሰጣጥ  አንድ ስለሆኑ በየሰፈሩ የተመረጡ የሀገር ሽማግሌዎች አሉ። ቅደም ተከተላዊ ስርዓቱም ጥፋት የሠራ ሰው መጀመሪያ በአንድ ሰፈር ሽምግልና /ጉታ/ ይዳኛል። ሁኔታው ከአንዱ ያለፈ ከሆነ ወደ ሶስት የሰፈር ሽምግልና ይታያል። የጥፋቱ አይነት ከ3ቱ ሸንጎዎች የበላይ አካል የሚፈልግ ከሆነ ወደ ጠቅላላ ጉባኤ የሚካሄድበት ፍርድ ሸንጎ (ዘጠኙ ጉታ/ሰፈር) ይላካል። በዚህ የመጨረሻው ጉባኤ የቀበሌው አጠቃላይ የሀገር ሽማግሌዎች፣ አለቆች አንድ ላይ በመሰበሰብ የሚሸመግሉበት ነው።

እንደ ቀበሌዎች ስፋትና ጥበት የሰፈር/ጉታ ሽምግልናዎች ሲኖሩ አካሄዳቸው ግን አንድ ነው። ለምሳሌ በሒርጳ ቀበሌ ያሉ ሰፈሮች /ጉታዎች/ ዞንባ፣ ጎሞራ፣ ጎንታ፣ ዜቃሴ፣ ላዌ፣ ፃፃ፣ መንዲዳ፣ በለሴ እና ፋንጎ ናቸው። ሁሉም ፍርድ ሸንጎዎች እንደ ደረጃቸው የራሳቸው ህግና ቅጣት ያላቸው ሲሆን አንዱ ከሶስቱ ሸንጎ፣ ሶስቱ ሸንጎ ከአጠቃላይ ዘጠኙ ሸንጎዎች ጋር የሚያገናኙትም የጋራ ህግና ቅጣት አላቸው። ይህ አካሄድ በፌደራል መንግስት የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት፣ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እየተባለ ቅደም ተከተላዊ ሂደቱን ጠብቆ ከሚካሄደው የፍርድ ስርዓት ጋር ተመሳሳይ ነው።

በእነዚህ ከላይ በተጠቀሱት ስርዓቶች ውስጥ የተሰየሙት፣ ሽማግሌዎች ነገሮችን አብጠርጥረው አይተው ለጥፋተኛም ቅጣቱን ለተበዳይም ካሳ እንዲያገኝ ያደርጋሉ። ከተጠቀሱት ጉታዎች መካከል በአንዱ በዞንባ ሽማግሌዎች ታይቶ ካልታዘዘ ወደ ሶስቱ /ዞንባ፣ ገሞራ እና ጎንታ/አንድነት ሸንጎ እንዲታይ ይተላለፋል። ለዚህም ሳይገዛ ቀርቶ ካስቸገረ ወደ ዘጠኙ ምልአተ ጉባኤ ይላካል። በዚህም ጥፋቱን ሳያምን ከቀረ ወይም በሌላ ጊዜም ከጥፋቱ ካልታረመ ለህጉ ካልተገዛ ከ2 እስከ 3 ወር ከአካባቢው እንዲገለል ይደረጋል። ህዝቡም ከእሱ ጋር ማህበራዊ ግንኙነቱን አያደርግም ማንኛውም አገልግሎት ላይ መሳተፍ አይችልም። ከተገለለ በኋላ ከጥፋቱ የታረመ ሰው ከሌላ አካባቢ ሽማግሌዎች ጠርቶ ወደ ሕዝቡ ይልክና ይቅርታ ጠይቆ ዳግመኛ ላለማጥፋት ቃለመሀላ ይገባል። የበደለውን ካሳ ከፍሎ ለሽማግሌዎችም ግብዣ አድርጎ መቀላቀል ይችላል።

በመሆኑም በዚህ ምዕራፍ በመጀመሪያው ክፍል የተጠቀሱትን የነውር አይነቶች እንዲከበሩና እንዲጠበቁ እንደ አይነታቸው የተለያዩ የቅጣት አይነቶች አሉ፡፡ የመጀመሪያው ቅጣት ይቅርታ መጠየቅ ሲሆን ነውር የጣሰ ሰው ጥፋቱን አምኖ ለሽማግሌዎች ለበደለው ሰው ተንበርክኮ ይቅርታ እንዲጠይቅ ይደረጋል፡፡ በወቅቱ የተፈጠሩ ነገሮችን አጢነው ዳግመኛ እንዳያጠፉ በማስጠንቀቅ በምህረት ያልፉታል፡፡

ሁለተኛው ቅጣት ሙሉ ጠላ /በእንስራ ቦርዴ/ እና በግ ይዞ መቅረብ ሲሆን ይህ በቤተሰብ ውስጥ ለሚደረግ ሽምግልና ነው፡፡ ያጎደለው ነገር ሲሆን፣ አባቱ ማድረግ የሚገባውን ነገር ልጅ ተላልፎ ካደረገ እንደ መታረቂያም ሽምግልና ማስኬጃም የሚታይ የቅጣት አይነት ነው፡፡ ለምሳሌ በሌላ ቦታ አግብታ የመጣች ልጅ ወደ አባቷ ቤት ስትሄድ ሙሉ እንስራ ጠላ እና በግ መውሰድ እንዳለባት ተጠቅሷል፡፡ ይህ ከተጣሰ ነውር ስለሆነ ሲታረቁ ቅጣቱም የቀረውን ነገር ማሟላት ማምጣት ነው፡፡ ለሌላ አይነት ጥፋት ደግሞ እንደካሳም የሚያገለግል ነው፡፡

ሶስተኛው የቅጣት አይነት ጋቢ/ ቡልኮ/ ማልበስ ነው፡፡ ይህ ቅጣት ለተበደለ የቤተሰብ አባል በተለይ እናትና አባት፣ የባል ወይም የሚስት ወላጆች የሚሰጥ ነው፡፡ ለረጅም ጊዜ ተቀያይመው የቆዩ ከሆነ ተንበርክኮ ይቅርታ ይጠይቅና ምረት ካደረጉ በኋላ ጋቢውን/ቡልኮውን/ በማልበስ ዕርቁ ይከናወናል ማለት ነው፡፡ በዚህም ላይ ግን በእንስራ ጠላ መቅረቡ አይቀርም በወቅቱ ለተሰበሰቡ ሰዎች የሚቀርብ ነው፡፡ አራተኛው የቅጣት አይነት ደግሞ የገንዘብ ቅጣት ነው፡፡ ይህ ከቤተሰብ ውጭ በጎረቤት እና አቅራቢያ ባሉ ሰዎች ላይ ወይም በሀገር ሽማግሌዎች ላይ ጥፋት ያደረሰ ሲሆን የሚጣልበት የቅጣት አይት ነው፡፡ ከቀላል ቅጣት ያልታረሙ ሲኖሩ ከ300 ሺህ ብር ጀምሮ የሚጣል ቅጣት ነው፡፡ አቅሙ ከቻለ ይከፍላል ካልቻለ ቤተዘመድ አዋጥቶ ይከፍላሉ፡፡ ከዚያ በኋላ ይታረቃል ማለት ነው፡፡

የመጨረሻው የቅጣት አይነት ከአካባቢው መገለል ሲሆን ከአንደኛ እስከ አራተኛ የተጠቀሱት የቅጣት አይነቶችን ተቀጥቶ ያልታረመ ሲሆን ከፍተኛ የተባለውን የጥፋት አይነት ያጠፋ ከሆነ ለምሳሌ ዘረኝነት የሚያራምድ፣ በቤተሰቡ በእናቱ ላይ ዝሙት የፈፀመ ከሆነ፣ በቤተዘመድ ላይ ግድያ የፈጸመና የሞከረ ከሆነ ከማሕበረሰቡ በማግለል ወደ መንግስት በፍርድ ቤት እንዲያዝ ያደርጋሉ፡፡ በተጨማሪም የመገለል ቅጣት ከዘጠኙ ጉታ /ሰፈሮች/ ሽንጎ በላይ ከሆነም የሚጣል ቅጣት ነው፡፡ እነዚህ ሁሉ ከማህበረሰቡ ሕግና ደንብ እንዳያፈነግጡ መቆጣጠሪያ ዘዴ በመሆን የሚያገለግሉ ናቸው፡፡

### 5.2.2. ማህበራዊ ሽልማቶች

ማህበራዊ ሽልማቶች የምንላቸው ለማህበራዊ ሕጎችና ደንቦች ተገዢና አክባሪ በመሆን የሚገኙ የሕሊና እርካታ እና በራስ መተማመንን የሚያጎናጽፉ ሰጦታዎች ናቸው። እነዚህ በህብረተሰቡ ዘንድ ተወዳጅነትን ፣ተአማኒነትን የሚያስገኙ ሲሆን ከባህሉና ከእሴቱ የማያፈነግጡ ነውር የሌለባቸው የሚከበሩበትና ትልቅ ቦታን የሚያሰጡ ናቸው። በአካባቢው ተመራጭነትን ከማግኘትም በላይ አለቃ በሚሸምበት ጊዜ ዕድሜው የደረሰ ከሆነ ለአለቃነት እስከመመረጥ ሊያደርስ ይችላል። ይህም አለቃ ለመሆን መሰፈርቱ ዋነኛው በስነ ምግባር የታነፀ የተመከሰረለት፣ ነገሮችን በማመዛዘን አስታራቂ መሆን የሚችል ሲሆን ነው። ስለዚህ ይህን አይነት ክብርና ቦታ ለማግኘት ማህበረሰቡ የሚመራባቸውን ሕግና ደንብ ነውሮች መጠበቅና ማክበር ለልጆቹም ማወቅና ማስተማር ያስፈልጋል ማለት ነው።

## 5.3. የነውሮች ፋይዳ እና ጉዳት በዶርዜ ማህበረሰብ

### 5.3.1. የነውሮች ፋይዳ

በተለያዩ መንገዶች የተሰበሰቡት መረጃዎች በየአይነቱ በማደራጀት ተስማሚ ከሆኑ ንደፈ ሀሳቦች አንጻር መተንተን እንዳለባቸው creswell (2007;161) ይገልጻሉ። በመሆኑም ለጥናቱ በተመረጡት ንድፈ ሀሳቦች አንጻር እንደሚከተለው ቀርበዋል።

ፎክሎር የተለያዩ ተግባራት አሉት bascom (1954፡346) ፎክሎርና ትርጉሙ ከሰው ጋር የተሳሰሩና ፎክሎር የማስተማር፣ የማዝናናት፣ የማስተላለፍ ባህላዊ ማንነትን የማስጠበቅ ተግባር እን ዳለው ይገልጻሉ። በመሆኑም ማህበረሰቡ በተለያዩ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በሚደረጉ ፎክሎራዊ ክንዋኔዎች እነዚህን ተግባራት ያገኛሉ። ነውሮችም በፎክሎር ከሚገለጹ ማህበራዊ ልማዶች መካከል አንዱ በመሆናቸው የማስተማርና ባህላዊ ማንነትን የማስጠበቅ ተግባር አላቸው።

በመሆኑም በጥናቱ የተገኙ ነውሮች በእያንዳንዱ ባህላዊ ክንውኖችና ማሕበራዊ አጋጣሚዎች ውስጥ የሚገለፁና እነሱንም ስርአትና ደንብ ባለው አካሄድ ለመምራት የሚያስችሉ ዘዴዎች ናቸው። የማስተማርና ባህላዊ ማንነት የማስጠበቅ ተግባር ያላቸው ሆነው ተገኝተዋል። ማህበረሰቡ ይበልጥ ትኩረት የሚያደርግባቸው የሕይወቱ ማራመጃ መንገዶች ናቸው። ተጠኚው ማህበረሰብ ለነውሮች ካለው እምነትና ቦታ አንጻር ጥቅሙን በማሰብ የሚኖር ነው።

ማህበረሰቡ ያወጣቸውን ሕጎችና ደንቦች ከማስጠበቅ አንጻር ትልቅ ሚናን ይጫወታሉ፡፡ ከሕብረተሰቡ አኗኗር ስርአት እንዳያፈነግጡ መቆጣጠሪያ፣ ለልጆቻቸው የስነ ምግባር ማስተማሪያ ዘዴ በመሆን የሚሰጠው ፋይዳ የላቀ ነው፡፡

## 5.3.2. የነውሮች ፋይዳ ከነውር አይነቶች አንጻር

### የመከባበር እሴትን ማስጠበቅ

ክብርን ከማስጠበቅ አንጻር የተጠቀሱት ነውሮች ልጆች ከልጅነታቸው ጀምሮ እናትና አባት ታላላቆችን፣ የሀገር ሽማግሌዎችን እና ማህበረሰቡ ትልቅ ክብር ለሚሰጣቸው የተመረጡ ቦታዎችን እንዲያከብሩ በተለያዩ መንገዶች ያስተምራሉ፡፡ ይህንም የሚከለከሉ ነገሮችን በማሳየት ሲፈልጉ የሚፈቀድላቸውን አካላት ማስፈቀድ እንዳለባቸው ይገልጻሉ፡፡ ለምሳሌ አባት በሕይወት እያለ ልጅ ከብት አያርድም፣ ደመራ አይለኩስም እሸት አይቆርጥም ወዘተ የሚጠቀሱ ክልከላዎች አሉ፡፡ የመጀመሪያው ለአባት ብቻ የሚፈቀደውን ነገር እንዲጠብቁና ከፈለጉም ፈቃድ መጠየቅ እንዳለባቸው፣ ሁለተኛው ነውር የደመራ ስርአቱን ሀይማኖታዊ ባህላዊ አከባበሩን ጠብቆ ለማቆየትና ባህላዊ ማንነት ለማስጠበቅ ነው፡፡ ሶስተኛው ምሳሌ ልጆች ለወላጆቻቸው ታዛዥ እንዲሆኑ ለማስተማር ነው፡፡ ስለሆነም ይህን ከጣሱ የሚደርስባቸውን ነገር በማሳወቅ የመካባበር እሴትን በማስጠበቅ ነውሮች ከፍተኛ ሚናን ይጫወታሉ ማለት ይቻላል፡፡

### ለወገን ደራሽ መሆን፣ መተዛዘን እና መተሳሰብን ማስተማር

በሁለተኛ የነውር አይነቶች ላይ በሌላ ወገን ላይ አደጋ ሲደርስ ዝም ማለት እና ክፋት ማድረግ ስርቆት ተጠቅሰዋል፡፡ እነዚህ ነውር የተባሉት ወገን ለወገን የመረዳዳትና የመተሳሰብ እሴትን ለማስጠበቅ ትልቅ ፋይዳ አላቸው፡፡ የውሸት ምስክርነት እንዳይኖር፣ ስርቆትን እንዳይማሩ፣ አደጋ የደረሰበትን ሰው የመርዳት ባህሪን እንዲያላብሱ ያደርጋል፡፡ ይህንን የጣሱ ደግሞ በእውነ ይደርሳል የተባለው የአንደበት መዘጋት፣ ሲሰርቁ እባብ የተጠመጠመባትን ሴትዮ በማየት ነውሮችን እንዲጠብቁ ያደርጋል፡፡ በሰው ላይ ግፍ ማድረስም ራስን እንደሚጎዳና ቅዥት እንደሚይዛቸው የተጠቀሱት ገጠመኞች ይገልጻሉ፡፡ እነዚህን ታሳቢ በማድረግ እርስ በርስ የመተሳሰብንና የመተዛዘንን ባህል ለማዳበር ይረዳሉ ማለት ነው፡፡

*ታማኝነትንና ታዛዥነትን ለማስተማር*

በዚህ ደግሞ የሚጠቀሰው ዝምድናን ከማስጠበቅ አንጻር የተገለጹት ነውሮች ናቸው፡፡ ከነሱም መካከል በቤተ ዘመድ መካከል ግብረ ስጋን መፈጸም በሀይማኖትም በባህልም የተወገዘ ተግባር ነው፡፡ ከፈቃድ ውጭ የሚደረገውን የመደፈር አደጋን ለመከላከል የሚጫወተው ሚና አለ፡፡ በወንጀልም የሚያስጠይቅ ስለሆነ ከስሩ ከመሰረቱ ለማስተማር ይጠቅማል፡፡ የትዳርን ሕልውና ከማስጠበቅ ጋር የሚገለፁ ነውሮች ሰዎች ለትዳራቸው ታማኝ እንዲሆኑ ቤተሰብ መርቆ እንዲሸኝ ለቤተሰቦቻቸው ይዘው የሚሄዱትን በግና ሙሉ እንስራ ጠላ እንዳይተው የጋብቻ ስርአቱን ቀጣይነት እንዲኖረው ያደርጋል፡፡ ለትዳሩና ለቤተሰቡ ታማኝ የሆነ ሰው ነገ ለሀገሩም ታማኝና ቅን አገልጋይ እንዲሆን ያደርጋልና፡፡

ለሴቶች የሚከለከሉ ነገሮችን ብንመለከት ከንጽህና ጋር በተያያዘ የወር አበባ ላይ ሆና በወላጆቿ አልጋ ላይ መተኛት አትችልም፡፡ በቤተ ክርስቲያንም ቤተ መቅደስ መግባት፣ በእስልምናም መስኪድ መግባት እንደማይቻል ይታወቃል፡፡ ለደመራ የተዘጋጀ ምሰሶጋ አትጠጋም የደመራ ስርአቱም የሚከናወነው በወንዶች ነው ሀይማኖታዊ ስርአቱም እንዲህ ነው፡፡ Mary dauglas (1996፡8) ነውሮች ሀይማኖታዊ ባህላዊ ይዘት እንዳላቸው ይገልጻሉ፡፡ በሀይማኖት ተቋማት የሚከለከሉ ነገሮች በባህልም ክልክል ሆነው ይታያሉ፡፡ በዚህም ሀይማኖትና ባህል በሰው ልጆች ሕይወት ውስጥ የተቆራኙ በመሆናቸው ለሁለቱም ታዛዥና ስርአቱን የሚጠበቅ ትውልድ ለማፍራት ይረዳል ማለት ነው፡፡

የመጨረሻው የተጠቀሰው የነውር አይነት ከእምነት ጋር የሚያያዙ ሲሆኑ ባዕድ አምልኮን፣ ከወንዝ ያደረን ነገር ማምጣት፣ መብረቅ የመታውን እንጨት ከባለቤቱ ውጭ ሌላ ሰው መጠቀም፣ ለቅሶ ባለበት ቤት /ሬሣ ከወጣበት/ በግ አለማረድ ወዘተ የተከለከሉ ነገሮች ናቸው፡፡ ከክፉ መንፈስ ጋር በማያያዝ ነውር ነው በማለት ይናገራሉ፡፡ እነዚህ ማህበረሰቡ ላመነባቸው ነገሮች መገዛት መከተል እንደሚገባቸው ለማስተማር የሚጠቀሙበት ነው፡፡

የዶርዜ ማህበረሰቡ የነውርን ፋይዳ ሲገልጹ ተተኪው ትውልድ ከማህበረቡ እንዳያፈነግጥ መቆጣጠሪያ፣ እሴቱን ባህሉንና ታሪኩን መጠበቂያ ማቆያ፣ ለልጆቻቸው ስነ ምግባር ማስተማርያ ዘዴ፣ ትዳሩ ቤተሰቡ የሚባረክበት፣ ነውርን ያከበረ ለሕግም የሚገዛበት እና በሕዝቡም ዘንድ ተወዳጅነትን ተቀባይነት የሚያገኝበት መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

### 5.3.3 የነውሮች ጉዳት

ነውሮች ጥቅም እንዳላቸው ሁሉ ጉዳትም አላቸው፡፡ ምክንያቱም ሁሉም የህብረተሰቡ ክፍል ሁሉንም የነውር አይነቶች ይቀበላቸዋል ማለት አይቻልምና፡፡ በመረጃ ስብሰባ ወቅት በተጠኚዎች ላይ የታየው ነገር አንዳንዶች ብዙም የማያምኑባቸውን ነውሮች ጉዳት እንዳላቸው የሚገልጹ ይስተዋላሉ፡፡ እነሱም ነውር የጣሰ ከተረገመ እድሜን ያሳጥራል ፣ቤተሰብ ይጎዳል፣ በእርቅ ያልተፈታ ነውር ካለ በቤተሰብ ላይ መቅሰፍት ያመጣል ይባላል፡፡ እነዚህን ይደርሱብኛል በማለት በፍራቻና ስጋት እንደሚንቀሳቀሱ ይገልጻሉ፡፡

ሌሎች ደግሞ አሁን ካለው የአኗኗር ሁኔታ ጋር የማይጣጣሙ ነውሮች ሲሆኑ ብዙሀኑ የህብረተሰብ ክፍል የሚኖረው ከተማ ነው፡፡ ወላጆቻቸው ደግሞ ገጠር ስለሚሆኑ በቤታቸው ከብት፣ በግ ፣ ፍየል አርዶ ለመብላት ይቸገራሉ፡፡ ወጣት ሀይሉ የተባለ መረጃ አቀባይ እንደገለፀልኝ ከሆነ "ብዙ ጊዜ አባቶች ልጆች በቤታቸው እንዲያርዱ አይፈቅዱም የተናቁ ይመስላቸዋል፡፡ በስራ ምክንያት ሌላ ቦታ ሄደው በዛው ትዳር መስርተው ያሉ የፈለጉትን ለማድረግ ነጻነት አይኖራቸውም፡፡ ጎረቤት ጠርተው ነው የሚያሳርዱት አንዳንድ አባቶች ይህን ተረድተው የሚፈቅዱ አሉ፡፡ በተለይ ልጆች ካሉ በጣም ትቸገሪያለሽ ሕግ በጣም ያጠብቃሉ" ይላል፡፡ (11/8/11)

ይህም በተለያዩ ምክንያት ከገጠር ወደ ከተማ የሚፈልሱ ብዙ ናቸው፡፡ ከተማ ካለው የአኗኗር ሁኔታ ጋር ለማጣጣም የሚቸገሩ በመሆናቸው አሉታዊ ጎኑን ይገልጻሉ፡፡ እነዚህንም የተወሰኑ ማሻሻያዎችን በማድረግ እየተጠቀሙ እንደሆነም ይናገራሉ፡፡ ሆኖም አብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል ነውሮችን የሚጠብቅና የሚያከብር በመሆኑም ነውሮች ጥቅም እንጂ ጉዳት አላቸው የሚል እምነት የለውም፡፡

## 5.4. የዶርዜ ማህበረሰብ የነውር አይነቶች ላይ የታየ ለውጥና ተከታታይነት

ለውጥ፡- ከፎክሎር ባህርያት መካከል አንዱ ተለዋዋጭነት ነው፡፡ በተለያዩ ጊዜያትና ሁነቶች አማካኝነት ለውጥ ይከሰታል፡፡ Sims and Stephens (2005፡85) በውጫዊና ውስጣዊ ሁኔታዎች ምክንያት ልምድ ይለወጣል፡፡ Tolken(1996፡45) ደግሞ በማንኛውም ሁኔታ ልምድ ላይ የሚደረጉ ፈጠራዎች ለውጥ ናቸው ይላሉ፡፡ እነዚህ ሀሳቦች የሚያስረዱት በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ ልምዶች በጊዜ ብዛት፣ በማህበራዊና ፓለቲካዊ ሁኔታዎች አማካኝነት የተለያዩ

ባህርያት ያሳያሉ እነዚህ ባህርያት ሰው ሰራሽ ወይም ተፈጥሯዊ ለውጦች ሲሆኑ ጨርሶ የመጥፋት ወይም በሌላ የመተካት ሊሆን ይችላል፡፡

በመሆኑም ነውሮች ከልምዶች መካከል አንዱ በመሆናቸው ለውጥ ሊከሰትባቸው ይችላል፡፡ ነውሮች በፊት ሲከበሩ የነበሩ በአሁን ሰአት የቀሩ ወይም ማሻሻያ የተደረገባቸው ይሆናል፡፡ እነዚህም ጨርሰው የመጥፋት ወይም ማሻሻያዎች የተደረገባቸው ሲሆኑ በሌላ አካባቢ (ከተማ) የሚኖሩት ካሉበት ቦታ አንጻር የማይመቹትን ቀለል አድርገው ማየትና መቀየር ናቸው፡፡ እየተቀያየሩ የመምጣት ባህሪ ያሳያሉ፡፡ ለምሳሌ በድሮ ጊዜ በጣም የሚካበዱና የሚፈሩ የነበሩ አሁን ካለው የአኗኗር ሁኔታ ጋር የማይጣጣሙ ከሆኑ ማህበረሰቡ እየተወና ግንዛቤው እየተቀየረ ሲመጣ ቀለል አድርጎ የማየት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ የሚጣሉ ቅጣቶችም ከነባራዊ ሁኔታዎች ጋር የሚሄዱ ይሆናሉ ማለት ነው፡፡ በተጠኚው ማህበረሰብ ዘንድም ባሉ ነውሮች ላይ የተከሰቱ ለውጦች አሉ እነሱም ከአካባቢው የአብያተ ክርስቲያናት መስፋፋት ምክንያት፣ በፓለቲካዊ ለውጥ እንዲሁም የማህበረሰቡ ተወላጆች በስራና በግል ሕይወት ምክንያት ወደሌላ አካባቢ በመዘዋወራቸው ነውሮች ተለውጠዋል፡፡

ከእምነት ጋር ተያያዥ የሆኑ ነውሮች የክርስትና እምነት በአካባቢው እየተጠናከረ በመምጣቱ የቀሩ ነውሮች አሉ፡፡ እባብና ነብርን በደጃፍ ሲመጡ አንዳች ክፉ ነገር እንደሚከሰት፤ እባብ በቀደደ ገብቶ በበር ከወጣ በቤቱ ውስጥ ሞት ይመጣል ይባል ነበር፡፡ ባሁን ጊዜ ግን ቢመጣም ይገሉትና ይጥላሉ ወይም በገለባ ውስጥ በማድረግ ያቃጥሉታል እንጂ ሞት ይመጣል የሚል ፍራቻው ቀንሷል፡፡ ለዚህም ቤተክርስቲያን እየሄዱ አጉል እንደሆነና በፈጣሪ ብቻ እምነታቸውን እንዲጥሉ ስለሚመከሩ ትተዋል ማለት ይቻላል፡፡ ሌላኛው ሴት ልጅ ወልዳ በቤተሰቧ ቤት አትታረስስም ነበር፡፡ በአሁኑ ሰአት ግን ካለው የኑሮ ሁኔታ ጋር በማያያዝ ብዙሀኑ ሀኪም ቤት ስለሚወልዱ ቤተሰቦቸው ጋ ሄደው መታረስ ይችላሉ፡፡

በፓለቲካዊ ምክንያት ደግሞ በነውሮች ላይ የተከሰተው ለውጥ የመንግስት አስተዳደር መቀያየር ምክንያት ሲሆን አብዛኛው ቀለል አድርጎ የማየት ክስተት እንደተፈጠረ ይገልጻሉ፡፡ “አብዛኛው ድሮ ጎጅ ባህል እየተባለ በደርግ ጊዜ ነው የቀረው፡፡ አለቃ መሾም መቀየር ቀርቷል በፊት አለቃ የነበሩት በልጆቻቸው አማካኝነት የሚከበረው ነገር እየቀጠለ ነው፡፡ እንጂ አሁን እኮ የሀገር ሽማግሌዎች ይመረጣሉ ይወከላሉ ግን ንጉስ (ዴሙሳ) መሾም የሹመት ስርአት የለም....” (አቶ ዛዳ ሄቦ እና አቶ ጌሮ ጌምቤሮ 1/8/11) ተጠኚዎቹ እንዳሉት ጎጂ ባህል ነው

በሚል ምክንያት ባህላዊ ክንውኖች መቅረታቸውን ሲሆን አብዛኞቹ የንጉስና የአለቆች ልጆች፣ የልጅ ልጆች አንዳንድ ስርአቶችን እንደሚያከናውኑ ነው፡፡

የመስቀል በአል ሲከበር በደመራው ቦታ ላይ የእርድ እለት በሬ ታርዶ ይለቀቅ ነበር፡፡ በዚህም በሬው እስኪወድቅ ድረስ በገበያው እንዲዞር ይደረጋል፡፡ ይህን ትዕይንት በሚመለከቱበት ወቅት የተለያዩ ሰዎች ከበሬው ለማምለጥ በሚተረማመሱበት ወቅት አቅመ ደካሞችና ሕጻናት ይወድቃሉ ይረጋገጣሉ፡፡ በመሆኑም ይቅር ተብሎ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ቀርቷል፡፡ የደመራ ስርአቱን የሚያከናውኑት የአለቃ ቤተሰቦችና ሌሎች ሽማግሌዎች ናቸው፡፡ እንዲሁም ሴት ልጅ ውርስ ላይ መከፋፈል አትችልም ነበር አሁን ግን እኩል መካፈል ትችላለች ቤትም መስራት ጀምረዋል፡፡ በፊት ውርስ መጠየቅ እራሱ አባትን የመዳፈር ወንዶች ልጆችንም  እንደመናቅ ይቆጠር ነበር፡፡

ከዝምድና ጋር በተያያዘ ዴገላ /ፋቂ/ ከሚባሉት ህብረተሰቦች ጋር መጋባት እንደነውር ይቆጠር ነበር፡፡ "በአሁን ሰአት የሚጋቡ አሉ ይህም  ችግር የለውም አንደኛው ሰው ናቸው ስራቸው ነው እንዲለዩ ያደረጋቸው በማለት በተለይ በከተማ የሚኖሩ ይህን ያደርጋሉ"፡፡ (አቶ አበራ ገነኔ 2/8/11) በማለት ይገልጻሉ፡፡ ይህ ነገር የሰዎችን እኩልነት  ለማሳየትና በአካባቢው ያሉ ፋቂ የሚባሉትም በፊት ሲናቁ ስለነበር ከማህበረሰቡ ጋር ለመቀላቀል ፍላጎት እያሳደሩ በመምጣታቸው ነው፡፡ ይሁን እንጂ የመናቅ ሁኔታ በተወሰነ መልኩ ይስተዋላል እንዲሁም አዋቂ ቤት እየሄዱ የሚጠይቁትም በሀይማኖት አባቶች እየተከለከሉ ስለሆነና ግንዛቤያቸው እየጨመረ ስለመጣ እየቀረ መምጣቱን ይገልጻሉ፡፡ ስለሆነም በጊዜና በሁነቶች አማካኝነት እየተለወጡ የመጡ ነውሮች መኖራቸውን ማወቅ ይቻላል፡፡

ተከታታይነት፡- ይህ ደግሞ የልምዶችን ድግግሞሽ የሚያሳይ ሲሆን በጊዜ ሂደት ውስጥ ያለውን የማያቋርጥ ሁነት የሚገልጽ ሀሳብ ነው፡፡ Sims and Stephens (2005፣65) በየትኛውም የጊዜ ርዝመት የሚደረግ ድግግሞሽ ልምድን ይፈጥራል፡፡ የልምድ መደጋገም ደግሞ ተከታታይነት ይፈጥራል፡፡ በዚህም የነበረውን መስሎ መቀጠል ሳይሆን የልምዱን ትርጉም ወይም ጥቅም የያዙ ነገሮችን የሚመለከት ሀሳብ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ በመሆኑም ነውሮች ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፉ የሚመጡና የሚጠበቁ ናቸው፡፡ አንዳንዶቹ እንዳለ ሲቀጥሉ የተቀሩት ደግሞ ከፊል ማሻሻያ ተደርጎባቸው የያዙት ትርጉምና ጥቅም እንዳለ ሆነው ይቀጥላሉ፡፡

በዶርዜዎች ዘንድም ብዙሀኑ ነውር የተባሉ ነገሮች ቀጣይነት ያላቸው ናቸው፡፡ ለምሳሌ የመስቀል በአል አከባበር አሁንም ድረስ ያለ ክብረ በአል ነው፡፡ በዚህ ላይ የሚገለፁ ነውሮች የሀገር ሽማግሌዎችና የየቤቱ አባወራዎች የሚያደርጉት የደመራ ስርአት እንዳለ ቀጥሏል፡፡ በዚህም ሴቶች የማይሳተፉበትን የሚከለከሉባቸውን ነገሮች አሁንም እንደተጠበቁ ናቸው፡፡ ባህላዊ ስርአተ ከበራውም በፊት የነበረውን ቅደመ ተከተላዊ ስርአቱን የተከተለ ነው፡፡ የለቅሶ ስርአቱም ከጥንት ጀምሮ የነበረውን አካሄድ ይዞ የቀጠለ መሆኑ በመረጃ ስብሰባ ወቅት የነበሩ ሁኔታዎች ያስረዳሉ፡፡

# ምዕራፍ ስድስት

# ማጠቃለያና የይሁንታ ሀሳብ

በዚህ ምዕራፍ ጥናቱ ከመነሻው አንስቶ እስከመጨረሻ የነበሩ ሂደቶች እና ውጤቶች የቀረቡበት ሲሆን በተጨማሪም የይሁንታ ሀሳቦች ተጠቅሰዋል፡፡

## 6.1. ማጠቃለያና የጥናቱ ውጤቶች

ይህ ክፍል መረጃዎችን ተመርኩዞ በቀረበው ትንታኔ ላይ የቀረበ ማጠቃለያና በጥናቱ የተገኙ አበይት እና ንዑሳን ውጤቶችን የያዘ ነው፡፡

### 6.1.1. ማጠቃለያ

ይህ ጥናት ነውር እንደማህበራዊ ደንብ ማስጠበቂያ ስልትነት በዶርዜ ማህበረሰብ በሚል ርዕሰ ጉዳይ የተጠና ነው፡፡ የርዕሰ ጉዳዩና የአካባቢው መመረጥ ምክንያት በግል ገጠመኝና በንባብ ልምድ ሲሆን ገጠመኙ በነውር መተላለፍ የደረሰውን ነገር በማየቴና ወደቦታው ለመስቀል በአል ባንድ ወቅት ሄጀ የተመለከትኩት ነገር ስለሳበኝ ነው፡፡ ይህም የማህበረሰቡ ተወላጅ ብሆንም ተወልጄ ያደጉት ሌላ ቦታ ስለሆነ ባህሉንና ታሪኩን ለማወቅ ጉጉት ስለደረሰብኝና ነውሮች ለማህበረሰቡ ያላቸውን ፋይዳ እና በምን መልኩ እንደሚገለገሉባቸው ለማወቅ ነው፡፡ በንባብ ልምዴ ደግሞ ይህ ርዕሰ ጉዳይ ብዙም ያልተጠናበት ሆኖ ስላገኘሁት ነው፡፡

የጥናቱ አላማ የዶርዜ ማህበረሰብ በነውር ዙሪያ ያለውን ዕውቀት፣ አስተሳሰብና ፍልስፍና በመመርመር ለሌሎች ማሳወቅና የነውሮችን ሚናና አገልግሎት ማሳየት ነው፡፡ አላማውን ለማሳካት ወደቦታው በመሄድ የተለያዩ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ የተሰበሰቡት መረጃዎች በምልከታና በቃለ መጠይቅ ሲሆን አሻሚና አከራካሪ የሆኑ ጉዳዮች ሲገጥሙ ደግሞ ቡድን ተኮር ውይይት ተግባር ላይ ውሏል፡፡ እንዲሁም የመዛግብት ፍተሻ ተካሂዷል፡፡ መረጃ አቀባዮች የተመረጡበት ንሞና ስልት አላማ ተኮር እና ጠቋሚ ናሙና ስልት ናቸው፡፡

በምልከታ የሽምግልና ስርአት ላይ በመገኘት ሲሆን ነውርን ለማግኘት የተለየ አውድ ስለሌለው አብዛኞቹ መረጃዎች በቃለ መጠይቅ የተሰበሰቡ ናቸው፡፡ እንዲሁም በለቅሶ ስርአት በክብረ በአላት እና በቡና ጠጡ ኘሮግራም ላይ በመገኘት መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ መረጃ በመስጠት ተሳታፊ የነበሩ ዕድሜያቸው ከ20 በላይ የሆኑ 30 ሰዎች ተሳትፈዋል፡፡ እነዚህም የሀገር

ሽማግሌዎችና ማህበረሰቡ ትልቅ ቦታ የሚሰጣቸው ያውቃሉ የሚሏቸውን እንዲሁም ከነውር ጋር በተያያዘ ገጠመኝ ያላቸው ሰዎች ናቸው፡፡ በመረጃ ስብሰባው የተገኙ ነውሮች በአጠቃላይ 72 ሲሆኑ ለናሙናነት የተመረጡት 52 ናቸው፡፡ ለዚህም ተመሳሳይ ይዘት ያላቸውን በመቀነስ ነው፡፡

ከላይ የተገለጹትን መረጃ መሰብሰቢያዎች በመጠቀም ነውር ያረፈባቸው ነገሮችንና ምክንያቶች፣ የታዩ ለውጦችን፣ ከጥፋት መመለሽ እሴቶችና ፋይዳውን በተመለከተ አስፈላጊ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ በመሆኑም ክብርን ከማስጠበቅ አንጻር፣ በሌላ ወገን ላይ በሚደርሱ ነገሮች አንጻር፣ ዝምድናን ከማስጠበቅ አንጻር፣ ለሴቶች የሚከላከሉ ነገሮች፣ የትዳርን ሕልውና ከማስጠበቅ ጋር እና ከእምነት ጋር ተያያዥ የሆኑ ጉዳዮችን ትኩረት ያደረጉ ነውሮች በጥናቱ ተካተዋል፡፡ በነሱም ላይ ትንተና ተካሂዶባቸዋል፡፡

የማህበረሰቡ አመለካከት ነውር (ጎሜ) ማለት ያልተገባ ያልተቀደሰ ክፉ ድርጊትና ሀጢያት ማለት ነው፡፡ ነውር በማለት የሚገለጹትም፡- ልመና፣ ስርቆት፣ ጥንቁልና፣ ሟርት፣ ዝሙት ያልሆነ ውሸት፣ ያልተገባ ንግግር፤ ለታላላቆች አክብሮት መንሳት፤ እናትና አባትን አለማክበር፣ ማሳዘን፣ የወሰዱትን የተበደሩትን መካድ፣ ለወላጅ አለመታዘዝ የተመረጡ የሚከበሩ ቦታዎችን የአካባቢ ችሎት አለማክበር፣ መሪዎችን አለቃ (ደሙሳ)የአካባቢ ባህላዊ አስተዳዳሪዎችን መዝለፍና አክብሮት አለመስጠት፣ በዓመት አንድ ቀን ደመራ ለመስቀል አለማውጣት፣ ሰው ከሞተበት ቤት የማንፃት በግ አለማረድ፣ ለአቅመ አዳምና ሄዋን የደረሱ ልጆች የወላጅ አልጋ ላይ መተኛት ወዘተ ክፉ ተግባርና ስራ እግዚአብሔርም ሰውንም የሚያሳዝን ድርጊት ነው ይላሉ፡፡

በጥናቱ መሰረት ነውር ለዶርዜ ማህበረሰብ ማሕበራዊ ደንቦችና ሕጎችን የሚያስፈጽምበት፣ ሕይወቱን የሚመራበት በአካባቢው ያሉ ነገሮችን የሚገለገልበትን መንገድ የሚቀርጽበት፣ የልጆቹን ባህሪ የሚቀርጽበት፣ ስነ ምግባር የሚያስተምርበት ዘዴውና የባህሉ እና የእምነቱ ዋነኛ አካል ነው፡፡ ነውርን ለሚተላለፍ የሚያምንበትን ምክንያት በመጥቀስ ማህበራዊ ደንቡንና ሕጎችን ያስከብርበታል፡፡ የሚቀርቡት ምክንያቶች በእምነት ብቻ ሳይሆን በተግባር በእውን የተከሰቱ ተጨባጭ ነገሮች ይታዩባቸዋል፡፡ ስለዚህ በተጨባጭ የተገኙ ነገሮች ነውሮች እንደይጣሱ ማስረጃ ይሆናሉ ማለት ነው፡፡

ነውሮችን የሚፈጥሩት ለአኗኗሩ መመሪያ፣ የትውልዱን ስብዕና ለመቅረጽ አጠቃላይ ፍላጎቶችን ለማርካት ደንብና ሕግ ሆነው እንዲያያገለግሉት በማሰብ ነው። ስለሆነም ነውሮች የኑሮ ቀውስና መፋለስ እንዳይኖር የሚከላከሉ የሚመቹ ዘዴ ብልሀት ያሉ የቀልጣፋ ስርአት ማስኬጃ ዘዴዎች ናቸው። እንደ አለንጋ የሚጋረፉ ተግሳጾች ከራስ ጋር ተስማምቶ ለመኖር ሚዛን ጠብቆ የመራመድ፣ ቅን ሕሊናን የመፍጠር፣ ለምኞትና ለስሜት ልጓም የሚሆኑ የቅንነትን የታማኝነት የመከባበርና የመረዳዳት የፍቅር የመግባባበትና የስምምነት እሴት መገለጫዎች ናቸው።

## 6.1.2. የጥናቱ ውጤቶች

በዚህ ጥናት የተበሰቡትን መረጃዎች በመመርኮዝ የቀረበውን ትንታኔ መሰረት በማድረግ ውጤቶች ተገኝተዋል። ይህ ማህበረሰብ ነውርን እንደቅዱስ የሚያይና የሚፈራ የሚያከብረው ነው። frued(2004፡21) ስለነውር የሰጠው ብያኔ በሁለት መንገድ ነው። አንደኛው የተቀደሰ አንደቅዱስ የሚታሰብ የተሰጠ ማለት ሲሆን ሁለተኛው ብያኔ በጣም ረቂቅ የሚፈራ ክልክል ያልጸዳ በማለት ይተረጉመዋል። በዚህ ማህበረሰብም የታየው ነውር ገሚሱ የሚያከብረው አምኖትና ተቀብሎት የሚኖር እንደቅዱስ የሚያየው ነው። የተቀረው አካል ደግሞ የሚፈራው እንደሀጢያት የሚቆጠር ሲሆን ሀጥያት ነው በማለት ፍቺ ይሰጣሉ። የfreud ብያኔ እና የማህበረሰቡ ለነውር ያለው አመለካከት ተቀራራቢ ሀሳብ ያላቸው ሆነው ተገኝተዋል። በሞላ(2009) ጥናት ውስጥ ለነውሮች የሚቀርቡት ምክንያቶች በእምነት ያሉ እንጂ በተጨባጭ የሚታዩ እንዳልሆኑ ተጠቅሷል። ነገር ግን በዚህ ጥናት ለነውር የቀረቡት ምክንያቶች አንዳንዶቹ ተጨባጭ ሆነው የሚገኙ ናቸው። የጥናቱ አበይትና ንዑሳን ውጤቶች እንደሚከተሉት ቀርበዋል።

- ❖ ነውር ለማሕበረሰቡ ማህበራዊ ደንብ ማስጠበቂያ ስልት ከመሆኑም በላይ በራሱ እንደሕግ በመሆን የሚያገለግል ሆኖ ተገኝቷል።
- ❖ ለነውር የሚሰጡት ምክንያቶች በሀሳብ/በእምነት ብቻ የሚገለፁ ሳይሆኑ በተጨባጭ ሁኔታ የሚታዩ ሆነው ተገኝተዋል።
- ❖ ነውር ለማህበረሰቡ ዋነኛ የህይወቱ አካል በመሆን የሚያገለግል ነው።
- ❖ ነውር እራሱንና ቤተሰቡን እንዲሁም የአካባቢውን ማህበረሰብ ከጉዳት ለመጠበቅ ያወጣው ክልከላ (ልቦናዊ ህግ) ነው።

ንዑሳን ውጤቶች

- ❖ የዶርዜ ማህበረሰብ ክብሩን የሚያስጠበቅ ማንነቱ እንዲነካበት የማይወድ መሆኑን
- ❖ ከራሱ ውጭ ከጎኑ ያለውን ማህበረሰቡ ከጉዳት የሚጠብቅ የሚከላከልለት
- ❖ ዝምድናውን ሀይማኖታዊና ባህላዊ መመሪያዎችን መሰረት በማድረግ የሚጠብቅ
- ❖ ትዳር የማህበረሰብ መሰረት ነውና ከስሩ በታማኝነትና በመቻቻል እንዲኖሩ ሕልውናውን የሚያስጠብቅ
- ❖ በሀይማኖትም በባህልም ያሉ ክልከላዎችን የሚያስጠብቅ
- ❖ ላመነባቸውና ለሚመራባቸው ነገሮች ሀላፊነቱን የሚወስድ ላወጣቸው ሕጎች ተገዢ ማህበረሰብ መሆኑን መረጃዎቹ ያሳያሉ፡፡

## 6.2. የይሁንታ ሀሳብ

በዚህ ጥናት ነውር እንደ ማህበራዊ ደንብ ማስጠበቂያ ስልትነት የሚለውን ርዕሰ ጉዳይ መነሻ አድርጎ በምልከታ፣ በቃለመጠይቅ፣ በቡድን ተኮር ውይይትና በመዛግብት ፍተሻ የተሰበሰቡ መረጃዎችና ጥናቱ የተነሳበትን አላማ መሰረት በማድረግ የተገኙት ውጤቶች ተጠቅሰዋል፡፡ የአንድን ማህበረሰብ ፍልስፍና፣ አስተሳሰብና እምነት ለማወቅ ማህበረሰቡ የሚገለገልባቸውን የሚታወቅባቸውን ነገሮች ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ ከነሱም መካከል ባህላቸውን፣ ታሪካቸውን ወዘተ መነሻ በማድረግ ለማጥናት ያስችላል፡፡ በዚህ ጥናት ነውሮች የአንድን ማህበረሰብ ፍልስፍና እምነትና አስተሳሰብ የሚገልፁ መሆናቸው የታየበት ነው፡፡ ስለሆነም በጥናቱ ላይ በታዩ ጉዳዮች መሰረት ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ነጥቦችን እንደሚከተለው አቅርቢያለው፡፡

- ➢ በመረጃ ስብሰባ ወቅት አብዛኛው መረጃ ሰጪ ነውር የተባሉ ነገሮችን ከመጥቀስ ውጪ ፍካሬያዊ የሆነውን ምክንያት አያውቁትም፡፡ ስለሆነም በማህበረሰቡ ዘንድ ትልቅ ቦታ የሚሰጣቸውና ባህሉንና ታሪኩን የሚያውቁ ሰዎች ምክንያቱን ለማያውቁት ቢያሳውቁ እርስ በርስ የመረጃ ልውውጡ የተጠናከረ ቢሆን፣
- ➢ ነውሮች በቃል የሚተላለፉ ባህል በመሆናቸው የመረሳትና የመቅረት እድሉ የሰፋ ስለሚሆን በወረዳውና በዞኑ ብሎም በባህልና ቱሪዝም ቢሮ በኩል በሰነድ መልክ

ተዘጋጅቶ ቢቀመጡ ለመጪው ትውልድ ለማስተላለፍና ለማስተማር ያገለግላሉ፡፡ ስለዚህ የተጠቀሱት አካላት ትኩረት ቢያደርጉበት፣

ከተጠቀሱት ነውሮች መካከል ፀጥታና ደህንነት ከማስጠበቅ ጋር በተያያዘ በርካታ ነውሮች ይጠቀሳሉ፡፡ ለምሳሌ ስርቆት፣ በሰው ላይ በደል ማድረስ፣ አደጋ ሲደርስ እያዩ ዝም ማለት ወዘተ ነውር ናቸው፡፡ እንደዚህ አይነት ነውሮች የአካባቢውን ሰላምና ደህንነት ለማስጠበቅ ከፍተኛ ሚና ስለሚጫወቱ የሚመለከታቸው የፀጥታና ደህንነት አካላት ነውሮችን የስራቸው አካል ቢያደርጉና ለሚቀርፁት ፖሊሲ እንደመነሻ የሚያገለግሉ በመሆናቸው ትኩረት ቢሰጡት እላለሁ፡፡

- ነውሮች ባህልን በማስጠበቅ እና ልጆችን በስነምግባር የታነፁ እንዲሆኑ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አላቸው፡፡ በመሆኑም አወንታዊ ጎን ያላቸውን በመውሰድ የትምህርት ፖሊሲ ሲቀረፅ ነውሮች ታሳቢ ቢደረጉ፣
- በዶርዜ ማህበረሰብ ዘንድ በደማቅ ሁኔታ የሚከበረው የመስቀል በአል ላይ በርካታ ጎብኚዎች ወደቦታው ለመታደም ይጓዛሉ፡፡ በአካባቢው ደግሞ የተለያዩ ዋሻዎችና ፏፏቴዎች ይገኛሉ፡፡ እነዚህን በሚጎበኙበት ወቅት ያለተገባ ድርጊቶች፣ ማህበረሰቡ የሚከለክላቸው ነገሮች እንዳይጣሱ በቀበሌዎች፣ በወረዳውና በአስጎብኚዎች ዘንድ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሰነዶች ወይም መመሪያዎች ቢያዘጋጁ መልካም ነው፡፡
- ሁሉንም የነውር አይነቶች ሁሉም የማህበረሰቡ አካል ይስማሙበታል ማለት አይቻልም፡፡ ነውሮች አወንታዊና አሉታዊ ጎን ያላቸው በመሆኑ የማይስማሙባቸውን ቢያስቀሩና ጠቃሚ የሚባሉትን ቢያስቀጥሉ፣

መረጃ በምሰበስብበት ወቅት ስለነውር መጠየቅ ራሱ እንደነውር የታየበት አጋጣሚ ነበር፡፡ ስለዚህ በህብረተሰቡ ዘንድ ግልፅ ውይይት ቢኖርና ነገሮችን በቀላሉ መንገድ ለመነጋገርና ለመረዳት ቢሞከሩ እላለሁ፡፡

ጥናቱ እንደሚያመለክተው የዶርዜ ማህበረሰብ አብዛኛው የህይወቱ ክፍል በነውርና በደንቦች የሚመራ ነው፡፡ ሆኖም በጥናቱ የተጠቀሱት ነውሮች ሁሉንም የሚመለከቱ ናቸው ማለት አይቻልም፡፡ ምክንያቱም መረጃዎች ቃላዊ ስለሆኑ የመዘንጋት ሁኔታ ስለሚያጋጥማቸው በአንድ ጊዜ ሁሉንም ለማግኘት አስቸጋሪ ሆኗል፡፡ በጥናቱ ውስጥ የተገለፁት ነውሮች የተወሰኑ ሲሆኑ ከዚህ በፊት ስለ ዶርዜ ማህበረሰብ በርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ የተጠና ጥናት

ባለመኖሩ ይህ ጥናት በከፊልም ቢሆን ማህበረሰቡን ያስተዋወቀ ነው የሚል እምነት አለኝ፡፡ በመሆኑም ሌሎች አጥኚዎች በማህበረሰቡና በርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ ሰፋ ያለ ጥናት ለማካሄድ እንደመነሻ ሀሳባ ያገለግላል እላለሁ፡፡

# ዋቢዎች


ሞላ ጀምበሬ (2009) ፡፡ የነውር እሳቤ በሊቦ ከምከም ወረዳ ማህበረሰብ እምነት፣ አዲስ አበባ

ዩኒቨርሲቲ በአማርኛ ቋንቋ ሥነጽሁፍና ፍክሎር ትምህርት ክፍል ለፎክሎር ዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፣ 2009፡፡

ሰሎሞን ተሾመ፡፡ (2007)፡፡ ፎክሎር ምንነቱና የጥናቱ የትኩረት አቅጣጫ፡፡ ፋር ኢስት ትሬዲንግ ኃላ.የተ.የግ.ማ.፡፡

ኪዳነወልድ ክፍሌ (1948)፡፡ *መጽሀፈ ሰዋሰው ወግስ ወመዝገበ ቃላት አዲስ*፡፡ አዲስ አበባ፤ አርትስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

ዋልተንጉስ መኮንን (2007)፡፡ "ተፈጥሮን መናቅ፣ ሥጋን ማክበር፤ ለክፉ አይን አጋላጭ ክስተት፤ በምስራቅ ጎጃም በሚገኘው የጎዛምን ማህበረሰብ እምነት"፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በአማርኛ ቋንቋ ሥነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ለፎክሎር ዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡

የኢትዮጵያ ቋንቋና ጥናት ምርምር ማዕከል (1993)፣ *አማርኛ መዝገበ ቃላት*፡፡ አዲስ አበባ አርቲስቲክ ማተሚያ፣ ቤት፡፡

ያለው እንዳወቅ (2004) ፡፡ *የምርምር መሰረታዊ መርሆችና አተገባበር*፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ደስታ ተክለወልድ፡፡ *አዲስ የአማርኛ መዝገበ ቃላት* ፡፡ አዲስ አበባ፣ አርትስቲክ ማተሚያ ቤት፣1962፡፡

ፈቃደ አዘዘ (1991) ፡፡ <u>*የስነቃል መምሪያ*</u>፤ አዲስ አበባ፣ ቦሌ ማተሚያ ቤት፡፡

Asima Habibovic; (2010) Taboo Language, Swedish teenagers' understanding of and attitudes to English taboo language; Kristianstad University; English Department C-level essay in Language and Gender;

Bascom, William R. 1954). "Four Functions of Folklore". The Journal o American Folklore, Vol.67, No.266 pp 333-349 (Oct.- Dec)

Bicheiri Cristina (2016); <u>Dynamics of a Social Norm: Female Genital Mutilation/Cutting;</u> Cambridge University press.

Creswell (2003) reseah design Qualitative, Quantitative. and Mixed Methods approaches 2nd ed. University of Nebraska, Lincoln

Crotty, Michael. (1998) The Foundations of Social Research: Meaning and Perspective In the research process. Sage,

Dorson, Richared (1972); Folklore and folk life An introduction, the university of Chicago press, Chicago London.

Engert, Andreas (2016); Norms, rationality and communication; A reputation theory of social norms; franz steiner verlag.

Erkki¸ Olkinuora (1972) ⁝ Socialization, Structure of Personal Norms, and Norm

Alienation Acta Sociologica, Vol.15, No. 3, pp.228-253. University of Jyvaskyla, Finland: Sage Publications, Ltd.

Ezra Rosser (2008) CUSTOMARY LAW: the way things were, codefied tribal L.J. 18 American University Washington College of Law Washington College of Law Research Paper No. 2009-15

Fershtman,C., Uri G. and Moshe, (2011): H. "Taboos and identity: Considering the unthinkable." American Economic Journal: Microeconomics 139-164.

Frued, Segmund (1919); Totem and Taboo; London and New York⁝ Edition Taylor & Francis e-Library, 2004.

Given, Lisa M. (ed).(2008) The Sage Encyclopedia of qualitative research methods. Sage Publications,

Kuzma, Jerzy, et al. (2013) "Food taboos and traditional customs among pregnant women in Papua New Guinea: Missed opportunity for education in antenatal clinics." Contemporary PNG Studies 19

LUIS G. NARDIN and others Classifying sanctions and designing a conceptual sanctioning process model for socio-technical systems; University of São Paulo; Brazil.

Mbaya, Maweja. (2002) "Linguistic taboo in African marriage context: A study of the Oromo Laguu." Nordic Journal of African Studies: 224-235

Mary Dauglas (1966); Purity and danger; an analysis of concepts of pollution and taboo; London And newyork; published in the Taylor & Francis e-Library, 2001

Muhammad, Aminu, et al. (2015) “Taboo Across Cultures: A Reading of Selected Nigerian/African Literary Texts.” Journal of Humanities and Social Science 20.9 : 01 — 03

Ndulo, Muna, (2011) "African Customary Law, Customs, and Women's Rights" Cornell Law Faculty Publications. Paper 187.

Okpewho, Isidore. (1992). African Oral Literature: Background, Character, and Continuity. Bloomington and Indianapolis; Indiana University Press.

Oluwakemi Akintana, Sarah Jewittb, Mike Clifford (2018). Culture, tradition, and taboo: Understanding the social shaping of fuel choices and cooking practices in Nigeria. journals

Osei, Joseph. (2006) "The value of African taboos for biodiversity and Sustainable development." Journal of Sustainable Development in Africa 8.3: 42-61.

Oxford Online Dictionary of English.2010-11-11.

http://oxforddictionaries.com/view/entry/m_en_gb0840030#m_en_gb0840030

Sims, Martha.C. And Stephens, Martine. (2005)፡ Living Folklore: An Introduction to Study of People and their traditions.Utah state university press, USA,

Suvi Keturi and Tiina Lehmonesn:- (2012)፡ A Study of Taboo Content in Finnish EFL Textbooks for Upper Secondary School; Master's Thesis; University of Jyväskylä; Department of Languages English; February 2012

Sunstein, Cass (2013); Social norms and rules; Cambridge University press.

Toelken, Barre. (1996): Dynamics of folklore. Logan: Utah State Univeristy Press,

WIPO/ World Intellectual Property Organization (2013) Customary law an intellectual property system: the issues Geneva; Switzerland

Yohannes ejigu (2015); Amharic<>English Dictionary; fyn system

## የመረጃ አቀባዮች ስም ዝርዝር

### 1.አብይ መረጃ አቀባዮች

| ተ.ቁ | ስም | ፆታ | ዕድሜ | አድራሻ | ስራ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ አስፋው ሶሬ | ወ | 60 | ዶርዜ ሐ.ርጾ | የግል |
| 2 | አቶ ጋሞ ጋጎ | ወ | 55 | ››› | ሽመና/አርሶ አደር |
| 3 | አቶ አንዛ አለሙ | ወ | 75 | ››› | ሽመና/አርሶ አደር |
| 4 | አቶ አለቴ አደሬ | ወ | 75 | ››› | ሽመና |
| 5 | አቶ አበራ ገነኔ | ወ | 55 | አዲስ አበባ | የግል |
| 6 | አቶ ተሾመ ከበደ | ወ | 45 | ››› | የግል |
| 7 | ወ/ሮ ደቦቴ ደቃ | ሴ | 72 | ››› | የቤት እመቤት |
| 8 | ወ/ሮ ዲላዬ | ሴ | 45 | ዶርዜ | አርሶ አደር |
| 9 | ወ/ሮ ከሬሴ ከንዶ | ሴ | 85 | ዶርዜ | የቤት እመቤት |
| 10 | መ/ር ሲሳይ ሰይፉ | ወ | 25 | አርባ ምንጭ | መምህር |
| 11 | ወ/ሮ አበራሽ መሸሻ | ሴ | 55 | አዲስ አበባ | የቤት እመቤት |
| 12 | ወ/ሮ አበበች አለሙ | ሴ | 55 | ››› | ›› |
| 13 | ወ/ሮ አልማዝ | ሴ | 50 | ›› | ›› |
| 14 | አቶ ደርዛ አበበ | ወ | 72 | ›› | የግል |
| 15 | አቶ ጌሮ ጌምቤሮ | ወ | 78 | ዶርዜ አይራ | ጡረተኛ |
| 16 | አቶ አልታ አበበ | ወ | 80 | አዲስ አበባ | ጡረተኛ |
| 17 | ዎጋ አዴ | ወ | 90 | ››› | ጡረተኛ |

## 2.ንዑሳን መረጃ አቀባዮች

| ተ.ቁ | ስም | ፆታ | ዕድሜ | አድራሻ | ስራ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ዛዳ ሄቦ | ወ | 90 | ዶርዜ አይራ | ጡረተኛ |
| 2 | አቶ ገርቦ ገብሬ | ወ | 85 | ዶርዜ ሒርጶ | ››› |
| 3 | ወ/ሮ ወገሪ ያርሼ | ሴ | 60 | ዶርዜ ሒርጶ | የቤት እመቤት |
| 4 | አቶ ማናዬ ማዳ | ወ | - | አዲስ አበባ | ጡረተኛ |
| 5 | አቶ ነቃ ሊንዳ | ወ | - | አዲስ አበባ | ››› |
| 6 | ወ/ሮ ሀሙሴ ሀሞ | ሴ | 60 | ዶርዜ ሒርጶ | የቤት እመቤት |
| 7 | አቶ ደንበሌ ዳሮታ | ወ | 65 | አዲስ አበባ | የግል |
| 8 | አቶ ፍቃዱ ባንጃ | ወ | 50 | ››› | ››› |
| 9 | አቶብርሀኑ ወ/ሰንበት | ወ | 50 | ››› | ››› |
| 10 | ወ/ሮ ብርሀኔ ገ/ስላሴ | ሴ | 55 | አርባ ምንጭ | የቤት እመቤት |
| 11 | ወ/ሮ ግርፌ ሙላቱ | ሴ | 65 | ዶርዜ | ››› |
| 12 | ወ/ሮ ጨፌ መኔ | ሴ | 60 | ››› | ››› |
| 13 | ወ/ሮ ሙኑቂ ገራ | ሴ | 65 | ››› | ››› |
| 14 | ሒርጶ ኢሺሬ | ሴ | 65 | አዲስ አበባ | ››› |